



# ሠሠሪዓለ ሰዶጎኖ




www.ethiopianorthodox.org

# ኢምፔሪያል /አስፋውና ቤተሰቡ/ ሆቴል



ባለ አራት ኮከቡ ሆቴላችን፡-

- እጅግ ምቹ የሆኑ የመኝታ ክፍሎች ከግል መታጠቢያ፣ ስልክ እና የሳተላይት ቴሌቪዥን አገልግሎት
- ዘወትር ሐሙስ ማታ የጋስታ ምሽት፣ ቅዳሜ ባሕላዊ የምሽት ፕሮግራም ያለው ምግብ ቤት
- ለስብሰባ፣ ለሠርግ እንዲሁም ለሌሎች ዝግጅቶች የሚሆኑ አዳራሾች ከተሟላ መስተንግዶ ጋር
- በጃዝ የሙዚቃ መዝናኛ ክበብ
- የምሽት ክበብ
- የእንፋሎት መታጠቢያና የመታሻ አገልግሎት
- የተሟላ የጅምናዚየም አገልግሎት
- የተሟላ የፋክስ፣ የኢ-ሜል፣ የፎቶ ኮፒና የጽህፈት አገልግሎት

## አዘጋጅቶ ይጠብቅዎታል

በበለጠ ለመረዳት ብቅ ብለው የአገልግሎታችንን ብቃትና ጥራት ይመልከቱ!

ጥያቄ ቢኖርዎ፣ በስልክ ቁጥራችን 614490 ይደውሉልን ወይንም 614493 ፋክስ ይላኩልን

አድራሻችን፣ ከቦሌ ወደ መገናኛ በሚወስደው መንገድ

# ኢምፔሪያል ሆቴል
## ስሙን የሚመጥን


# መልእክተ አድኅኖ

1992 ዓ.ም

•

በወርቅ ጉር ቅዱስ ገብርኤል የቤተክርስቲያን ሥራና የልማት ኮሚቴ የቀረበ

•

አዘጋጅ

በየነ ሞገስ

•

የዝግጅት ክፍል

. ታደሰ ታምራት ፕ/ር
. ኃይለ ገብርኤል ዳኜ ዶ/ር
. ንጉሤ ኃብተ ሚካኤል
. አበበ ወርቄ
. ፍሥሐ ኃይለ መስቀል ዶ/ር
. በየነ ሞገስ

•

የሽፋን ሥዕል

አርቲስት ልዑል ሰገድ ረታ

•


✉ 4043
☎ 18-35-05/55-15-40
ፋክስ 251-1-55-19-44
E-mail: bmb9201@hotmail.com
አዲስ አበባ


## ማውጫ


መልእክተ አድኅኖ . . . . . . . . . . . . . 2

አጼ ዘርዓ ያዕቆብና ተጉለት .
አጭር የታሪክ ዘገባ . . . . . . . . . . . . . 3

የኢትዮጵያ ማንነትና ባህል
በ16ኛው ክፍለ ዘመን የፖርቹጋል ውለታ . . . . 9


የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
ለአገሪቱ ሕግ ቀረፃና ልማት ያደረገችው አስተዋፅኦ . 15

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት መካናት
ንብረቶች በኢየሩሳሌም . . . . . . . . . . . 18

ባህላዊ የቤተ ክህነት ትምህርት ከየት ወዴት? . . . . 26

ማኅበራዊ ሕይወት በተጉለት ወግዳ . . . . . . 30

የወርቅ ጉር ገዳመ አድኅኖ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን
ሥራና ልማት ኮሚቴ ዓላማ፣ ስልትና ክንውን . . . 34

www.ethiopianorthodox.org

# መልእክተ አድኅኖ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርትን በማስፋፋት፣ የተለያዩ የኪነ ጥበባት ዘርፎችን በማበልጸግ፣ ፍቅርን በማስተማር፣ የአገር ዳር ድንበርንና ነፃነትን በማስከበርና ይህን በመሳሰሉ ብዙ ተግባራት ያደረገችው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው። ቀደምት አባቶቻችን ቤተ ክርስቲያንን ማዕከል በማድረግ ያቆዩልን ትሩፋቶች ጉልህ እንደ መሆናቸው እነዚህን ጠብቆና አበልጽጎ ተተኪው ትውልድ እንዲያውቃቸውና እንዲጠቀምባቸው ማድረግ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።

የወርቅ – ጉር ቅዱስ ገብርኤል የቤተ ክርስቲያን ሥራና ልማት ኮሚቴ ከሚያራምዳቸው ዓላማዎቹ አንደኛው እነዚህንና ተመሳሳይ የቤተ ክርስቲያንን ተግባራት በተቻለ መጠን በስፋት ማስተዋወቅ በመሆኑ፣

- በኢትዮጵያ ታሪክ የጎላ ሥፍራ ካላቸው ነገሥታት መካከል አንዱ የሆነው አፄ ዘርዓ ያዕቆብ በዘመነ መንግሥቱ የፈጸማቸውን መንፈሳዊ ተግባራት፣ በወቅቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ማዕከል የነበረውን ተጉለትን መሠረት በማድረግ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑት ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት ያቀረቡት የታሪክ ዘገባ፣
- አርክቴክት ግርማ ሞገስ በተለያዩ ጊዜያት በኢትዮጵያ ኪነ ጥበብ ታሪክ ላይ የተካሄዱ ውይይቶች የነበራቸውን እንድምታና በ16ኛው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ላይ የተካሄደውን ወረራ ለመመከት ፖርቹጋሎች ስለ ፈጸሙት ተጋድሎ የሚገልጽ፣
- ቤተ ክርስቲያን በሕግ ቀረፃና ልማት በኩል ለአገሪቱ ስላደረገችው አስተዋፅኦ የሕግ ባለሙያ የሆኑት አቶ አበበ ወርቁ ፍትሐ ነገሥትን መሠረት በማድረግ የሰጡት ትንታኔ፣
- የክርስትና ምንጭ በሆነችው በኢየሩሳሌም ንብረት ካላቸው አብያተ ክርስቲያናት መካከል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አንደኛዋ መሆኗ ይታወቃል። በንብረቶቹ ላይ በተለያዩ ጊዜያት ተቀናቃኞች እንዴት እንደ ተነሡ፣ ይህንንም ለመመከት የተወሰዱት እርምጃዎች ምን እንደሚመስሉ አምባሳደር ተፈራ ኃይለ ሥላሴ በምርምር በማስደገፍ ያቀረቡት ጽሑፍ፣
- ባህላዊ የቤተ ክህነት ትምህርት በአገራችን ማኅበራዊም ሆነ መንፈሳዊ ሕይወት ላይ ያለው ድርሻ ከፍተኛ መሆኑ አያጠያይቅም። የዚህን ባህላዊ ትምህርት አመጣጥና ዕድገቱን፣ ዘመናዊው አወቃቀር ያስከተለበትን ችግር፣ የወደፊት ሁኔታውም ምን እንደሚመስል ለብዙ ዓመታት በዩኒቨርሲቲ መምህርነት የታወቁት ዶ/ር ኃይለ ገብርኤል ዳኜ አስተያየታቸውን ያቀረቡበት፣
- የወግዳ አማራ ገበሬ ሕዝብ የችግር ኑሮው ያስከተለበትን ውጣ ውረድ በማስመልከት በቅርቡ አንድ መጽሐፍ የጻፉት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር ዶ/ር ያሬድ አማረ፣ በተለይ ለዚህ መጽሔታችን ስለ አገሩ ማኅበራዊ ሕይወት ያዘጋጁት ጥናታዊ ጽሑፍና፣
- የወርቅ – ጉር ቅዱስ ገብርኤል የቤተ ክርስቲያን ሥራና ልማት ኮሚቴ ያቀረበው የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅድ በዚህ የመጽሔታችን እትም እንዲወጡ ተደርጓል።

በቀረቡት ጽሑፎች ላይ ሊነሡ የሚችሉ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ቢኖሩ ለመጽሔቱ የዝግጅት ኮሚቴ ቢላኩለት፣ በሚቀጥለው እትም ላይ እናስተናግዳለን። ይህም ሲሆን መጽሔታችንን የክርስቲያናዊ ባህላችንና ታሪካችን መወያያ መድረክ በማድረግ ልናዳብረው እንችላለን የሚል እምነት አለን።

የወርቅ ጉር ቅዱስ ገብርኤል
የቤተ ክርስቲያን ሥራና ልማት ኮሚቴ



# አፄ ዘርዓ ያዕቆብና ተጉለት

## አጭር የታሪክ ዘገባ

ከፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት

ይህ በየመቱ ታኅሣሥ 19 ቀን፣ በአንድነት እየተሰባሰብን መጥተን፣ በዓሉን የምናከብርለትና በብዙ ምዕመናን መንፈሳዊ ትብብር ዘመናዊ ሕንፃ እየተሠራለት ያለው የወግዳ ወርቅ–ጉር ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የሚገኝበት አካባቢ፣ የዛሬ ስድስት መቶ ዓመት ያህል የኢትዮጵያ መንግሥት ማዕከላዊ አካባቢዎች ከሚባሉት ሥፍራዎች አንደኛው ነበር። በዘመኑ በጠቅላላው የክርስቲያን ዓለምና በተለይም በመካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ እጅግ በጣም ዕውቅ የነበረው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አፄ ዘርዓ ያዕቆብ (1426–1460) በዚያን ጊዜ ነበር ዋና መዲና ከተማውን ደብረ ብርሃን ላይ የቆረቆረው። በወርቅ–ጉርና በደብረ ብርሃን መካከል ያለው ትልቅ ወንዝ፣ ስሙ ወራሪ ነበር በዚያን ዘመን። ይህ ወንዝ አሁንም ቢሆን በሚነሣባቸው ተራራዎች አካባቢ፣ በዚያው ስም ነው የሚጠራው። ብዙ ቆይቶ ነው፣ በተለይ ከታች በኩል ያለው ፍሳሹ በሬሣ የሚል ስም የተሰጠው።

ባጠቃላይ የመንዝና የተጉለት አካባቢ የቤተ መንግሥትና የመንግሥት ሠራዊት መናኸሪያ መሆን የጀመረው ከዚያም ጊዜ በፊት ቀደም ብሎ ነው። ከዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ስድስት ትውልዶች ያህል ቀደም ብሎ «ሰሎሞናዊ» እየተባለ የሚጠራውን፣ እስከ አፄ ኃይለ ሥላሴ (1923–67) ፍጻሜ መንግሥት ድረስ ሲታሰብ ለሰባት መቶ ዓመታት ያህል ኢትዮጵያን ከተለያዩ ማዕከሎች ሲያስተዳድር የቆየውን ዝነኛ የአማሮች ሥርወ–መንግሥት ያቋቋመው አፄ ይኩኖ አምላክ (1262–77)፣ ከግሸንና ከሐይቅ ጀምሮ እስከዚህ የሰሜን ሸዋ ደጋማ አገር ድረስ ባለው አካባቢ ነበር የመንግሥት ምሥረታውንና የግዛት ማስፋፋት እንቅስቃሴውን የጀመረው። የዘርዓ ያዕቆብ ቅድመ–አያት፣ ዝነኛው አፄ አምደ ጽዮን (1306–1336) ደግሞ፣ እንዲያውም ከተጉለት እየተነሣ ነበር ምድረ ሸዋን በሙሉ ከሰሜን እስከ ደቡብና ከምዕራብ እስከ ምሥራቅ በሥልጣኑ ሥር ተዋሕደው እንዲተዳደሩ ያደረጋቸው። ከተጉለትና ከመንዝ አፋፍ በተደጋጋሚ እየወረደ ነበር የአርጎባ ሕዝብንና ወላስማ በሚል ጥንታዊ የማዕርግ ስም የሚጠራውን መሪያቸውን በማግባባት የቀድሞው የይፋት አካባቢ በመላው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ውስጥ ተጠቃሎ ከሸዋ እስከ ኤደን ባሕረ ሰላጤ ያለው ረጅም የንግድ ጐዳና ለሁሉም ክፍት እንዲሆን ያስቻለው። አፄ ዓምደ ጽዮን በዚህ ዓይነት ነበር አሁን ሸንኮራና ምንጃር በሚባሉት ሥፍራዎች አግጣጫ፣ በዘመኑ ግን ፈጠጋር፣ ደዋሮ እየተባሉ እስከ አዋሽ ባሻገር ያሉትን አገሮች፣ ከዚያም አልፎ ባሌንና አካባቢዎቹን፣ በስተደቡብ ደግሞ በዘመኑ የሐድያ መንግሥት ይባል የነበረውን፣ በአሁኑ ጊዜ ከአርሲ እስከ አባያታ ሐይቅ ባሉት አውራጃዎች በስፋት ተዘርግቶ የነበረውን አገር ሁሉ በአስተዳደሩ ሥር በማስገባት፣ አያሌ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በቀጥታ የሚገናኙበትና ሰፊ ባህላዊና ሕዝባዊ መቀራረብ ማድረግ የሚችሉበት አንድ መንግሥታዊ መዋቅር ያጠናከረው!

የዓምደ ጽዮን ልጆችና የልጅ ልጆችም፣ ይህን ጠንካራ መነሻ ይዘው ነበር ለብዙ ምዕት ዓመታት በዚህ የግንባታ እንቅስቃሴ የቀጠሉበት። የአብዛኛዎቹም የሥልጣን መናኸሪያ በወግዳ ወርቅ–ጉር ዙሪያ ያለው የተጉለት አውራጃ እንደ ነበረ ሰነዶቹ በግልጽ ይናገራሉ። ይፋትን፣ መንዝን፣ ተጉለትንና የሸዋን ደጋማ ምሥራቃዊ ጫፍ እምብዛም ይርቅ፣ አሁን ጠራ፣ ቡልጋ ሸንኮራና ምንጃር የሚባሉትን አውራጃዎች፣ እስከ አዋሽ መሻገሪያ ያለው አካባቢ የሥልጣናቸው ዋነኛ መድረክ ሆኖ ነበር ማለት ይቻላል።

ይልቁንም ዓመት ካመት ግዛታቸው ከሸዋ ደጋማ አገር በስተሰሜን፣ በስተምዕራብ፣ በስተ ምሥራቅና በስተደቡብ ብዙ እየተስፋፋ ሲሔድ፣ ባጠቃላይ እነዚህ የሸዋ አውራጃዎች የመንግሥቱ አማካይ የልብ ሥር እየሆኑ መሔዳቸው በጣም ግልጽ ሆኖ ይታያል። ከዚህ ማዕከል እየተነሣ ነበር ታዲያ ወደ ሰሜን እስከ ኻማሴንና እስከ ባሕረ ኤርትራ፣ ወደ ሰሜን ምዕራብ እስከ ሰሜን ተራራና እስከ መተከል፣ ወደ ምሥራቅ እስከ ዜይላ፣ ወደ ምዕራብ በጥንቱ ዳሞት ዳርቻ ይኖሩ እስከ ነበሩት የዓባይ ሰኻራዊ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦች አገር ድረስ፣ በስተደቡብ ደግሞ እስከ ኦሞ ሸለቆ ድረስ በያግጣጫው የነገሥታቱ ሠራዊትና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መምህራን በሰፊው ተሰማርተው የአንድ አገር ግንባታውን ተግባር ሲያካሒዱ የነበረው!



www.ethiopianorthodox.org

አፄ ዓምደ ጽዮንና ከሱ በኋላ ደግሞ የልጅ ልጁ አፄ ዳዊት፤ በተጉለት ውስጥ በተለይ መርዓዴ የተባለችውን ሥፍራ ያዘወትሩ ነበር። ይህች ቦታ እስካሁን የት አካባቢ እንደሆነች በውል የታወቀ ነገር የለም። ዓምደ ጽዮን ከደብረ ሊባኖስ የሦስት ቀን ርቀት ባላት፤ እሷም የት እንደሆነች ገና ማወቅ ባልቻልናት፤ ሰዌን በምትባል ሌላ ሥፍራ ይቆይ እንደ ነበር ይታወቃል። የልጅ ልጁ አፄ ይስሐቅም፤ ከብዙ ዓመታት በኋላ በዚሁ ሥፍራ ይከርም እንደ ነበረ ማስረጃ አለ። የዘርዓ ያዕቆብ አባት አፄ ዳዊት፤ በመጀመሪያ አሁን ደብረ ሲና በምትገኝበት አካባቢ ጦቢያ በምትባል ቦታ፤ በኋላ ደግሞ ጥልቅ በምትባል፤ ቀድሞ ፌጠጋር፤ አሁን ግን ምንጃርና ናዝሬት በሚገኙበት አካባቢ በነበረች ሌላ ለምለም ሥፍራ ይኖር እንደ ነበረ የጊዜው ሰነዶች ያሳያሉ። በዚች ሥፍራ፤ በተለይ ቤተ መንግሥቱ፤ ረዘም ላለ ጊዜ የቆየ ይመስላል። ዳዊት ሠራዊቱን እየመራ እስከ ዜይላ ድረስ የዘመተው ከዚሁ ከጥልቅ ቤተ መንግሥት ተነሥቶ ሳይሆን አይቀርም። ዝነኛው ልጅ ዘርዓ ያዕቆብ ራሱ የተወለደው እዚሁ ጥልቅ በነበረው ቤተ መንግሥት ውስጥ እንደ ነበረ የታወቀ ነው።

የቀደምቶቻችን ዘመናት ዘመቻ የሚበዛባቸውና ብዙ ጉዞዎች የሚታይባቸው ነበሩ። በዚህም ምክንያት የቀድሞዎቹ ነገሥታት አብዛኛውን ጊዜ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወሩ ያለ ዋና መዲና ከተማ ነበር ዘመናቸውን የጨረሱት። ከአባቱ፤ ከአያቱና ከቅድመ አያቱ ዘመናት ሲነፃፀር ግን፤ የአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ሰፋ ያለ የመረጋጋትና የግምባታ ዘመን መስሎ ይታያል። አንዱም የዚህ ምልክት ዘርዓ ያዕቆብ ራሱ፤ ልክ የወራሬ ወንዝ ወደ ሰሜን ምዕራብ ከሚታጠፍበት ማዕዘን በስተሰሜኑ ባለው ገዢ ኮረብታ ላይ ደብረ ብርሃንን ዋና መዲናው አድርጎ መከተሙ ነው። በዚያውም ዘመን ውስጥ በከተማውና በአካባቢውም ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን እንደ መሠረተ ይነገራል።

ዘርዓ ያዕቆብ የመጨረሻ 12 የግዛት ዓመታቱን ያሳለፈውና በመጨረሻም ያረፈው በደብረ ብርሃን ቤተ መንግሥቱ ውስጥ ነው። እነዚህ ዓመታት፤ በመንግሥት አስተዳደርም ሆነ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን በኩል ብዙ ታላላቅ ተግባሮችን የፈጸመባቸው ዘመናት ናቸው። ይልቁንም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በተለይ የሚታወቅባቸውን ብዙዎቹን ሃይማኖት ነክ ተግባሮቹን የፈጸመው ቤተ መንግሥቱ እዚሁ ደብረ ብርሃን ከተማ በነበረበት ጊዜ ውስጥ ይመስላል። በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ብዙ የሃይማኖት ውዝግብ ተነሥቶ እንደ ነበረ ይታወቃል። ለዚህ ሁሉ ውዝግብ መፍትሔ ለመፈለግ፤ ንጉሠ ነገሥቱ ከየክፍለ ሀገሩ እጅግ በጣም ዕውቅ የነበሩትን ታላላቅ ሊቃውንት እያስጠራ በደብረ ብርሃን ቤተ መንግሥቱ ውስጥ ብዙ የሃይማኖት ጉባኤዎች አካሒዷል። እሱም ራሱ በጣም የተራቀቀ የሥነ መለኮት (Theology) ምሁር ስለነበረ፤ ካህናቱ በመካከላቸው የሚያደርጉትን የሐሳብ ልውውጥ እየሰማ ማከራከር ብቻ ሳይሆን፤ እሱም ራሱ ክርክሩ ውስጥ እየገባና መጻሕፍትን እያመሳከረ በመተርጎም በቀጥታ ይሳተፍ ነበር።

ዘርዓ ያዕቆብ ታላቅ የሃይማኖት ሊቅ ከመሆኑ የተነሣ፤ እስካሁን ድረስ እጅግ በጣም የተከበሩ ድርሰቶችን እንደ ደረሰ ይታመናል። በዚህ ምሁር ንጉሠ ነገሥት ከተደረሱት ታላላቅ የሃይማኖት መጻሕፍት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

- ጦማረ ትስብእት
- መጽሐፈ ብርሃን
- መጽሐፈ ሚላድ
- ክሕደተ ሰይጣን
- መጽሐፈ ባሕርይ
- ተአቅቦ ምሥጢር
- እግዚአብሔር ነግሠ

ታዲያ እነዚህን ሁሉ መጻሕፍት የደረሳቸው ከዚህ ከኛው ከወገዳ ወርቅ–ጉር አጠገብ፤ ልክ የወራሬ ወንዝን ተሻግሮ በምትገኘዋ የደብረ ብርሃን ከተማው ውስጥ በነበረባቸው ዓመታት ውስጥ ነው!

በዚሁ በደብረ ብርሃን ቤተ መንግሥቱ በነበረበት ጊዜ የፈጸመው አንድ ሌላ ታላቅ ታሪካዊ ተግባር፤ በዘመኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ እጅግ በጣም የተመሰገነበት ሥራ ነበር። በዚያን ዘመን የኢትዮጵያ ጳጳሳት የሚመጡት ከግብፅ በእስክንድርያው ፓትርያርክ ተመርጠው እየተሾሙ እንደ ነበር የታወቀ ነው። ታዲያ ለዘርዓ ያዕቆብ አቡነ ሚካኤል፤ አቡነ ገብርኤል የተባሉ ሁለት በጣም የተከበሩና ምሁራን የሆኑ ጳጳሳት ተልከውለት በፍቅርና በሙሉ የመተባበር መንፈስ እያገለገሉት ነበር የሚኖሩት። ባጠቃላይ በዚያ ዘመን በጣም ሀብታምና ኃያለኛ የነበረው የኢትዮጵያ መንግሥት፤ ለግብፅ ቤተ ክርስቲያንና ለምዕመናኗ ታላቅ መመኪያቸው እንደ ነበር ታሪክ ይመሰክራል። በያመቱ ለፓትርያርኩ ብዙ ወርቅና የተለያዩ ብርቅዬ ስጦታዎች ይላካሉ። የግብፅ እስላም ገዥዎች፤ ክርስቲያኖቹንና ፓትርያርካቸውን ሲያንገላቱባቸውና ግብፃዊ ክርስቲያኖች አቤቱታ ሲልኩባቸው፤ የኢትዮጵያ ነገሥታት በልመናም ሆነ በማስፈራራት







በተቻለ መጠን ምንም ጥቃት እንዳይደርስባቸው አጥብቀው ይከራከሩላቸው ነበር።

ታዲያ ከዕለታት አንድ ቀን አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ደብረ ብርሃን እንዳለ ከእስክንድርያው ፓትርያርክ አንድ የኀዘን ደብዳቤ ይደርሰዋል። ደብዳቤውም

> እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሕፃን ልጇን ይዛ ወደ ግብፅ ተሰዳ በነበረበት ጊዜ አርፋበት በነበረው የመቅደስ ቦታ ላይ ተሠርቶ ለብዙ ምዕት ዓመታት የተለያዩ ድንቅ ተአምራት ሲታዩበት የነበረውን የደብረ ምጥማቅ ቤተ ክርስቲያን እስላሞቹ በቅናትና በቁጣ አቃጠሉት፤

የሚል አቤቱታ ነበር። ይህን ሲሰማ ዘርዓ ያዕቆብ እጅግ በጣም አዘነ፤ በጣም ተቆጣ። ሁለቱንም ጳጳሳቱን ይዞ በደብረ ብርሃን ከተማ ታላቅ የኀዘን ጉባኤ አካሔደ። ከፍተኛ ኀዘኑንና ቁጣውን የሚገልጹ ደብዳቤዎችንም ለግብፁ እስላም ገዥና ለፓትርያርኩ ወዲያውኑ ላከ። ከዚህ የበለጠ ግን፤ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ፤ በጉባዔው ላይ በተሰበሰበው ሕዝብ መካከል እንዲህ ንጉሣዊ መሐላ አደረገ።

> እንደ ግብፅ ውስጥ በምዕራቡ ሥልጣኔ ሥር የምትገኘውን ደብረ ምጥማቅ ቢያቃጥሉም፤ እኛ እዚህ በሀገራችን ውስጥ በአንድ የተጉለት ማዕከላዊ ሥፍራ ሌላ የራሳችን የሆነች ደብረ ምጥማቅ እንሠራለን፤

ብሎ አወጀ። እንዳለውም በጥቂት ጊዜ ውስጥ ሌት ተቀን እየሠራ በተጉለት ምድር ሕንፃውን አሳምሮ አስጨረሰና በሚያከብራቸው በአቡነ ገብርኤልና በአቡነ ሚካኤል አስባርኮ፤ የራሱን ደብረ ምጥማቅ በታላቅ ድምቀት መረቃት! በተጉለት ሰሜን ጫፍ ላይ እስከ ዛሬ ድረስ የምትገኘው በታሪካችን ውስጥ ታላቅ ሥፍራ ያላት የደብረ ምጥማቅ ቤተ ክርስቲያን ከዛሬ 550 ዓመታት በፊት የተመሠረተችው በዚህ ዓይነት ነው።

ቤተ ክርስቲያኒቱ ከተቋቋመች በኋላ፤ በእስክንድርያና በኢትዮጵያ መካከል ላለው የቅርብ ግንኙነት ልዩ ማስታወሻ ይሆን ዘንድ በቤተ ክርስቲያኒቱ ዙሪያ የሚኖረው ክርስቲያን ሕዝብና የመሬቱ ይዞታ በግብፃውያን ጳጳሳት ርስት ጉልትነት እንዲተዳደር በዚያን ጊዜ የተወሰነ ይመስላል። ከዚያ ወዲህ በዳግማዊ አፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት መጥተው እስከ ዕለተ ዕረፍታቸው ድረስ ለብዙ ዓመታት ጠንካራ መንፈሳዊ አመራር ይሰጡ የነበሩት አቡነ ማቴዎስ፤ በደብረ ምጥማቅ አጠገብ ሰላድንጋይ ላይ የቅዱስ ማርቆስን ደብር በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድና ድጋፍ አሳምረው ያሠሩት፤ ይህንኑ ከእስክንድርያው መንበረ ማርቆስ ጋራ የነበረውን ጥንታዊና የፍቅር አንድነት እንደ ገና ለማደስ አስበው ሳይሆን አይቀርም።

አፄ ዘርዓ ያዕቆብ በደብረ ብርሃን ቤተ መንግሥቱ ሆኖ ከሠራቸው ሌሎች ዋና ዋና ነገሮች መካከል ሕዝቡ በአስማት ደጋሚዎችና በጠንቋዮች እየታለለ እንዳይጎዳ ብዙ የሃይማኖት ትምህርት እንዲሰጠውና በዚህ ዓይነት የማጭበርበር ተግባር ላይ የተገኙትንም በጥብቅ እንዲቀጡ ማድረጉ በተለይ ይጠቀሳል። የዚህ ዓይነቱን ጥፋት ሲያደርጉ የተገኙት ሁሉ፤ ካህናትም ሆኑ ወይም መሃይምን፤ ተራ ሰዎች ሆኑ ወይም የባላባት ወገኖች፤ ሁሉንም ሳያበላልጥ ይፈርድባቸውና ያለ ምንም ርኅራኄ ይቀጣቸው ነበር እየተባለ እስካሁን ድረስ ይተረክለታል። ይህንን በሚመለከት የራሱን ልሁሳን ልጆች፤ የቤተ መንግሥት ሴት ወይዛዝርትና ከፍተኛ ባለ ሥልጣኖቹን እንኳን ሳይቀር ምንም ሳይምር ይቀጣቸው እንደ ነበረም በዜና መዋዕሉ ተመዝግቦ ይገኛል። እንዲያውም የከተማው ስም ደብረ ብርሃን የተባለው የዚህ ዓይነት ቀጥተኛና አድልዎ የሌለበት ፍርድ በሰጠበት በአንደኛው ቀን በልዩ ተአምር በቤተ ክርስቲያኑና በቤተ መንግሥቱ አጠገብ ከሰማይ አስደንጋጭና አስገራሚ ብርሃን ወርዶ በመታየቱ ነው የሚል ጠንካራ እምነት አለ።

ከዚህም ባሻገር፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን የበዓላትና የጸሎት ሥነ ሥርዓቶች በውል መሠረት ያስያዘ ሊቁ ዘርዓ ያዕቆብ እንደ ነበረ ይታወቃል። በተለይ ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ድንቅዩ ተአምራት የሚያወሳው ተአምረ ማርያም የተባለው መጽሐፍ፤ በአባቱ በአፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ ወደ ግዕዝ መተርጎም ቢጀምርም፤ ትርጉሙን ራሱ በቅርብ እየተከታተለ ወደ ፍጻሜ ያደረሰው ዘርዓ ያዕቆብ ስለሆነ፤ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደ ታላቅ ባለውለታ አስቆጥሮታል። ከዚያን ጊዜ ወዲህ ነው በተለይ ተአምረ ማርያም በየቤተ ክርስቲያኑ እየተነበበ ለምዕመናን የሁል ጊዜ አለኝታና መንፈሳዊ እርካታ እንዲሰጥ የተደረገው። ይልቁንም በየዓመቱና በየወሩ ሊደረጉ የሚገባቸውን በዓላት ሳይቀር በዝርዝር ደንግጎ ክርስቲያኖች ሁሉ በጥንቃቄ እንዲያከብሯቸው ያስተላለፈው መመሪያ ለብዙ ምዕት ዓመታት ተጠብቆ በመኖር እስካሁን ድረስ ይገኛል።

እነዚህ ሁሉ ተግባራት በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ለዚህ ንጉሥ እንደ ሕያው ቋሚ ሐውልቶች ይቆጠሩለታል። በዚህም ምክንያት፤ ንጉሠ ነገሥትነቱ ካስመዘገባቸው የአስተዳደርና ሰፊ የሕዝቦች ግንኙነት ሥራዎቹ ባሻገር ስለ ሃይማኖትም ጥራትና ዝርዝር የቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት በሙሉ ኃላፊነት ይሰጥ የነበረው አመራር በዚያ የጥንት ዘመን መንግሥትና ቤተ ክህነት ለነበራቸው የጠበቀ ትስስር እንደ ዋና ምሳሌ እንዲወሰድ አድርጎታል። በእነዚህ፤ ልክ ከወንዙ ባሻገር በቅርብ በሚታየው የደብረ ብርሃን ቤተ መንግሥት በተከናወኑት ታላላቅ ሥራዎች አፈጻጸም ሂደት ውስጥ፤ እንደ ወገዳ ወርቅ–ጉር ባሉት አካባቢዎች ይኖር የነበረውም ኅብረተሰብ ቀጥተኛ ተሳትፎ እንደ ነበረው ምንም አያጠራጥርም። ስለዚህም ወደፊት



www.ethiopianorthodox.org

በጠንቃቄ ማካሔድ ለሚገባን የወግዳ ወርቅ–ጉር ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያንና የአካባቢው የታሪክ ጥናት የአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ከፍተኛ አብነት እንደሚኖረው መገመት አስቸጋሪ አይሆንም።

በአጠቃላይ፣ የአፄ ዘርዓ ያዕቆበ ዘመነ መንግሥት፣ በተለይ ለመላው ተጉለትና ለአካባቢው የወርቅ ዘመን ነበር ማለት ይቻላል። ነገር ግን ይህ አጠቃላይ ሁኔታ፣ በወርቅ–ጉር ገብርኤልና በሌሎቹ የወግዳ አብያተ ክርስቲያናት ዝርዝር ታሪክ ውስጥ በትክክል እንዴት እንደሚንጸባረቅ ማወቅ የምንችለው፣ በዚህ አካባቢ ሊገኙ ከሚችሉ የጥንት ጽሑፎች፣ ሌሎችንም ቅርሳ ቅርሶችና የአካባቢውን ወግና ታሪክ ከሚያውቁ አዛውንቶች ጋራ እየተነጋገርን ትምህርት በማግኘት ብቻ ነው። እነዚህን ወሳኝ መረጃዎች በማፈላለጉና ጥናቱን በማመቻቸቱ አኳያ፣ የአካባቢው ካህናትና ምዕመናን ሁሉ ሙሉ ድጋፍ ለመስጠት እንዲዘጋጁ በዚህ አጋጣሚ መጠየቅ እንወዳለን!

እስካሁን ድረስ ከአካባቢው አንዳንድ የታወቁ ሽማግሌዎች ጋራ ልናደርጋቸው በቻልናቸው ውይይቶችና በወርቅ–ጉር ዙሪያ ከተካሔደ አንድ አጭር ጥናታዊ ጉብኝት ከተገኙ አስተማማኝ የሚመስሉ መረጃዎች እንደሚታየው፣ በዚህ በወግዳ ወረዳ ያሉ ብዙ የተራራ ጫፎች፣ ኮረብታዎች፣ ሸንተረሮች፣ ዋሻዎችና ሸለቆዎች ሁሉ በአብያተ ክርስትያኖች የተሞሉ ናቸው። ብዙዎቹ አመሠራረታቸው ጥንታዊነት ያለው ነው። ለምሳሌ ከወርቅ–ጉር ገብርኤል ፊት ለፊት ደረቱን ሰጥቶ ከሚታየው እስካሁን ድረስ መለከ–ድብ በሚለው ጥንታዊና ታሪካዊ ስም ከሚጠራው ታላቅ ተራራ ስር ያለችው ሰገድ ማርያም፣ በአካባቢው ካሉት ሁሉ አስቀድማ የተመሠረተች መሆኗን መገንዘብ ተችሏል። ምሥረታዋም ቢያንስ ቢያንስ እስከ አፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት ሊደርስ የሚችል ይመስላል። በተለይም በዘርዓ ያዕቆብ ዘመን የነበሩት የቤተ መንግሥትም ተወላጅ የሆኑትና በጣም የታወቁተ ጻድቅ አቡነ መባዓ ጽዮን ይጸልዩባት እንደነበረ አንዳንድ ፍንጭ ተገኝቷል።

ከወርቅ–ጉር አጠገብ ከሚገኙ ሌሎች ጥንታውያን ቤተ ክርስቲያኖች መካከል አንደኛው አፄ ዋሻ ማርያም የሚባለው ነው። ይህ ቤተክርስቲያን ከቤተ መንግሥት ጋር የተለየ ቅርበት ያለው መሆኑ በስሙ ብቻ ሳይሆን፣ ከስፍራው የመጡ አዛውንትም ከሚያስተላልፉት ባህላዊ ታሪክ ለመረዳት ይቻላል። ከደብረ ብርሃን ወደ ወርቅ–ጉር ሲመጣ፣ ታላቅ አምባ ከሚባለው አካባቢ አለፍ ብሎ ጎሼባዶ ከተማ ከተገባ በኋላ፣ በስተግራ በኩል ለጥቂት ደቂቃ ሲሔዱ፣ እይታው በጣም ከሚያምር አፋፍ ይደረሳል። ከዚህ አፋፍ በታች በስተግራ በኩል ከበርበሬ ወንዝ ከፍ ብሎ በሚታየው የተዋበ ሸንተረር መካከል ያለው አፀደ ቤተ ክርስቲያን የአፄ ዋሻ ማርያም ነው። ከሱ በስተምዕራብ ሲመለከቱ ያለው ከፍታ ጅለሎ ጋራ ይባላል። በሥሩ ያለው ወንዝም በጋራው ስም ጅለሎ ወንዝ ተብሎ ነው የሚጠራው። በርበሬ ወንዝና ጅለሎ ወንዝ፣ ሁለቱም የጫጫ ወንዝ ገባሮች ናቸው። ታዲያ አዛውንቱ እንደሚናገሩት፣ ጅለሎ ተራራ አፋፉ ላይ አፄ ይኩኖ አምላክ ከትሞበት ነበር ይባላል። ምናልባትም አፄ ዋሻ ማርያም የተመሠረተችው በዚያው ዘመን ሊሆን ይችላል።

ከዚህ በላይ ያነሣናቸው ሰገድ ማርያምና አፄ ዋሻ ማርያም በጣም ጥንታዊነት ስላላቸው እንዲያው በምሳሌነት ተጠቀሱ እንጂ ሌሎችም ብዙ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት በወርቅ–ጉር አካባቢ ይገኛሉ። ይህ አካባቢ የመንግሥት ማዕከል ሆኖ ለብዙ ምዕት ዓመታት ያገለገለ በመሆኑ፣ በተለያዩ ዘመናት የተከሰቱ፣ በተለይ በመንግሥት ላይ ያተኮሩ ግጭቶችና ወረራዎች ኢላማ እንደ ነበረም መገመት ይቻላል። ይልቁንም የአህመድ ግራኝ ዘመቻና ከዚያ በኋላ ለብዙ ዘመን እየተስፋፋ የሔደው የኦሮሞ ሕዝብ ሰፈራ ባስከተሉት ማኅበራዊ ግጭትና አለመረጋጋት ምክንያት የአካባቢው አብያተ ክርስቲያናት ተደጋጋሚ የስደትና የጥፋት አደጋ እንደ ደረሰባቸው የአገሩ አዛውንት እስካሁን ድረስ ከሚያቀርቡት ባህላዊ ትረካ ብቻ ሳይሆን ለየሸንተረሩ፣ ለየሜዳው፣ ለየአፋፉና ለየሸለቆው ከተሰጡት የቦታ ስሞችም ለመረዳት ይቻላል።

እዚህ አካባቢ ካሉት አብያተ ክርስቲያናት መካከል፣ ከጥንት ጀምሮ እስከ ቅርቡ የፋሽሽት ኢጣልያ ወረራ ድረስ ታቦቶቻቸው ከቀድሞ ቦታቸው ተነሥተው በየአቅራቢያው ወደሚገኝ ዋሻ እየተወሰዱ የደረሰባቸውን ክፉ ቀን ተደብቀው ያላሳለፉ ብዙም አይገኙ። አብዛኛውን ጊዜ ከፍ ካለው ደጋማ ሥፍራ ይሸሹና ዝቅ ወዳለው ሸለቆና ዋሻ ተወስደው ይደበቃሉ። እንደዚህ ባለው የችግር ጊዜ የአካባቢው ኢኮኖሚና የኑሮ ሁኔታዎችም ባጠቃላይ ስለሚናጉ፣ እንደዚሁም የብዙ ሰዎች ሕይወት ስለሚያልፍ፣ የካህናቱ ቊጥር እየቀነሰ ይሔዳል። በችግሩ ምክንያት በጣም ተጎድተው ደከም ያሉት አብያተ ክርስቲያናት፣ ታቦታቸው ለጊዜው ጠንከር ወዳሉት መቅደሶች እየተወሰደ በደባልነት እንዲቆይ ይደረጋል። ዘመናት አልፈው ችግሮች እየተቃለሉ ሲሔዱ፣ ከስደተኞቹ ታቦቶች መካከል አስታዋሽና ተቆርቋሪ ያላቸው፣ ከተቻለ ጥንት ወደ ነበሩበት ሥፍራ ተመልሰው፣ ካልሆነ ደግሞ ከየተደበቁበት ዋሻ ወይም በደባልነት ከቆዩበት መቅደስ ተነሥተው ትንሽ ሻል ወዳለ ከፍተኛ ስፍራ ይወሰዱና እንደገና አዳዲስ ቤተ ክርስቲያን እየተሠራላቸው ይወጣሉ። አንዳንዶቹ ካንዴም ሁለት ጊዜ በዚህ ዓይነት ከየተሰደዱበት ቦታ ወደ ተሻለ አዲስ ሥፍራ የተዘዋወሩ አሉ።

ይህ የቦታ ዝውውር እንቅስቃሴ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሲኪያሔድ መቆየቱን ባይናቸው ማየት የቻሉ አዛውንቶችንም ማነጋገር ተችሏል። አሁን ካለንበት ከወርቅ–ጉር አፋፍ ሆነን ወደ ፊት ለፊታችን ወደ ቆላው አገር፣ በስተግራም ሆነ በስተቀኝ ከሩቁ ስንመለከት የሚታዩን አፀደ ቤተ ክርስቲያናት፣ አብዛኞዎቹ የዚህ ዓይነት የመፈናቀል ታሪክ የደረሰባቸው ናቸው። ቀደም ብለን የጠቀስናቸው ሰገድ ማርያምና አፄ ዋሻ ማርያምም በዚሁ ዓይነት ብዙ ውጣ ውረድ ያሳለፉ መቅደሶች ናቸው። ብዙዎቹ ተጠናክረውና ተከብረው እንደገና ሊቋቋሙት የቻሉት፣ ከ18ኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ እየተጠናከረ በመጣውና ከጎንደር ቤተ መንግሥት በወታደራዊና በመንፈሳዊ የሰው ኃይል እየተደገፈ እያበበ በሔደው የሸዋ መንግሥት ዘመን መሆኑ ግልጽ ነው። እንዲያውም በጣም የታወቁት አብያተ ክርስቲያናት መምህራንና መሪዎች፣ የትውልድ ሐረጋቸውን የሚያጣቅሱት በዚሁ ዘመን ከጎንደር በመንዝ በኩል ወደ ሸዋ ከመጡ ታላላቅ ሊቃውንት መሆኑ ተደርሶበታል።

የዚህ የኛው የወርቅ–ጉር ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያንም ታሪክ ተመሳሳይ ሒደት እንደ ነበረው ማረጋገጥ ተችሏል። ከፊት ለፊቱ ከሚታየው ከሰገድ ማርያም በላይ ካለው የመለከ–ድብ ተራራ ወገብ ላይ ሆነን ወደ ወርቅ–ጉር አሻግረን ስንመለከት፣ የገብርኤል አፀደ ቤተ ክርስቲያን ከአካባቢው ሁሉ በተለይ ደምቆና ከበድ ብሎ ይታየናል። ለዚህ አንደኛው ምክንያት መቸም ይህ የኛው የቤተ ክርስቲያን ሥራና የልማት ኮሚቴ ባለፉት ስምንት ዓመታት ውስጥ በትጋት ሲያካሒድ የቆየው የዛፍ ተከላ ፕሮግራም መልካም ውጤት መሆኑ አያጠራጥርም። ከዚያ ባሻገር ግን ከመቃኞውና አዲስ ከሚሠራው ሕንፃ በስተጀርባ ዘወር ብለን ስንቃኝ፣ ብዙ ጥንታዊነት ያላቸው ዕፀዋትና ግንዶች እናገኛለን። ይልቁንም አሁን በሕይወት ያሉ ብዙ አዛውንት በልጅነታቸው ጊዜ ያላቸውን ትዝታ ሲያወጉን፣ ከሕፃንነታቸው ዘመን ጀምሮ ይህንን ስፍራ የሚያስታውሱት ከበድ ባለ ደንነቱና በአስፈሪነቱ እንደሆን አበክረው ዘግበውልናል። አሁን ጠና ጠና፣ ደከም ደከም ያሉ አዛውንት በወጣትነታቸው ዘመን በቡድን በቡድን እየሆኑ ለልጅነት የጉብዝና ጨዋታና ለወንድነት ወኔ ማዳበሪያ እየተባለ በወርቅ–ጉር ጫካ ውስጥ ብዙ የዕረፍት ጊዜያቸውን በማሳለፍ ይዝናኑ እንደ ነበር ናፍቆት የተሞላበት ትዝታቸውን አጫውተውናል። እንዲያውም ብዙ የሚያስፈሩ የደን አራዊት በሥፍራው መገኘታቸውንና አንዳንድ ጊዜም ወደ ቦታው ለአደን የሚመጡ ሰዎች እንደ ነበሩ ሳይቀር የሚያስታውሱ አዛውንት አሉ።

ይህ እንግዲህ የወርቅ–ጉር ቤተክርስቲያን የመጀመሪያ ምሥረታ ጥንታዊነት እንዳለው ሊያሳዩን ከሚችሉት ምልክቶች አንዱ ሊሆን ይችላል። ከዚህም በላይ ግን፣ ምንም እንኳን በዚህ ጊዜ ተመሠረተ ብሎ የተወሰነ ዘመን ለመጥቀስ የሚያስችለን ቀጥተኛ መረጃ ገና ባናገኝም፣ ከአካባቢው ጠቅላላ የታሪክ ሒደት ተነሥተን በቃል ሲወርድ ሲዋረድ የመጣልንንና ውል ያለውን ባህላዊ የቃል ታሪክ ሁሉ ቀረብ ብለን ስንመረምር፣ የወርቅ–ጉር ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ከግራኝ ዘመቻ በፊት የተመሠረተ ይመስላል።

የዚህ ጥንታዊ ምሥረታ ትዝታ በአካባቢው ሕዝብ ሥነ ቃል ማኅደር ውስጥ ከፍተኛ ቦታ እንደ ተሰጠው ግልጽ ሆኖ ይታያል። ብዙ የአገሩ አዛውንት አጠንክረው ከሚነግሩን ታሪክ ውስጥ፣ ከቤተ ክርስቲያኑ በላይ አሁን መንገድ ከተሠራበት ከፍ ብሎ ተንጠልጥሎ የሚታየው ገደል ከላይ በኩል አንድ ትልቅ ዋሻ እንዳለበት ሽማግሌዎቹ ይነግሩናል። በአፍላነታቸውም ዋሻውን በተደጋጋሚ መጐብኘታቸውንና ውስጡ ገብተው እንደ ተንጎራደዱበት በመንፈሳዊ ኵራት ያወሱን ብዙ ናቸው። «የዚህ ዓይነቱን ጀብዱ እኛም ሠርተናል» የሚሉም ወጣትነት ያላቸውም የአካባቢው ልጆች አልታጡም። ዋናው ቁም ነገር ግን በዋሻው ውስጥ አያሌ የጥንት ንዋየ ቅዱሳትና የተለያዩ ዕቃዎች ተቀብረውበታል እየተባለ ከጥንት ጀምሮ የሚነገር መሆኑ ነው። እንዲያውም እስካሁን ያልተደረሰባቸው የተከበሩ የሃይማኖት ዕቃዎች በውስጡ እንደሚኖሩና ጊዜው ሲደርስ የሚገለጡበት ዘመን ይመጣል የሚል ትንቢትም እንዳለ ከአገር አዛውንት አንደበት በተደጋጋሚ ይሰማል። በጣም የሚገርመው ደግሞ፣ ስለዚህ ዋሻና በውስጡ ይገኛሉ ተብለው ስለሚታመኑት ንዋየ ቅዱሳት የሚነግሩን ሁሉ፣ ታሪኩን የሚያወሱት በሹክሹክታ፣ በታላቅ መንፈሳዊ ፍራቻና ሁል ጊዜ ከጥንቱ የቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ምሥረታ ጋር በማያያዝ መሆኑ ነው።

የጥንቱ ቤተክርስቲያን የተቃጠለው በግራኝ ዘመቻ ጊዜ እንደ ነበረ ነው የሚነገረው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ግን፣ አፀደ ቤተክርስቲያኑ በአካባቢው ሕዝብ በጣም ተከብሮና ተፈርቶ እንደ ቆየና እምብዛም ሳይነካ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንደ ተላለፈ ይታመናል። ከአገሩ ተወላጆች መካከል ጠለቅ ያለ ዕውቀት የነበራቸውና ታሪክ የሚመራመሩ ሊቃውንት፣ የዚህን ስፍራ ጥንታዊነትና ልዩ ቅድስና እያሰቡ ለወደፊቱ እንደገና ተከብሮ የሚቋቋምበትን መንገድ ሲያዘጋጁ እንደ ቆዩ የሚያሳዩ ምልክቶች አሉ። ከነዚህ የአካባቢው ሊቃውንት መካከል የፈንጣጣ ዋሻ አቦው አለቃ ወልደ ሥሉስ ቤተሰብ በቀደምትነት የሚጠቀሱ ናቸው።

አለቃ ወልደ ሥሉስ ከመንዝ ወደ አካባቢው መጥተው ቀድሞ ተዳክመው የነበሩትን አብያተ ክርስቲያናት እንደ ገና እንዲጠናከሩ ካደረጉት ትላልቅ ሊቃውንት መካከል አንዱ እንደ ነበሩ ይነገርላቸዋል። እሳቸው የመጡት ከስድስት ትውልዶች በፊት፣ ምናልባት በ19ኛው ምዕት


www.ethiopianorthodox.org

ዓመት የመጀመሪያው አጋማሽ ውስጥ ሳይሆን አይቀርም። አለቃ ወልደ ሥሉስ የትምህርት ገባዔ መስጠት የጀመሩት ከወርቅ–ጉር አፀደ ቤተክርስቲያን ወረድ ብሎ በሚገኘው የራሱ የሆነ ቀደምትነት ባለው በፈንጣጣ ዋሻ አቦ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው። ይህም የፈንጣጣ ዋሻ አቦ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሌሎቹ የአካባቢው አብያተ ክርስቲያናት ከቦታ ወደ ቦታ የመዘዋወር ዕድል አጋጥሞታል። አሁን ወዳለበት ሥፍራ የመጣው በቅርብ ጊዜ፣ ባለፉት 40 ዓመታት ውስጥ እንደሆነ ሽማግሌቹ ያወሳሉ። አለቃ ወልደ ሥሉስ በመጡበት ዘመን ቤተክርስቲያኑ አሁን ካለበት ዝቅ ብሎ ከቁልቁለቱ በታች ነበር። ከሳቸውም ቀጥሎ ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው፣ እነአለቃ እንግዳ ወርቅ፣ አለቃ ተክሌና አለቃ ወርቅ አገኘሁ የእሳቸውን ፈለግ በመከተል ፈንጣጣ ዋሻ አቦ በአካባቢው የታወቀ የትምህርት ማዕከል ሆኖ እንዲቆይ ለማድረግ ችለዋል። የአለቃ ወርቅ አገኘሁ ልጅ ብላታ ደምሴ ደግሞ፣ እንደ አባታቸውና እንደ አያቶቻቸው የቤተክርስቲያን ትምህርት ባለሞያ ከመሆናቸውም በላይ፣ በጠቅላይ ቤተክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ በነበሩበት ጊዜ ምስጉን አስተዋፅኦ በማድረጋቸውና በከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ በመጨረሻም በጠቅላይ ፍርድ ቤት በምክትል አፈንጉሥነት ለብዙ ዓመታት የተከበረ አገልግሎት በማበርከታቸው፣ የወግዳና የፈንጣጣ ዋሻ አቦ ህልውና በብራዊም ደረጃ የበለጠ የታወቀ እንዲሆን አስችለዋል። ወንድማቸው አቶ መኮንን ወርቅ አገኘሁም እንደዚሁ በመጨረሻም፣ የወርቅ–ጉር ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን በዚህ ጥንታዊ አፀደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደገና እንዲተከል ለተደረገው የአገሩ ሕዝብ እንቅስቃሴ ተገቢውን አመራርና ግፊት የሰጡትም መምህር ወርቅ አገኘሁና ልጆቻቸው ብላታ ደምሴና አቶ መኮንን ናቸው።

አንዳንድ ሽማግሌች እንደ ነገሩን፣ ቤተክርስቲያኑ እዚህ ሥፍራ ላይ ከመተከሉ በፊት፣ ፈንጣጣ ዋሻ አቦ በደባልነት ይኖር የነበረውን የቅዱስ ገብርኤል ፅላት፣ በያመቱ ለታኅሣሥ ገብርኤል ዋዜማ ወደዚህ ጥንታዊ አፀደ ቤተክርስቲያን በክብር እያመጡ ድንኳን ውስጥ ሲጸለይበትና ሲዘመርበት ያድርና የአካባቢው ሕዝብ በብዛት በሚገኝበት በታኅሣሥ ገብርኤል ዕለት እዚሁ እያነገሡ ይመልሱት ነበር። ይህ ሥነ ሥርዓት ለብዙ ዓመታት ሲካሔድ መቆየቱን ሽማግሎቹ ይናገራሉ። የአካባቢው ሕዝብ በዚህ ዓይነት የሥፍራውን ጥንታዊ ቅድስና ለብዙ ዓመታት ሲያከብረው ከኖረ በኋላ ነው በ1955 ዓ.ም በጊዜው የሐረር ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በተገኙበት፣ የአለቃ ወርቅ አገኘሁ ልጆች ብላታ ደምሴና አቶ መኮንን ከቅርብ ወዳጅና ቤተሰብ ጋር በመረዳዳት በራሳቸው ወጭ አሠርተውት በነበረው መለስተኛ የቤተክርስቲያን ሕንፃ ውስጥ ተባርኮ በክብርና በድምቀት እንዲገባ የተደረገው

ይህ ከሆነ ዛሬ ልክ 37 ዓመት ሆኖታል። እነሆ ዛሬ ደግሞ በልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ፣ በቅዱስ ገብርኤል መልአክ አድኅኖ ዕርዳታ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ አገሮች በሚገኙ ብዙ የአካባቢው ተወላጆችና በሌሎችም ምዕመናን፣ የሕንፃ መሣሪያዎች፣ የገንዘብና የተለያዩ የንዋየ ቅድሳት አስተዋፅኦ፣ ከተቋቋመ 5 ዓመት የሆነው የቤተ ክርስቲያኑ ሥራና የልማት ድርጅት ዓቢይ ኮሚቴ ሳያቋርጥ በትጋት ሲሰጥ በቆየው ጠንካራ አመራር፣ በተለይም ደግሞ ምን ጊዜም ባልተለዩት የድርጅቱ የበላይ ጠባቂ በብፁዕ አባታችን በአቡነ ኤፍሬም የሰሜን ሸዋ ሊቀ ጳጳሳት ጸሎትና ቡራኬ፣ ይህንን ዘመናዊ ሕንፃ ለመሥራት ላስቻለው ለቸሩ አምላካችን ክብር ምስጋናችንን እያቀረብን፣ ይህንን ጥንታዊ የሃይማኖትና የባህል ሥፍራ እንደገና የአካባቢው ሕዝብ የተሟላ የትምህርት፣ የጤና፣ የልማት ሥራ ምክርና ዕርዳታ የሚያገኝበት ማዕከል ለማድረግ ያለውን ቆራጥ ዓላማ ለመፈጸም ብርታቱን እንዲሰጠው እንጸልያለን። ❑


ACPSERIC PLC.

HP COMPUTER PRODUCTS SUPPLIER
HP COMPUTERS AND PERIPHERALS
MAINTENANCE & SUPPORT PROVIDER
TRAINING & CONSULTANCY SERVICE




OUR ADDRESS
KASANTCHSE SUPERMARKET
4th Floor, Tel: 51 39 52/51 39 76,
Fax: 51 12 98 • E-mail: acpseric.plc@telecom.net.et
P.O. Box: 2764, Addis Ababa, Ethiopia




# የኢትዮጵያ ማንነትና ባህል

## በ16ኛው ክፍለ ዘመን የፖርቱጋል ውለታ

አርኪቴክት ግርማ ሞገስ (ለንደን)

ከጥቅምት 17 እስከ 22 ቀን 1992 ዓ.ም በፖርቱጋል በሚገኘው የአራቢዳ ገዳም አምስተኛው የኢትዮጵያ የኪነ ጥበብ ታሪክ ውይይት ተካሂዶ ነበር። አራቢዳ ከፖርቱጋል ዋና ከተማ ከሊዝበን (ፖርቱጋሎች ሊዝቦ ነው የሚሉት) ሠላሳ ኪሎ ሜትር በስተደቡብ አትላንቲክ ውቅያኖስ ዳርቻ የሚገኝ ሠላሳ አምስት ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው የተጠበቀ (reserved) የጋራ ሰንሰለት ነው።

ለውይይቱ የተመረጠው ገዳም አካባቢው በቁጥቋጦ የተሞላ፣ ከበስተጀርባው ከሚገኝ ዋና መንገድ ስምንት ኪሎ ሜትር የሚርቅ፣ ባሕር ዳርቻ ላይ የሚገኝ ቢሆንም፣ አምስት መቶ ሜትር ከፍታ ላይ የሚገኝ ነፋሻ ቦታ ነው።

ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ኪነ ጥበብ ታሪክ ውይይት የሚካሄደው በየሦስት ዓመቱ ነው። የመጀመሪያው እ.ኤ.አ ጥቅምት 1986 በለንደን ዩኒቨርሲቲ ዋርቡርግ ኢንስትትዩት ተካሄደ። የውይይቱን ሐሳብ ያመነጩትና የመጀመርያውም ለንደን እንዲሆን የወሰኑት በኢትዮጵያ ጥናት ላይ ረጅም ጊዜ ያሳለፉት ዶክተር ሪቻርድ ፓንክኸረስት ናቸው።

ዶክተር ሪቻርድ ፓንክኸረስት ውይይቱን ለመጥራት ምክንያት የሆናቸው ለ90ኛው ዓመት የአድዋ ድል መታሰቢያ በዓል ያዘጋጁትና ውይይቱን ከመጥራታቸው ሰባት ወራት በፊት ያደረጉት ንግግር እንደሆነ ገልጸዋል። ያቀረቡትም ንግግር በኢትዮጵያውያን አርቲስቶች በተሣሉ ሥዕሎች የተደገፈ እንደ ነበር ባንድ ጽሑፍ ተጠቅሷል። በንግግራቸው መግቢያ ላይ በቅድመ አድዋ አፍሪካን ለመከፋፈል ይሽቀዳደሙ የነበሩት ቅኝ ገዥዎች ስለ ኢትዮጵያ የነበራቸው አስተያየት ከጊዜ ጋር እንዴት ይለዋወጥ እንደ ነበር ሲያስረዱ የሚከተለውን ጠቅሰዋል:-

> «...መቅደላ ላይ በእንግሊዞች ከተገኘው ውጤት በኋላ ‹ኢትዮጵያን በቀላሉ ለመያዝ ይቻላል› የሚል አስተሳሰብ በቅኝ ገዥዎች ሰፈር ተቀባይነትን አገኘ። ይህም ብዙዎቹን አቋመጣቸው። ይሁንና አፄ ዮሐንስ በተደጋጋሚ መጀመሪያ ግብፆችን፣ በመቀጠልም ግብፆችን በመጨረሻም ደርቡሾችን አሸነፉ። በነዚህ ድሎች የኢትዮጵያ ነፃነት ተጠበቀ። የቅኝ ገዥዎችን እምነት የሰበረው ግን የአድዋ ድል ነበር። ከአድዋ ድል በኋላ አንድ ጣሊያናዊ፣ ‹ሐበሻን ማሸነፍ የሚባል ነገር የት ተሰምቶ ይታወቃል?› በማለት እስኪተች ድረስ የአስተሳሰብ ለውጥ ተፈጠረ...።»

በንግግሩ ሁለተኛ ክፍል ከአድዋ በኋላ በኢትዮጵያውያን አርቲስቶች ስለ አድዋ ጦርነት የተሣሉትን ሥዕሎች በስላይድ በተከታታይ እያሳዩ፣ «ታሪክ ባለፈ ድርጊት ላይ አሁንታ የሚያሳርፈው ነጸብራቅ ነው» "History is a projection of the present on the past" በማለት ተናግረው ነበር። ይህ ብሂል ለትዕይንት በቀረቡት ሥዕሎቹ ላይ ተንጸባርቆ ነበር። ለምሳሌ፣ ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የተሣሉት ሥዕሎች በአድዋ ጊዜ ያልነበሩትን እንደ መትረየስ የመሳሰሉ መሣሪያዎችን ያሳያሉ። ከአርበኝነት ዘመን በኋላ የተሣሉት ደግሞ በአድዋ ጦር ሜዳ ላይ የተዋጋውን የጠላት ጦር በግንብ ምሽግ ውስጥ ሆኖ እንደሚከላከል አድርገው ያሳያሉ። ለአንደኛው ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ኪነ ጥበብ ታሪክ ውይይት ያቀረቡት በዚህ መልክ ነበር።

በኢትዮጵያ ኪነ ጥበብ በተለይም በሥነ ሥዕል ምሁርነትና ተቺነት የታወቁት ፕሮፌሰር ቾይናስኪም ከመጀመሪያው ጀምሮ በየውይይቱ ልዩ ተሳትፎ በማድረግ ተባብረዋቸዋል። ይህ ትብብርም አምስተኛውን ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ኪነ ጥበብ ውይይት ጨምሯል።

ሁለተኛው ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ኪነ ጥበብ ታሪክ ውይይት በፖላንድ ብሔራዊ ሙዚየም ተቀነባብሮ በመስከረም 1990 (እ.አ.አ) ኒየቦሮው ቤተ መንግሥት (ፖላንድ)፤

ሦስተኛው በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ጥናት ኢኒስትትዩት ተቀነባብሮ በመስከረም 1993 (እ.አ.አ) አዲስ አበባ፤

አራተኛው በትሪየስቴ ከተማ ማዘጋጃ ቤት አቀናባሪነት በመስከረም 1996 (እ.አ.አ) ትሪየስቴ ሙዚየም ጣሊያን ተደርገዋል።



www.ethiopianorthodox.org

በመጀመሪያና በሁለተኛ የቀረቡት ጥናቶች ብዙዎቹ የኢትዮጵያን ባህል፡ በተለይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስትያን ቅርሶችን መርምረዋል። ለምሳሌ፡ «የኢትዮጵያ ኪነ ጥበብ ገጽታዎች» (Aspects of Ethiopian Art/1993) በሚል አርዕስት ከታተሙትና ኒየቦሮው ከቀረቡት አሥራ ሰባት ጥናቶች አሥራ ሁለቱ የቤተክር ስትያንን ቅርፅና ሥነ ሥዕላዊ ይዘት ከልዩ ልዩ አቅጣጫ ተመልክተዋል።



የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን (ሶቲቡል)

Igreja de Jesus (Setibul)

አምስተኛው ውይይት እላይ እንደ ተገለጸው በአራቢዳ ገዳም የተካሄደ ሲሆን፡ ውይይቱ በ16ኛው ክፍለ ዘመን ፖርቹ ጋሎች ከአውሮፓ አገሮች በቀደ ምትነት ለአፍሪካ፡ እሲያና አሜ ሪካ የባሕር ንግድ መሥመር የዘረ ጋችበትና ሌሎችም ታሪካዊ ሁኔ ታዎችን ያከናወኑችበትም ወቅት እንደ ነበር ተወስቶአል።

የኢትዮጵያ ማንነት፡ የኅብረ ተሰቧ ትስስርና የቤተክርስቲያኗ ህልውና በአጭሩም ሆነ በሰፊው ሲወሳ፡ በጣም አደገኛ ሁኔታ ላይ ነበር ተብሎ የሚገመተው በ16 ኛው ክፍለ ዘመን ሲሆን፡ ይህም ግራኝ አሕመድ ያደረሰውን እልቂትና ውድመት በማሰብ ነው። በዚህም በኩል በኢትዮጵያውያን ልክ እንደ ተአምር በተደጋጋሚ የሚነሣው ይህንኑ አደጋ ለመቋቋምና ለማስወገድ የፖርቹጋል ወታደሮች የፈጸሙት ወቅታዊና ታሪካዊ ጀብዱ ነው።

ለምሳሌ፡ ታኅሣሥ 19 ቀን 1989 ዓ.ም በታተመው «መልዓከ አድኅኖ» መጽሔት፡ መርቆሬዎስ ሕይወት «ኢትዮጵያ» በሚል አርዕስት በአቀረቡት ጽሑፍ የሚከተለውን አስፍረዋል:-

> «በግራኝ ወረራ ጊዜ ጦር ተፈትቶ፡ ሕዝብና መሪ ሸሽቶ፡ ተስፋ መቍረጥ በሰፈነበት ጊዜ ማንም ሰው ሊገምት በማይችለው ሁኔታ አገሪቱ በአጠቃላይ ወደ እስልምና ለመለወጥ የተቃረበችበት ሁኔታ ነበር። ነገር ግን የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ በዚያን ጊዜ ከመገናኛ አንጻር እጅግ ሩቅ ከሚባል አገር ፖርቹጋል በጣም ጥቂት ወታደሮች ልኮ ለማመን በሚያዳግት መልክ ሁኔታዎችን በመለወጥ ያንን የተሸነፈ ሕዝብና መሪ እንደገና በማጽናናት ቀድሞ የነበረውን እምነትና ነፃነት እንዳይጠፋ አድርጓል።»

«መልዓከ አድኅኖ» ከ472 ዓመታት በፊት ግራኝ አሕመድ ካወደማቸው አብያተክርስቲያን አንዱ የሆነው የወርቅ ጉር ቅዱስ ገብርኤል ነው። የወርቅ ጉር ቅዱስ ገብርኤል በሰሜን ሸዋ በተጉለት ወረዳ ይገኛል።

በመጀመሪያ የተተከለው በ14ኛው ምዕተ ዓመት በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ነው። የቅዱስ ሲኖዶስ አባልና የሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም በዚሁ መጽሔት መግቢያ ላይ ቤተክርስቲያኑ በግራኝ ወረራ ተደምስሶ ከቆየ በኋላ ቅዱስ ገብርኤልን በሚወዱ በክቡር ብላታ ደምሴ ወርቅ አገኘሁና ወንድሞቻቸው አማካኝነት አሁን የሚገኘውን ቤተክር ስቲያን አሠርተው ሚያዚያ 19 ቀን 1955 ዓ.ም ታቦቱ ወደ መቅደሱ መግባቱን አስረድተዋል።

በዚሁ መጽሔት ባላንበራስ የሺ ጌታ መኩሪያ ባቀረቡት ጽሑፍ የምረቃውን ሥርዓተ ጸሎትና ቅዳሴ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ መምራታቸውን፡ አለቃ ወርቅ አገኘሁ ተክሌ ደግሞ የወርቅ ጉር ቅዱስ ገብርኤልን ቅዱስ ቦታነት ለማብሠር «ደብረ አድኅኖ» ተብሎ እንዲሠየም ማድረጋቸውን ጠቅሰዋል። አጠቃ ላይ አስተያየት በመሰንዘርም የሚከተለውን አስነብበዋል፤

> «የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስ ቲያን ሃይማኖት ለእንግዳ ተመልካች የቀዘቀዘች መስላ ብትታይም፡ እንደ ፍም እሳት ሲገልጧት ሙቀት ሳይለያት ሳትጠፋ የምትኖር መሆኗ በዚህ ጥንታዊና ታሪኩ በሚነገርለት መንፈሳዊ ቦታ በተደረገው አሁንም በመደረግ ላይ ባለው መረዳት የሚቻል ነው። ወደፊትም በምዕመናን ጽናት እንደሚቀጥል አያጠ ራጥርም።»

ከላይ የተጠቀሰውና የሚከተሉት ሁኔታዎች እንደሚ ጠቁሙት፡ በ1950 ዓ.ም አካባቢ የኢትዮጵያ ባህልና እምነት መጠበቅ ለወጣቱ ትውልድ በአዲስ መልክ መነገር እንዳለበት በቤተክርስትያን አባቶች በኩል ጥረት የተደረገበት፡ አንዳንድ ምዕመናንም ይህንኑ በተግባር ለመተርጐም ልዩ ሙከራ ያደርጉ የነበረበት ጊዜ ይመስላል። ለምሳሌ፡ ባህልን መጠበቅና ማክበር ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ በወቅቱ የሐረር ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ለጀነራል ዊንጌት ተማሪዎች የግራኝን ዘመን በመጥቀስ የተናገሩትን አንድ ተማሪ በማስታወሻው እንደሚከተለው መዝግቦት ነበር፤

> «...አሁን እስካለንበት ዘመን (1952 ዓ.ም) የአብዛኛው የኢትዮጵያውያን ሃይማኖታዊ እምነት ኦርቶዶክስ ሲሆን በ1520 (እ.እ.አ) እስልምና ጣልቃ በመግባት በግራኝ አሕመድ አዝማችነት በተቀደሰችው ደሴት በኢትዮጵያ ድንበርና ዙሪያ የሚገኙትን ክርስትያን ሕዝቦች በማስፈራራትና በማሠቃየት የእስልምና ሃይማኖት አሳድረውባቸዋል...»



ስለ ሁለቱ ሃይማኖቶች የገለጹት ዝርዝር ጥናት የሚጠይቅ ነው። ሆኖም ኢትዮጵያ ክርስትናን በፈቃዷ እንዳ ተቀበለችና ከቅድመ ክርስትና ባህሏ ጋር አመቻችታ እንዳዋሐደችው ሁሉ የእስልምና እምነት ያላቸው አረቦች አገራቸው ችግር ላይ ወድቀው በተደጋጋሚ ሂጅራ (Hijra) በተሰደዱበት ጊዜ ኢትዮጵያ መጠለያቸው እንደ ነበረች፡ ከዚያም በላይ ቁረይሽ (Quraysh) አሳዳጆቻቸው ብዙ ስጦታ ለኢትዮጵያ ንጉሥ በማበርከት የነብዩ መሐመድን ተከታዮች አሳልፈው እንዲሰጡ ቢጠየቁም፡ ኢትዮጵያውያን ግን አሳልፈው አለመስጠታቸው በታሪክ የተመዘገበ እውነታ ነው። የእስልምና እምነት ተከታይ አረቦች ሃይማኖታቸውን ኢትዮጵያ ውስጥ ሲከታተሉ ምናልባትም ሲሰብኩ ኖረው ለመጀመሪያ ጊዜ በሰላም ወደ አገራቸው ለመመለስ የቻሉት በ628 ዓ.ም ነው።

ወደ አለንበት ዘመን ስንመለስ፡ ቅዱስ ቁርአን ለብዙኃኑ ኢትዮጵያውያን ሊደርስ የሚችለው ከአረብኛ ይልቅ በአገሩ ቋንቋ ቢሆን ይሻላል በማለት ወደ አማርኛ ተተርጕሟል። በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች እስላሞች የሚያከብሩትን፡ እስላሞች ክርስቲያኖች የሚያከብሩትን በዓል በአንድ ላይ ወይም በተመሳሳይ ሁኔታ ሲያከብሩ ይታያል። ለምሳሌ፡ አስትሮ ማሪያም ወሎ ውስጥ፡ ቁልቢ ገብርኤል በሐረር በሁለቱም ሃይማኖት ተከታዮች ይከበራሉ። ሚያዚያ 30 ቀን 1955 ዓ.ም የታተመ «ዜና ቤተ ክርስቲያን» የሚል መጽሔት፡ የወርቅ ጉርን መመሥረት ለማብሠር ባቀረበው የፎቶግራፍ መግለጫ ላይ፡ «ፊታውራሪ ኢብራሒም ሐሚድ ከሌሎች መኳንንቶች ጋር በሥነ በዓሉ ላይ ይታያሉ» ይላል። እነዚህ ሁኔታዎች በከፊል የኢትዮጵያ ባህል የምንለውን ይገልጻሉ ብለን መገመት ይቻላል።

ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያን ህልውናና ባህል ለመጠበቅ ለ16 ዓመታት ስለ ተካሄደው ትግል በመጨረሻም የፖርቹጋል ወታደሮች ያበረከቱትን ሚና በማሰብ ለተማሪዎች ያደረጉት ንግግር ላይ የሚከተለው ይጠቀሳል፤

> «ኢትዮጵያውያን የጠላትን ቀንበር መሸከም መከራ መሆኑን ከማወቅ በላይ በጠላት መያዝና ሌላ ሃይማኖት መውረስ ከትልቅ ውርደት ቈጥረውት ከግራኝ ጋር ብዙ ትግል ካደረጉ በኋላ የጠላታቸው ኃይል እየበረታ መሄዱን ባወቁ ጊዜ ከአውሮፓ መንግሥታት በተለይም ከፖርቹጋል ተጻጽፈው ዕርዳታን በማግኘት ጠላታቸውን ድል መትተዋል...።»

ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ግንቦት 13 ቀን 1952 ዓ.ም ከተናገሩት ምን ያህሉን ተማሪዎቹ እንደ ተገነዘቡት መገመት አስቸጋሪ ነው። ግን ያው ተማሪ መዝገቡ ላይ ከሦስት ወራት በኋላ ያሰፈረውና ስለ ፖርቹጋሎች ሚና ለማወቅ የተነሣሣው ምናልባት ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ የተናገሩትን በማዳመጡ ነው ብሎ መገመት ይቻላል። በአራት ማዕዘን [ ] ቅንፍ ከተደረገው ሌላ የሚከተለው ተማሪው ካሰፈረው የተወሰደ ነው። ከ40 ዓመታት በፊት የተማሪዎች አመለካከት ምን ይመስል ነበር የሚለውንም ጥያቄ ለማንሣት እንዲረዳ ከሞላ ጎደል እንዳለ ቀርቧል።

> «ዓርብ ነሐሴ 20 ቀን 1952 ዓ.ም
>
> የፖርቹጋል ጀግንነት የሚለውን መጽሐፍ አንብቤአለሁ። ...የዚህ መጽሐፍ ታሪክ ከልክ ያለፈ ስላስደሰተኝ ከዚህ ጋር የሚወዳደር በአማርኛ የተጻፈ የታሪክ መጽሐፍ የለም እስከማለት ደርሻለሁ።
>
> በተለይም የክርስቶፍ ዳ ጋማ [Christopher da Gama] ጀግንነት በ25 ዓመት ወጣት የኢትዮጵያን ታሪክና የወደፊት መልኳን የሚለውጥ ሥራ መሥራቱ በማንም የማይካድ ነው። በተለይም አንድ ሰው ከ10 ሰው ጋር ተዋግቶ እንኳን ለማሸነፍ ለመትረፍ ያለው ተስፋ በፍጹም የማይታሰብ ሲሆን፡ ክርስቶፍ ዳ ጋማ የራሱን ወታደሮችና ኢትዮጵያውያኖችን፡ ከ1500 ፈረሰኛና ከ5000 እግረኛ ጋር ግጥሚያ ለማድረግ ማሰቡ የሚያስገርም ነው። «የሰው ጠባይና አብሮ የመኖር ዘዴ» በሚለው በአቶ ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ መጽሐፍ እንደ ተገለጸው ሁሉ፡ የክርስቶፍ ቆራጥነት በማንም የሚደነቅ ነው። ነገር ግን በመጨረሻ እንደዚያ ያለ ሥቃይ ሲደርስበት መንፈስ ያናውጣል።...»

በማለት በ1543 ዓ.ም ስለ ተደረገው ተጋድሎና በመሥዋዕትነት ስለ ተገኘው ድል ሐሳቡን ያጠቃልላል።

ተማሪው ያልገለጸው፡ ምናልባትም የማያውቀው ነገር ቢኖር፣ ክርስቶፍ ዳ ጋማ የቫስኮ ዳጋማ (Vasco da Gama) ልጅ መሆኑን ነው። ቫስኮ ዳ ጋማ ለሀገሩ ለፖርቹጋል ቀደምትነትን በማጎናጸፍ በደቡብ አፍሪካ በኩል ያለውን የባሕር መንገድ አግኝቶ ህንድ መጀመሪያ የደረሰው፡ የምሥራቅን ዓለም ለምዕራባውያን ያስተዋወቀው በ1461 ተወልዶ በ1516 ያረፈው ሁሌም የሚወደስ ዓለም አቀፍ ጀግና ነው።

በ16ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ ፖርቹጋል በሥነ ጥበብም የሚታወቁ ምሁራን ነበሯት። ለምሳሌ ፍራንሲስኮ ደ ሆላንዳ (Fransisco de Holanda) የተባለው የሚካላንገሎ (Michelagelo) ጓደኛ የነበረ ስለ ሥነ ሥዕል በዓለም የመጀመሪያውን በሬንሳንስ (Rennaisance) ዘመን ብቸኛውን መጽሐፍ (Do tirar pelo natural 1549) አቀነባብሮ የጻፈ ነው። ሳንቸዝ ኮኤሎና (Sanchez Coelo 1531-88) ሲልቫ ቬላስክዌዝ (Silva Velazquez 1599-1660) የተባሉት በዓለም የታወቁ ሠዓሊዎች የፖርቹጋል ዘር አላቸው።

በሕንፃ (architecture) ሥራም እንዲሁ በማኑኤል አንደኛው ዘመነ መንግሥት (Manuel I 1495-1521) ያበቡት ስልቶች እስካለንበት ዘመን ማኑኤላዊ (Manueline Style) በመባል በዓለም አቀፍ ደረጃ ይታወቃሉ። በ1494 የማኖኤላዊን ስልት የጀመረው ዲዖጎ ቦይታክ (Diogo Boitac) የተባለው አርኪቴክት ይህንኑ ስልት መጀመሪያ በሥራ ላይ ያዋለው የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን (Igreja de Jesus በተባለው ነው። እንደ አጋጣሚ ሆኖ ቤተክርስቲያኑ አራቢዳ አጠገብ በሚገኝ ሶቲቡል (Setibul) በተባለ ከተማ ይገኛል። ማኑኤላዊ የሆኑት ስልቶች ልዩ መታወቂያ ከድንጋይ የተሠሩ እንደ ገመድ ሦስት ጥንድ ሆነው የተደራረቡና የተጠማዘዙ ምሰሶዎችና የሕንፃው አካሎች (columns/ribs/corbels) ናቸው።



www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ከላይ የተጠቀሰውን ኢትዮጵያውያን «...ከግራኝ ጋር ትግል ካደረጉ በኋላ የጠላታቸው ኃይል እየበረታ መሄዱን ባወቁ ጊዜ...» ብለው ስለ ኃይል ሚዛን ሁኔታ በደፈናው ተናግረዋል። በቅርብ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ያ በየቦታው ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙት የቅድመ ታሪክ ቅርስ የሆኑ ድንጋዮች «ፈረሱን ለማሠር የተከለው ነው» የጦር ችሎታውን ሲተቹ ደግሞ «ዛፉን በሩቅ ይገነድስ ነበር» እየተባለ በአፈ ታሪክ የሚነገርለት ግራኝ (አሕመድ ኢብን ኢብራሒም) ታሪካዊ ኃይሉ በከፊል ከኦቶማን ኢምፓዬር (Ottoman Empire) ሱሊማን አንደኛው (Suleiman I 1520-66) የተላከለት የዘመኑን ጠመንጃና መድፍ የያዙ ወታደሮች ዕርዳታ መሆኑን ያስረዳሉ።

እነዚህ ጥናቶች ጂሃድንና ዝርፊያን መመሪያው በማድረግ ምሥራቅ አውሮፓን ከ1307 እስከ 1683 ለመቆጣጠር የቻለው የኦቶማን ኢምፓዬር የኢትዮጵያን ዳርቻ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ቢዳስስም ማንነትዋን ለማጥፋት፣ ለመለወጥ ወይም ለመቆጣጠር ያልቻለው ከኢትዮጵያ አይበገሬነት (military impregnability) ሌላ መሠረታዊ ምክንያት እንዳለ ይጠቁማል።

ኢትዮጵያን ለማቆየት ምክንያት የሆኑት በአንድ በኩል የኢትዮጵያ ቤተክርስትያን ከንጉሠ ነገሥት ሥርዓት ጋር በመደጋገፍ የነበራቸው ሕዝብን የማዋሐድ ማዕከላዊ ሚና፣ በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአመዛኙ በንግድ ሳይሆን በገባር ይዞታ ተመሥርቶ ውትድርናን ያጣመረ ግብርና ስለነበር ነው በማለት "Survival and Modernization" (1999) በተባለው መጽሐፋቸው መሳይ ከበደ ያስረዳሉ። የመጽሐፉ መሠረታዊ ዕንስ ሐሳብ፣ ከባህል ጋር ካልተቀነባበረ የህልውናና የዕድገት ነገር አይታሰብም የሚል ነው።

ተማሪው «የኢትዮጵያን ታሪክና የወደፊት መልኳን የሚለውጥ ሥራ» ብሎ ላጠቃለለውና ብዙ ምሁራን ወሳኝነቱን ለሚቀበሉት የፖርቹጋሎች ሚና የመሳይ ከበደ አመለካከት እንደሚከተለው ይገለጻል፤

> «የግራኝ ኃይል ቱርኮች ካቀበሉት ጠብመንጃና መድፍ የመነጨ ነው። የፖርቹጋሎች መምጣት የዚያን አዲስ መሣሪያ ምስጢር እርቃኑን አስቀረው።
>
> የነሱን ዕርዳታ ከዚህ የሞራል ድጋፍ በላይ አድርጎ መገመት ከነበረው ሐቅ ጋር አይጣጣምም። ወደ እውነቱ የሚጠጋው የፖርቹጋሎች መምጣት ኢትዮጵያውያን እንደገና እንዲደራጁ ፋታ ማግኘታቸውን የምቀበለው ነው።»

በ1540 ኢትዮጵያ የመጡት 400 ፖርቹጋሎች ቍጥራቸው አነስተኛ በመሆኑ የንጉሠ ነገሥቱ የአፄ ገላውዴዎስን ሠራዊት ለድል ያበቁት ለግራኝ ዓይነታዊ ምላሽ ለመስጠት በመቻላቸው ሳይሆን፣ ጠመንጃ መያዛቸው ያስከተለው የሞራል እምርታ ነው ማለት ይቻላል።

በጠመንጃ አጠቃቀም ፖርቹጋል ቀደምት ከሚባሉት አገር ነች። በተለይ ከስፓኝ (Spain) ጋር ተባባሪም ተወዳዳሪም ስለነበሩ፣ የፖርቹጋል ወታደሮች ኢትዮጵያ በመጡበት ወቅት አርከቡስ (arquebus) በተባለው እ.አ.አ በ1450 በስፔን ሥራ ላይ የዋለውን የመጀመሪያውን የዘመናችን ጠብመንጃ የሚመስል መሣሪያ ተጠቅመው ሊሆን ይችላል። ይህ መሣሪያ በ1503 ስፓኝ ለመጀመሪያ ጊዜ ተጠቅማበት ፈረንሳይን ሴሪኞላ (Cerignola) በተባለ ጣሊያን አገር በሚገኝ ቦታ አሸንፋታለች። የሮማው ጳጳስ የክርስቲያኑን ዓለም ለሁለት ከፍለው አንዱ ስፓኝ ሌላውን ፖርቹጋል ከተቀናቃኝ ኃይሎች እንዲጠብቁ ኃላፊነት ሰጥተው ነበር። ክርስቲያን ፖርቹጋል ክርስቲያን ኢትዮጵያን ለመደገፍ የበቃው በዚያ ምክንያት ሲሆን፣ በንግድም በኩል ጥብቅ ግንኙነት እንደ ነበራቸው የሚገልጹ ማስረጃዎች አሉ። ለምሳሌ፣ የማኑኤል አንደኛው ረጅም የማዕርግ ስም ከኢትዮጵያ፣ ከአረቢያ፣ ከፔርሲያና ከህንድ ጋር የንግድ ግንኙነት እንዳለ የሚያስረዳ ሲሆን፣ በተቀናቃኞች በተለይም በፈረንሳይ ንጉሥ ለማኑኤል አንደኛው የሰጡት «የቅመማ ቅመም ንጉሥ» የሚለው የማጥላሊያ ስም ዋናው የንግዱ ዓይነት ምን እንደ ነበረ የሚጠቁም ነው።

አራቢዳ ከቀረቡት ሃያ አራት ጥናቶች አሥራ ሦስቱ በ16ኛው እና በ17ኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያንና የፖርቹጋልን ግንኙነት ውጤት የመረመሩ ናቸው። ከሃያ አራቱ ጥናቶቹ ውስጥ ሰባቱ በኢትዮጵያውያን ቀርበዋል። ከነሱም አንዱ የወርቅ ጉር ቅዱስ ገብርኤልን ከታሪክ፣ ከቅድመ ታሪክ፣ ከቅርስና ከሥነ ጥበብ አንፃር መርምሯል። ❑


አስሚ ኢንዱስትሪ ኃ.የተ.የግ.ማ.
የሕክምና ፋሻና የፀረ ብክለት አምራች
ASMI INDUSTRY PLC.
Surgical Dressing Material And Disinfectant Producers

Life care products...
Life Bandage
Life Elastic Bandage
Life Gauze Swab
Life Gauze
Life First Aid Bandage
Life Triangular Bandage
Lifetol Antiseptic-Disinfectant

ASMI INDUSTRY PLC.
☏ 712994/93
Fax 251-1-517453
✉ 2403
Addis Ababa
Ethiopia





GAKY Engineering & Automotive P.L.Co.

የሆንዳ ሲ. አር. ቪ. መኪና ከከተማ ወጣ ብለው ታሪካዊ ሥፍራዎችን፤ እንዲሁም የእምነትና የመዝናኛ ቦታዎችን ለመጎብኘት ይችሉ ዘንድ በገጠሩ አስቸጋሪ መንገድ ላይ በአስተማማኝነት በመጓዝ ፍላጎትዎን የሚያሳካልዎት ምቹና ዘመናዊ የፎር ዊል ድራይቭ መኪና ነው።

CR-V



በተጨማሪም የሆንዳ ጀኔሬተሮች ኤሌክትሪክ በማይደርስበት የገጠሩ ክፍል በሚገኙ ታሪካዊ እና የእምነት ቦታዎች ላይ በብቃትና በአስተማማኝነት የኤሌክትሪክ ኃይል በመስጠትና በረጅም ጊዜ አገልግሎታቸው የታወቁ ስመ ጥር ጀኔሬተሮች ናቸው።




ብቸኛ አስመጪ፤ ጋኪ ኢንጂነሪንግና አቶሞቲቭ ኃ.የተ. የግል ኩባንያ

ለማንኛውም መረጃ በሚከተለው አድራሻ ይጠይቁን፤
ስልክ 654000 / 653761 ፤ ፋክስ 653763
e-Mail: gaky@telecom.net.et ፤ ፖ.ሣ.ቁ. 8524፤ አዲስ አበባ




www.ethiopianorthodox.org

**Add Col ur to Your Work**

With XEROX

- Xerox Col ur printing
- Xerox Col ur copying
- Xerox Col ur scanning
- Xerox Fax machines

DIGITAL
The Document Company
XEROX

M&M TRANS-AFRICA TRADING PLC.
ኤም እና ኤም ትራንስ አፍሪካ ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ.
Tel: 51 04 33/51 59 73/ 51 05 88 / 51 27 35
Fax: 51 55 06 P.O. Box 21331, Addis Ababa

**አንጋፋው እውቁና በጥራቱ ተወዳዳሪ የሌለው**
**ስታር ቴክኒካል ትሬዲንግ ኃ.የተ. የግል ኩባንያ**
**ዋንዛ የእንጨት ሥራ ፋብሪካ**

- የውስጥና የውጪ በሮችን
- ጠቅለላ የቤትና የቢሮ እቃዎችን
- ኪችን ካቢኔቶችና ቁምሳጥኖች
- የቤት ግንባታ አጨራረስ ጌጦችን
- የእንጨት ቤቶችንና ክፍሎችን

አድራሻችን፡
አዲስ አበባ፡
ወ. 22 ቀ. 04
ስልክ 157995
159925
ፖ.ሳ.ቁ. 3419
አዋሳ፡
ስልክ፡ 06-200626



ከብረት የተሰሩ፡
- በሮች - መስኮቶች - የበረንዳ ግሪሎችንና አልጋዎችን በተጨማሪ በእንጨት ተባይ መከላከያ ኬሚካል የተቀቀሉ

- ለአጥር - ለስልክ - ለድልድይና ለተለያዩ ኮንስትራክሽን አገልግሎት የሚውሉ እንጨቶችን በምትፈልጉት አይነት መጥን ጥራትና ጊዜ እናመርታለን።

በምርቶቻችን ጥራት ከልብ ይረካሉ




# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስትያን
## ለአገሪቱ ሕግ ቀረፃና ልማት ያደረገችው አስተዋፅኦ
(ፍትሐ ነገሥትን መነሻ በማድረግ የቀረበ)

አበበ ወርቁ

1

«በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!!» ብለን የምንጀምረው ያለ ምክንያት አይደለም። በእግዚአብሔር በመመካት የተጀመረ ሁሉ መልካም ፍጻሜ ይኖረዋል ብለን ስለምናምን ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ለአገሪቱ ሕግ ቀረፃና ልማት ያደረገችውን አስተዋፅኦ ፍትሐ ነገሥትን መነሻ በማድረግ እጅግ በጣም አጭር በሆነ መልኩ እንደሚከተለው አቅርቤአለሁ። ለጽሑፉ መነሻ ይሆን ዘንድ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት፡ ፍትሐ ነገሥትን እንዲታተም ባደረጉበት በ1958 ዓ.ም ከሰጡት ንጉሣዊ ቃል የሚከተለውን በመጥቀስ ነው፤

> «...የኢትዮጵያ ሕዝብ (አንድ) መንግሥት ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ከሕግና ከፍርድ ውጭ የሆነበት ጊዜ ከቶ የለም። እንዲያውም አገዛዙ መንፈሳዊ እንደ መሆኑ መጠን በመጀመሪያ በኦሪታዊ ሕግ ሲተዳደር የሙሴንም ሕግ ሲጠብቅ ኖረ። በኋላም በሥጋዊ ጊዜ ሕገ ኦሪትንና ሕገ ወንጌልን በማገናዘብ ሲሠራበት ቆየ። እንደዚሁም እየዋለ እያደረ መንግሥት ለሥጋዊ ፍርድ የወንጀለኛ መቅጫ ስላስፈለገው ቤተ ክርስቲያንም በበኩልዋ መንፈሳዊ ወንጀል የሠራውን የምትቀጣበት መንፈሳዊ ሕግ ስለ አስፈለጋት ከብሉይና ከሐዲስ ኪዳን የተውጣጣ ፈውስ መንፈሳዊ እና ፍትሐ ነገሥት የተባሉ የሕግ መጻሕፍት እንዲዘጋጁ ሆነ።»

ግርማዊነታቸው ቤተ ክርስቲያንን ከፍትሐ ነገሥት ጋር በማዛመድ የጠቀሱት፡ ፍትሐ ነገሥት ስሙ እንደሚያመለክተው (The Law of the Kings) የንጉሦቹ ሕግ ይሁን እንጂ ወደ ሕዝቡ የወረደ፤ ሕዝቡ ተረድቶት አክብሮት እንዲኖር የሠረፀ ሳይሆን በቤተ መንግሥት አካባቢ ብቻ ታውቆ በጥቂቶች ምሁራን እየተተረጐመ ከሥራ ላይ እንዲውል የሚደረግ ነበር እንጂ፡ ሕዝቡ የሚያውቀው አልነበረም። ምሁራን የሚባሉትም በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የነበሩ፤ የቀለም ትምህርት ገብቷቸው መጻሕፍትን አንብበውና ተረድተው ከመምህርነት ዓለም ተራምደው በመጻሕፍት የላቀ ዕውቀት ያላቸውን ነበር።

ከእነዚህም ውስጥ በጣም የላቁት «ሊቅ» የሚባል ማዕርግ እየተሰጣቸው በፍትሐ ነገሥት ትርጓሜያቸው የታወቁና የተከበሩ ሊቃውንት ይገኙባቸዋል። እነኚህ የቤተክርስቲያን ሰዎች በቤተ መንግሥት አካባቢ እየተገኙ ፍትሐ ነገሥቱን በመተርጐም፤ ፍትሕ አንድ ወጥ መልክ እየያዘ እንዲሄድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

ፍትሐ ነገሥትን መለስ ብለን በመጠኑ ብናይ፤ ለዝግጅቱ መነሻ ተደርጎ የተወሰደው የብሉይ እና የሐዲስ ኪዳን፤ የሌሎች (Appostolic Orgin) ጸሐፊዎች እንዲሁም 318ቱ አባቶች በኒቂያ ጉባኤ (325) ከሰበሰቧቸው ሕጎች ተውጣጥቶ ፍትሐ ነገሥት በቀደምት አባቶች፤ የቤተ ክርስቲያን ምሁራንና በቤተ መንግሥት አካባቢ ሰዎች እጅግ ከፍተኛ አክብሮት የተሰጠው በመሆኑ በቤተ መንግሥት የሚሠራበትና ቤተ ክርስቲያንም የምታስተምርበት ሕግ ሆኖ ቆይቷል።

ፍትሐ ነገሥት ወደ ኢትዮጵያ የገባበት ወቅት በትክክል ባይታወቅም፤ ሲወርድ ሲዋረድ እምነቱ እንደ ሚያስረዳው፤ በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን (1427–1460) ወደ ኢትዮጵያ እንደገባ ይተረካል። አፄ ዘርዐ ያዕቆብ ያለንበት ዘመን የአዲስ ኪዳን ዘመን ቢሆንም፤ ሕዝቤ የሚተዳደረው በኦሪትና በብሉይ ኪዳን ነው እያሉ በጣም ያዝኑ ስለነበረ፤ ወዳጃቸው የሆነ አንድ የግብፅ ሰው በዘመኑ የንጉሣውያን ሕግ እየተባለ የሚጠራውን ፍትሐ ነገሥት አንሥቶ ስለ አጻጻፉ፤ ስለ ወጥነቱ፤ ስለ ፍትሐዊነቱ ስለ ነገራቸውና ወደ ኢትዮጵያም ለማስመጣት እንደሚቻል ስላወጋቸው ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ ያስደረጉት በዚያን ጊዜ ነው ይባላል። በመሆኑም ግብፃዊው ወዳጃቸው ይህን መጽሐፍ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ በማድረግ ወደ ግእዝ እንዳስተረጐመው (እንደ ተረጐመው) ይነገራል።

ይህ መጽሐፍ ወጥነት ባለው ሁኔታ በአንድ ጊዜ የተጻፈ ሳይሆን፤ የብዙ ጽሑፎች ስብስብ ሆኖ በመጨረሻም በሁለት ክፍል ማለትም በዓለማዊና በመንፈሳዊ ሕግጋትነት የተከፋፈለ ነው። የተጻፈበትን ዘመንና ወደ ኢትዮጵያ የገባበትን ዘመን አስመልክቶ አወዛጋቢ ምንጮች አሉ። ፍትሐ ነገሥት የተጻፈበትም ሆነ የተተረጐመበት ዘመን የተነሣንበት ዓላማ የሚመለከት



www.ethiopianorthodox.org

ስላልሆነ በዚህ ጽሑፍ ትኩረት የምንሰጥበት ጉዳይ አይሆንም።

እንደ ግብፁ የአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ወዳጅ እንደ ጴጥሮስ አስተያየት ከሆነ፣ ፍትሐ ነገሥት የኒቂያ ጉባኤ አባቶች ያሰባሰቡት ወይም ያጠናቀሩት እንጂ ከላይ እንደ ተገለጸው እነርሱ ከራሳቸው አፍልቀው የጻፉት አልነበረም። ጴጥሮስ የፍትሐ ነገሥትን መጽሐፍ እንዲያስመጣም አፄ ዘርዐ ያዕቆብ 20 ወቄት ወርቅ ሰጥተውት እንደ ነበር ይነገራል። ብዙዎች የሚስማሙበት ነው የሚባለው ግን ፍትሐ ነገሥት መጀመሪያ የተጻፈበት ቋንቋ ግሪክኛ ሲሆን፣ አብርሃም በተባለ ሰው ወደ አንድ የታወቀ ሌላ ቋንቋ ተተርጉሞ በመጨረሻ ይህን ቅጂ ወደ አፄ ዘርዐ ያዕቆብ ያመጣውና ወደ ግእዝ የተረጐመው ጴጥሮስ መሆኑን ነው።

ፍትሐ ነገሥት በደንብ ሥራ ላይ ስለ መዋሉ ተጨባጭ መረጃ አለ የሚባለው ግን በአፄ ሠርፀ ድንግል (1557 – 1590) ዘመን ነው። ሆኖም ፍትሐ ነገሥት ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ጥብቅ ቁርኝት እንዲኖረው የተደረገው ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር መሆኑ እሙን ነው። ትምህርቱም የተስፋፋው በቤተ ክርስቲያንዋ ደብተራዎችና ምሁራን አማካኝነት ሲሆን፣ እንደ ሕግነቱ በተለይም እንደ መንፈሳዊ ሕግነቱ ሕገ አጽዋማትን፣ ሕገ ጸሎትን፣ ሕገ ምፅዋትን፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት መስተዳድርን እና የመሳሰሉትን፣ እንዲሁም እንደ ዓለማዊ ሕግነቱ የንግድ ሕግን፣ የቤተሰብ ሕግን፣ የንብረት ሕግን፣ የብድር ሕግን፣ የባርነት ሕግን፣ የወንጀል ሕግን እና የመሳሰሉትን በሰፊው የያዘ ስለነበረ፣ በየዘመኑ የተነሡ ነገሥታት ሕጎቹን በሥራ ላይ በሚያውሉበት ጊዜ ትርጉሙንና እንደምታውን የሚቀበሉት የግእዙ ዕውቀት ካላቸው የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ነበር።

ፍትሐ ነገሥት ከምን? ወደ ምን? በማንና በእነማን ተጻፈ? ተሰበሰበ? ተተረጐመ? የሚለውን አመጣጡን፣ ዛሬ ያለበትን ቅርፁንና ይዘቱን በዝርዝር ለማወቅ ከላይ በመግቢያው የተገለጸውን ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከ1928 ዓ.ም የጠላት ወረራ በፊት አሰባስበው ለሕትመት አብቅተውት የነበረውን፣ በጠላት ወረራ ጊዜ ማተሚያ ቤቱ ሲቃጠል አብሮ የተቃጠለውንና የሸያጭ ወግ ያላገኘውን፣ በኋላም በ1958 ዓ.ም እንደገና በማሰባሰብ «ፍትሐ ነገሥት ንባቡና ትርጓሜው» በሚል ስያሜ ያሳተሙትን መጽሐፍ ማየት ይቻላል።

ይኸው የፍትሐ ነገሥት መጽሐፍ (The Fetha Nagast the Law of the Kings) በሚል ስያሜ ከግእዝ ወደ እንግሊዘኛ በአባ ጳውሎስ ፃድዋ ተተርጉሞ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ሕግ ፋካልቲ በ1960 –61 ዓ.ም የታተመ በመሆኑ እሱን ማየቱ ጠቃሚ ነው። በተጨማሪም ፍትሐ ነገሥት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ከተተረጐመው ሌላ በጣ ልያንኛ፣ በጀርመንኛና በላቲን ቋንቋዎች ተተርጉሞአል።

## 2

ፍትሐ ነገሥት ወደ ኢትዮጵያ ገባ ከምንልበት ከአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን ጀምሮ በየነገሥታቱ ዘመን መንፈሳዊ ሕጉን ቤተ ክርስቲያኒቱ እንዳለ ስትጠቀምበት፣ ቤተ መንግሥቱ ደግሞ ዓለማዊውን ክፍል እንዳለ በሥራ ላይ አውሎ ሲጠቀምበት ቆይቷል። ሆኖም የተለያዩ ልማዳዊ ሕጎች በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች በሥራ ላይ በመዋል ተፈጻሚነት የነበራቸው በመሆኑ፣ ሀገሪቱ ሙሉ በሙሉ በፍትሐ ነገሥቱ ትዳኝ ነበር ማለት በፍጹም የማይቻል ነው።

በቤተክርስቲያኗና በቤተ መንግሥቱ አካባቢም ይሠራበት የነበረው ከላይ እንደ ተገለጸው በጥቂት ምሁራን ተሳታፊነት እንጂ በሕጉ የሠለጠኑ ዳኞች በብዛት ኖረውም አይደለም። የሕጉ አጠቃቀምም በፍትሐ ብሔርም ሆነ በወንጀል ጉዳይ ተገቢ ነው ወይም ተጠቃሽ ነው የሚባለው ሕግ ተነብቦ፣ የሕጉ ትርጉም በሊቃውንት ተተንትኖ፣ ሕጉ በዚህ ሲፈጸም ይታየኛል የሚል እንድምታ ተሰጥቶት፣ የንጉሡ ቃል የመጨረሻ ሆኖ ነው እንጂ፣ ወንበሮች (ዳኞች) በሥርዓት በየደረጃው ተቀምጠው በፍትሐ ነገሥቱ ትርጓሜ ውሳኔ እየሰጡ፣ ፍትሕ ተጓደለብኝ ባዮች በይገባኝ ወደ ላይ እየተላለፉ አልነበረም።

መደበኛው የወንበሮች (የዳኞች) አሠራር በኢትዮጵያ የተጀመረው በአፄ ምኒልክ ዘመን ነው። ለዚሁም ቢሆን በመጀመሪያ አንድ አፈ ንጉሥ ብቻ አይቶት ወደ ንጉሡ ይግባኝ የሚቀርብበት ጊዜ ነበር እንጂ እንደ ነገሩ ብዛት ብዙ ወንበሮች (ዳኞች) አልነበሩም። ወንበሮች የተጨማመሩት ወደ መጨረሻው የአፄ ምኒልክ ዘመን ነው።

ፍትሐ ነገሥቱ በሕግነት ተሰባስቦ አንድ ወጥ ሆኖ የቀረበበት ዘመን በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን እንደ መሆኑ መጠን፣ የኢትዮጵያ ሕግ ቀረፃ በመጀመሪያ በመጠኑ ሥርዓት መያዝ የጀመረው ዝክረ ነገር ከተባለው ከብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ መጽሐፍ (በመጀመሪያ 1939 ዓ.ም ከታተመው) እንደሚገኘው፣ በዳግማዊ አፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ነው። በወቅቱ በሥራ ላይ የዋሉት የሕግ ትምህርት በነበራቸው ምሁራን ተረቅቀው የወጡ ሳይሆን፣ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ በሚገኙ ደብተራዎች ዕውቀት የተረቀቁ፣ በመሠረታዊ መንፈሳቸውም በፍትሐ ነገሥቱ ላይ በሰፈሩ ሐሳቦች ላይ በመመርኮዝ የተዘጋጁ ናቸው ተብሎ ቢገመት ስሕተት አይሆንም።

በወቅቱ የተረቀቁትን ሕጎች ከዝክረ ነገር እንደሚታየው (ገጽ 58 እና ተከታታይ ገጾች) የመንግሥት (የንጉሥ) ሥልጣን በጣም የተስፋፋ፣ ወሰን የሌለው፣ በሥጋዊም በመንፈሳዊም ጉዳይ ውስጥ የሚገባ፣ ስሙ የሚያንቀጠቅጥ፣ በንጉሥ ስም ቂም የተባለ ንቅንቅ የማይልበት፣ ንጉሥ ይሙት ብሎ የማለ ከቃሉ ዝንፍ የማይልበት ሁኔታ እንደ ነበር መገንዘብ ይቻላል። የንጉሥ ስም አንሥቶ መማልም የነገሮች መደምደሚያ ነበር። ምኒልክ ይሙት ከተባለ፣ ኃይለ ሥላሴ ይሙት ከተባለ በራሱ በሕግ መፈጠም እንደሆነ የታወቀ ነበር።

ይህም የእኛ ትውልድ (ቀደም ያልነው) የደረስንበትና የምናውቀው ነው።

በ1900 ዓ.ም መጀመርያ በአፄ ምኒልክ፣ ከ1909 ዓ.ም በኋላ በንግሥት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት በአልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን እንደራሴነት የተረቀቁት ሕጎች የወጡት የውጭ አገር የሕግ አርቃቂዎች ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ወይንም ኢትዮጵያ የሕግ ትምህርት የቀሰሙ ሙያተኞች ኖረዋት ሳይሆን፣ ከላይ እንደ ተባለው የፍትሐ ነገሥት ምሁራን ዕውቀት ታክሎበት የተረቀቁ ናቸው። ከነዚህም የሚከተሉት ይገኙበታል። የቤተ መንግሥት ሥርዓት፣ የአገር ውስጥ ሥራ አካሄድና ደንብ፣ የዳኝነት ሚኒስቴር፣ ለፍርድ ሚኒስቴርና ለወንበሮች የተሰጠ ደንብ፣ ስለ ነፍስ ገዳይ ነገር የተሰጠ ደንብ፣ የውጭ አገር ሰዎች የፍርድ ቤት ደንብ፣ የአፈርሳታ አገዛዝ ደንብ፣ የቀላድ አጣጣል ደንብ፣ የመሬት ይዞታ ደንብ፣ የ1923 ሕገ መንግሥት፣ ስለ ውጭ አገር ዜጋ የወጣ ደንብ ሁሉ እና የመሳሰሉት ናቸው።

ከ1934 ዓ.ም የኢጣሊያ ፋሽስት ወረራ በኋላ (በሌላ አነጋገር ዘውድ ከተመለሰ በኋላ) የሕግና የፍትሕን ሥራ በተመለከተ ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር በተደረጉ ስምምነቶች የእንግሊዝ ዜግነት ያላቸው ምሁራን እስከ 1960 ዓ.ም መባቻ ድረስ በቀጥታ በዳኝነት ሥራ ላይ ተመድበው በበላይነት ሲሠሩ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በፍትሕ በአስተዳደርና በዐቃቤ ሕግ አገልግሎትም ከፍተኛ ቦታ ተሰጥቷቸው የነበረ ሲሆን፣ የፍትሐ ነገሥት ዕውቀት የነበራቸው ኢትዮጵያውያንም አብረዋቸው ያገለግሉ ነበር። የሕጎች ቀረፃን በተመለከተ ከ1934 ዓ.ም ጀምሮ በነጋሪት ጋዜጣ እየታተሙ ይወጡ የነበሩት የተለያዩ ሕጎች፣ በዚሁ ሁኔታ በውጭ አገር ሰዎች ተሳትፎ ጭምር ይረቀቁ እንደ ነበረ በርካታ ማስረጃዎች አሉ። በወቅቱ የኢትዮጵያ ፓርላማ (ምክር ቤት) መክሮባቸው የሚወጡት ሕጎች በዚህ ዓይነት እየተዘጋጁ የሚወጡ ከመሆናቸውም በላይ፣ ዋና ዋናዎቹ ሕጎች በፍትሐ ነገሥት ጉባኤ ጭምር ከፍተኛ ውይይት ተደርጎባቸው የሚያልፉ ነበሩ።

በዚህ ዓይነት ከወጡት ሕጎች በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱት መካከል የ1948 ዓ.ም የተሻሻለው ሕገ መንግሥትና የ1949 ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ይገኙበታል። ከእነኚህ ቀጥለው በመከታተል የወጡት የፍትሐ ብሔር፣ የንግድ፣ የባሕር ሕጎች በ1950ዎቹ መጀመሪያ ዓመታት የወጡ ሲሆን፣ የእነኚህ ሕጎች ምንጮች በአብዛኛው ዘመናዊ የውጭ ሀገር ሕጎች፣ አርቃቂዎቹም የውጭ ሀገር የሕግ ምሁራንም ጭምር ናቸው። በምክር ቤት ደረጃና ከዚያም በፊት ግን የፍትሐ ነገሥት ምሁራን ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገውባቸዋል።

### መደምደሚያ

በዚህ ጽሑፍ ለማቅረብ የተፈለገው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በሕግ ቀረፃ ረገድ የነበራትን መሠረታዊ ሚና ከየት እንዳገኘችው በመግለጽና በተዘዋዋሪ የፍትሐ ነገሥት ትምህርት ምን ያህል በቤተክርስቲያን አካባቢ እንደዳበረና ለቤተ መንግሥትም እገዛ እንዳደረገ ለመጠቆም እንጂ ሙሉ ትንታኔ ለማድረግ አይደለም። በመሆኑም የተሰነዘረው ሐሳብ ፍትሐ ነገሥት ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደ ገባ፣ ተተርጉሞ እሥራ ላይ እንዴት እንደ ዋለ፣ ለዘመናዊ ሕግ ቀረፃም ምን ያህል አስተዋፅኦ እንዳደረገ መንደርደሪያ እንዲሆን በማለት የቀረበ ነው። ❑


The Careful Movers

PACKTRA Pvt. LTD. Co,

* Packing - Moving
* Clearing - Fowarding
* Shipping, Transportation
* Heavy Lifting - Storage

Branch Offices: ASSAB, MASSAWA, DIREDAWA, MOYALE, DJIBOUTI

HEAD OFFICE:
Phone: 251-1-519723
251-1-516504
Fax: 251-1-513788
Telex: 21963 PACKTRA
WARE HOUSE:
Phone: 251-1-130052
P.O. Box 5432
Addis Ababa
Ethiopia






www.ethiopianorthodox.org

# የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን

## ቅዱሳት መካናት ንብረቶች በኢየሩሳሌም

አምባሳደር ተፈራ ኃይለ ሥላሴ

ኢየሩሳሌም የክርስትና ሃይማኖት ምንጭ ስለሆነች ልዩ ልዩ የክርስትና ሃይማኖቶች በዚህች ቅድስት መዲና በተለይ በኢየሩሳሌም ዙሪያ ወይም አቅራቢያ፣ ገዳም ወይም መቅደስ ከተቻለ ሁለቱንም ለማግኘት ብርቱ ጥረት ማድረጋቸው የታወቀ ነው። በኢየሩሳሌም መቅደስ ወይም ገዳም ካላቸው ሃይማኖቶች መሐል የአርመን፣ የሶርያ፣ የኢትዮጵያና የግብፅ ኦርቶዶክስ አብያተክርስቲያን ይገኙባቸዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ንብረቶች፣ የቅዱስ ሚካኤል መቅደስና የዴር ኤል ሡልጣን ገዳም በኢየሩሳሌም መቅደስ ካላቸው ኑታ ገጠም አቀማመጥ ሌሎች አብያተ ክርስቲያን የሚመኙአቸው ናቸው። የግብፅ ቤተክርስቲያን በኢየሩሳሌም በጊዜው ከነበሩት አብያተ ክርስቲያን ሀብታምና በቱርክ መንግሥት ዘንድ ተሰሚነት ከነበረው ከአርመን ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ጋር ተመሳጥረው የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከንብረቶችዋ ለመንቀል እርምጃ ወስደዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የቅዱስ ሚካኤልን መቅደስ የዴር ኤል ሡልጣንና ሌሎችም አያሌ ንብረቶች ከጥንት ጀምሮ በይዞታዋ ሥር አድርጋ ስትገለገልባቸው እንደነበረ ብዙ ታሪክ ጸሐፊዎች በየዘመኑ መዝግበውታል። ከእነዚህም ውስጥ ለምሳሌ ያህል ጥቂት መጥቀስ ይቻላል።

በፓሪስ ብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት የሚገኝ ስለ ኢትዮጵያ የተዘጋጀ ጽሑፍ በ1370 ዓ.ም እና በ1371 ዓ.ም በኢየሩሳሌም ስለ ንብረቶች ባለቤትነት የወጡ ማስታወቂያዎች ኢትዮጵያ የንብረቶቹ ባለቤት እንደነበረች ይጠቁማሉ። በቢሪቲሽ ሙዝየም የሚገኝ አንድ ስለ ኢትዮጵያ የተዘጋጀ ጽሑፍ ከ1422 ዓ.ም በፊት ኢትዮጵያ በጎልጎታ መቅደስ እንደ ነበራት መዝግቦታል። በተጨማሪም አፄ ያዕቆብ በ1430 ዓ.ም ለዴር ኤል ሡልጣን ገዳም የላኩት ስጦታ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች በኢየሩሳሌም ማስታወቂያ ተገልጾአል።

ከእነዚህ መረጃዎች ኢትዮጵያ ቢያንስ ከ15ኛው ክፍለ ዘመን በፊት የንብረቶቹ ባለቤት እንደ ነበረች ማስተዋል ይቻላል። በንብረቶቹ ላይ ተቀናቃኝ የተነሣው በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ሲሆን ለዚህም አመቺ አጋጣሚ የፈጠረው በ1830 ዓ.ም በኢየሩሳሌም ገብቶ የነበረው ወረርሽኝ በሽታ ነው። ወረርሽኙ ኢትዮጵያውያን ምእመናንን ፈጃቸው። በዚህ አሳዛኝ አጋጣሚ ተጠቅመው የአርመንና የግብፅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያን በገዳሙ የነበሩትን መጻሕፍት፣ መዛግብትና ሰነዶች ወዘተ. ወረርሽኙን ያሰራጫሉ በሚል ሰበብ እንዲቃጠሉ የኢየሩሳሌም ገዥ ለነበረው ለቱርክ መንግሥት እንደራሴ አቤቱታ አቀረቡ። እንደራሴውም በቀረበለት አቤቱታ መሠረት ሰነዶቹ እንዲቃጠሉ አደረገ። በተወሰደው እርምጃ የኢትዮጵያን የንብረት ባለቤትነት የሚያረጋግጡ መረጃዎች በእሳት ቃጠሎ ወደሙ። ግብፆቹም ያለአንዳች ሥጋት የመቅደሱንና የገዳሙን በሮች ቁልፎች በእጃቸው አደረጉ። ወረርሽኙ ካለፈም በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም የሄዱትን ምእመናን ግብፆቹ መጸለይና መጠለያ ነፈጓቸው። ኢትዮጵያውያኑ ምእመናንና መነኮሳት ንብረታቸውን መነጠቃቸውንና የደረሰባቸውን ግፍ በመዘርዘር ንብረቶቹ እንዲመለሱላቸው ለቱርክ መንግሥት እንደራሴ ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ። ምእመናኑ ለኢትዮጵያ መንግሥትም አቤቱታቸውንና የተፈጸመባቸውን በደል ከማሰማት አልተቆጠቡም።

ከዚህ በታች እንደምንመለከተው በየዘመኑ በኢትዮጵያ ነገሥታትና መሪዎች አቅም፣ ጊዜና የፖለቲካ ሁኔታ በፈቀደ መጠን ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች በኢየሩሳሌም ትኩረት ሰጥተዋል።

## I

ዘመነ መሳፍንት የማዕከላዊ መንግሥት አመራር የተፈታበት ቢሆንም እንኳ ኃያላን ከነበሩት መሳፍንት የአማራና የበጌምድር ገዢ ራስ አሊ አሉላና የትግራይ ገዢ ደጃዝማች ውቤ ኃይለ ማርያም በጐንደር ቤተ መንግሥት ንጉሡ በተገኙበት የሃይማኖት መሪዎችንና ታላላቅ ሰዎችን ሰብስበው በጉዳዩ ላይ ከተመከረበት በኋላ ለእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶሪያ ንብረቶቹን በማስመለስ ረገድ ዕርዳታ እንዲያደርጉላቸው ጥያቄ እንዲቀርብ ስምምነት ተደረገ። ሁለቱ መሳፍንት በይዘት አንድ ዓይነት የሆኑ ደብዳቤዎች ለንግሥት ቪክቶሪያ ጽፈው ላኩ።

ደብዳቤዎቹ ቀንና ቦታ አይጠቅሱም። ዳሩ ግን ቆንስል ወልተር ፕላውደን ለእንግሊዝ መንግሥት ካቀረቡት ዘገባ ደብዳቤዎቹ የተጻፉት ከ1844 ዓ.ም በፊት እንደ ነበር መገመት ይቻላል።

ከላይ እንደ ጠቀስነው የመሳፍንቱ ደብዳቤዎች ከመጨረሻው ዐረፍተ ነገር በስተቀር አንድ ዓይነት ስለሆኑ የራስ አሊን ደብዳቤ እነሆ በሙሉ ጠቅሰነዋል።

«እምኀበ ርዕሰ መኳንንት አሊ ገብረ ንጉሠ ነገሥት እግዚአብሔር ዘይትወሐድ በመለኮት ወይሴባሕ በገጻት ትብጻሕ ኀበ መንግሥተ እንግሊዝ ። እንዴ ነሽ በጐ ነሽ የሰማይ የምድሩን ያህል እኔ ባንቺ ወዳጅነት ጠንቻለሁ። አንቺም በእኔ ወዳጅነት ጥኚ። ምነው አንቺ ባለሽ እርስቱን መንቀሌ። ሁሉ በየእርስቱ ተቀምጦ እኔ ተነቀልሁ። አሁንም ርስቱን እንዳልነቀል አድርጊልኝ። የሐበሻን እጣ መሬቱን ተነቀልሁ። ርስት መንቀል ጥሩ ነገር ነው? ርስተ ምድር ርስተ ሰማይ ነውና። ባንቺ መንግሥት ዘመዴ አይነቀል። ሳሙኤል ጉባት አደራህን ጠበቃ ሁናቸው። ርስቱን አልነቀል፤ ዘመዶቼን አደራ። ምትወጂውን ነገር ላኪልኝ እልክልሻለሁ።»

ራስ አሊ (ማህተም)

ደብዳቤው በዲፕሎማቲክ ቋንቋ የተጻፈ ባይሆንም የቅሬታቸውን ጭብጥ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።

የእንግሊዝ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቪስካውንት ፓልመርስቶን ደብዳቤዎቹ እንደ ደረሱዋቸው ኢየሩሳሌም ለነበረው ቆንስላቸው ለሚስተር ጀምስ ፊን ኢየሩሳሌምን ለመሳለም ለሚመላለሱት ምእመናንና በኢየሩሳሌም ለሚኖሩት መነኮሳት ዕርዳታ እንዲያደርጉላቸውና ድጋፍ እንዲሰጣቸው ትእዛዝ አስተላልፈውለት ነበር።

ቆንስሉ በኢትዮጵያውያኖቹ ላይ የተፈጸመውን ግፍ በኢየሩሳሌም የአንግሊካን ቤተክርስቲያን ጳጳስ አቡነ ሳሙኤል ጉባት አስጨብጠውት ስለ ነበር ለመነኮሳቱ ምክር በመለገስና ጉዳያቸውን ለቱርክ መንግሥት ባለሥልጣኖች በማቅረብ ከፍ ያለ ድጋፍ ሰጥቶአቸዋል።

በተለይ አቡነ ሳሙኤል ጉባት በኢትዮጵያ የአንግሊካን ሚስዮን አቋቁመው ከ1820 ዓ.ም በቆዩበት ዘመን በግብፅና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አብያተክርስቲያን መሃል የነበረውን የበላይነትና የበታችነት ግንኙነት ጠንቅቀው በመረዳታቸው የግብፅ ቤተክርስቲያን የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች በኢየሩሳሌም የራሷ ለማድረግ ከአርመን ቤተ ክርስቲያን ጋር የምትሸርበውን ሴራ ለመረዳት አላዳገታቸውም ነበር። የግብፅ ቤተክርስቲያን የሃይማኖት ቅኝ ገዥ ሆና በኢትዮጵያውያኑ ላይ የምትፈጽመውን በደል ለመቋቋም ኢትዮጵያውያኑ ጎን ቆመው ምክርና ድጋፍ ይሰጡአቸው ነበር። የሚያስገርመው ነገር በእምነት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ጋር አንድ የሆኑት የግብፅና የአርመን ኦርቶዶክስ አብያተክርስቲያን እውነትን አድበስብሰው በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላይ ግፍ ሲፈጽሙ በእምነት የማትመስላቸው የአንግሊካን ቤተክርስቲያን ጳጳስ በኢትዮጵያ በደጃዝማች ውቤ ኃይለ ማርያም በመባረራቸው ቂም ሳይዙ እውነትን ብቻ በመመርኮዝ የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን መብት ለማስከበር ከሚጠበቅባቸው በላይ ጥረት አድርገዋል።

ኢትዮጵያውያኑ መነኮሳት፣ አቡነ ጉባት በሰጡአቸው ምክር መሠረት ከጸሎት በኋላ የግብፅ ካህናት ሲዝናኑ አዘናግተው የበሮቹን ቁልፎች ወሰዱ። ኢትዮጵያውያኑ በወሰዱት እርምጃ የተናደዱት የግብፅና የአርመን አብያተ ክርስቲያን ተጠሪዎች ቆንስሉ ቁልፎቹን እንዲያስ መልሱላቸው ስሞታ አቀረቡ። ቁልፎቹ የተወሰዱባቸው በአቡነ ሳሙኤል ጉባት ምክር እንደ ነበረ ጨምረው አስረዱ። አቡነ ጉባት ወረርሽኙ ከመግባቱ ከሃያ አምስት ዓመታት በፊት የኢትዮጵያን ገዳም በጐበኙበት ጊዜ የተቃጠሉትን መዛግብት የተመለከቱና ሰነዶቹም የኢትዮጵያን ባለንብረትነት ማረጋገጣቸውን ለቆንስል ፊን ገለጹ።

ቆንሲሉ በሽምግልና የግራ ቀኙን አዳምጠው አዲስ የአርመን ፓትርያርክ ተሹመው ሥራቸውን ሲጀምሩ ጉዳዩ በዝርዝር ይወሰናል፣ እስከዚያው ድረስ ቁልፎቹ በሦስተኛ ሰው እጅ ተቀምጠው ቤተ መቅደሱ ለሁሉም ወገኖች ክፍት እንዲሆን ያቀረቡትን አስታራቂ ሐሳብ የግብፅና የአርመን አብያተክርስቲያን ተጠሪዎች ሳይቀበሉት ቀሩ። ከዚያም አቤቱታቸውን ለኢየሩሳሌም የቱርክ መንግሥት ፓሻ (እንደራሴ) አቀረቡ። ፓሻው ያሰባሰቡት መጀሊስ ጉዳዩን በአዩበት ቀን አቡነ ጉባት ተገኝተው ስለነበር የአርመን ፓትርያርክ እስከሚሾም ድረስ በገዳሙ በኩል ወደ መቅደሱ የሚያስገባው በር ቁልፍ በኢትዮጵያውያኑ እጅ በኢየሩሳሌም መቅደስ በኩል ወደ መቅደሱ የሚያስተላልፈው በር ቁልፍ በግብፆቹ እጅ እንዲቀመጥ ያቀረቡት ሐሳብ ተቀባይነት



www.ethiopianorthodox.org

ሳያገኝ ቀረ። መጅሊሱ ጉዳዩን ከሥር ገብቶ ሳይመረምር በግብፆቹ ጥያቄ መሠረት ኢትዮጵያውያኑ ቁልፎቹን እንዲመልሱ ወሰነ።

ጉዳዩ በዚህ ደረጃ ላይ እንዳለ ኅዳር 14 ቀን 1843 ዓ.ም የአርመን ፓትሪያርክ ተሾሙ። ፓትርያርኩ በአቀራረባቸው አስመሳይና ጮሌ ስለነበሩ እንዴት በወንድማማች መሃከል እንዲህ ያለ አሳፋሪ ድርጊት ይፈጸማል በማለት ቆንስል ፊን አቡነ ጐባትና የኢትዮጵያውያኑ ወኪሎች በተገኙበት የግብፆቹንና የአርመኖቹን ተጠሪዎች ገሠፁ።

ከዚህ በኋላ ፓትርያርኩና ቆንስል ፊን ታኅሣሥ 5 ቀን 1843 ዓ.ም ጉዳዩ ተጣርቶ የንብረቶቹ ባለቤት ሁለቱ ወገኖች በሚያቀርቡት ማስረጃ መሠረት እስከሚወሰን ድረስ የበሮቹ ቁልፎች በግብፆች እጅ ሆነው መቅደሱ ለግብፆቹና ለኢትዮጵያውያኑ በእኩልነት እንዲያገለግል ቀደም ሲል ግብፆቹ ሲያደርጉት እንደ ነበረው በሮቹ በምሽት እንዳይቆለፉ፣ ኢትዮጵያውያኑ በአፈጻጸም ረገድ ለሚያጋጥማቸው ማናቸውም ችግር በቆንሲል ፊን አማካይነት አቤቱታ ለአርመኑ ፓትርያርክ እንዲያቀርቡ ወሰኑ።

ቆንስል ፊን ውሳኔው ለኢትዮጵያውያኑ ያለ ገደብ በመቅደሱ ለመገልገል ከሰጣቸው መብትና በሮቹ በማናቸውም ጊዜ ክፍት እንዲሆኑ ከመደረጉ አኳያ ሲታይ እንደ እመርታ ሊቆጠር ይችላል ብለው ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ ውሳኔው ጊዜያዊ ቢሆንም ተፋላሚዎቹ ወገኖች የሰነድ ማስረጃ ስላልነበራቸው ለዘለቄታ የሚቆይ ነበር። ግብፆቹ የይዞታ መብት ሲጸናላቸው ኢትዮጵያውያኑ የመገልገል መብት ብቻ ነው የታወቀላቸው። በዚህ አንጻር ሲታይ ውሳኔው ለግብፆቹ በሚያመች መልክ ነው የተሰጠው። የአርመኑ ፓትርያርክ በዚሁ አጋጣሚ የአርመን ቤተክርስቲያን በንብረቶቹ ላይ የነበራትን የተፋላሚነት ጥያቄ ስላነሡ ሙግቱ በኢትዮጵያና በግብፅ ቤተክርስቲያናት መሃከል ብቻ ሆነ።

አቡነ ሳሙኤል ጐባት ኢትዮጵያውያኑን በሕጋዊ መንገድ ለመርዳት እንዲፈቀድላቸው በ1844 ዓ.ም የራስ አሊንና የደጃዝማች ውቤን ደብዳቤዎች የእንግሊዝኛ ትርጉሞች አያይዘው ለእንግሊዝ መንግሥት ጥያቄ አቀረቡ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከእርሳቸው በፊት የነበሩት ሚኒስትር ቪስካውንት ፖለመርሰቶን ለኢየሩሳሌም ቆንስል ለሚስተር ፊን ሰጥተውት የነበረውን መመሪያ ሽረው አዲሱ ቆንስል ለኢትዮጵያውያኑ መነኮሳትና ምእመናን በሚስጥር ድጋፍ ከመስጠት በስተቀር በኢትዮጵያውያኑ ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገቡና

አቢሲኒያ ባንክ
BANK OF ABYSSINIA
INNOVATIVE, COMPETITIVE, EFFICIENT AND DYNAMIC

| | | |
|---|---|---|
| Tel: | 51 18 22 | Bole Branch |
| | 15 97 17 | Guenet Branch |
| | 75 25 20 | Negadras Branch |
| | 12 08 53 | Mela Branch |
| | 51 41 30 | Filwoha Branch |
| | 08-20 13 44 | Bahr Dar Branch |
| | 06-20 32 80 | Awassa Branch |

We are committed to maintaining the highest standard of banking service.

*P.O. Box 12947 Fax: (251-1-514409*
*E-mail: abyssinia@telecom.net.et*
*Addis Ababa, Ethiopia*



በቱርክ መንግሥት ዘንድ የኢትዮጵያውያኑ ሕጋዊ ጠባቂ መስሎ እንዳይታይ በብርቱ አስጠነቀቁት። ጳጳሱንም ለኢትዮጵያውያን የሚሰጡት ድጋፍ ከፖለቲካ ውዝግብ የራቀና በመንፈሳዊ ዕርዳታ ላይ ብቻ እንዲያተኩር አሳሰቡአቸው።

አቡነ ጐባት ኢትዮጵያውያንን በበለጠ ለመርዳት ፈልገው ለመንግሥታቸው ላቀረቡት ጥያቄ የተሰጠው መልስ የእንግሊዝ ቆንስል ለኢትዮጵያውያኑ ሲሰጥ የነበረውን ድጋፍና ዕርዳታ ጨርሶ አስቀረው። የኢየሩሳሌም የቱርክ መንግሥት እንደራሴም በበኩሉ የእንግሊዝ ቆንስል ስለ ኢትዮጵያውያኑ የሚያቀርበውን ማናቸውንም ጥያቄ የማይቀበል መሆኑን አስታወቀ።

የአርመኑ ፓትርያርክ የሰጡት ጊዜያዊ ውሳኔ ክርክሩ ተዳፍኖ እንዲቆይ ከማድረጉ በስተቀር ዘላቂ መፍትሔ አልነበረም። የቱርክ መንግሥት ለኢትዮጵያውያኑ በጎ አመለካከት ከመንፈጉም በላይ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ጥገኛ እንደ ነበረች አገሪቱና ሕዝቦቿዋም በቀጥታ የግብፅ መንግሥትና በተዘዋዋሪ ደግሞ የቱርክ ጥገኞች አድርጎ የመቁጠር የተሳሳተ አቋም ነበረው። ይህ የተሳሳተ አመለካከት የቱርክን ቅኝ ገዥነት ለተቀበለችው ለግብፅ የንብረት ክርክርዋን በፈለገችው መልክ ለማስወሰን አመቺ ነበር። ግብፆቹ በቱርክ መንግሥት ዘንድ ተሰሚነት ሲኖራቸው ኢትዮጵያውያኑ የግብፅ ጥገኛ እንደሆኑ ተቈጥረው የሚያቀርቡትን አቤቱታ በሥርዓት አዳምጦ ፍትሕ የሚሰጣቸው መንግሥት አልነበረም።

በጊዜያዊው ውሳኔ ያልረኩትና የቱርኩ መንግሥት ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የነበረው አቋም የሚጠቅማቸው መሆኑን የተገነዘቡት ግብፆች ክርክሩን ቀስቅሰው አቤቱታቸው እንደገና እንዲታይ ለቱርክ መንግሥት ፓሻ አመለከቱ። በፓሻው የተመራው መጅሊስ መቅደሱና ገዳሙ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ንብረቶች ስለሆኑ ኢትዮጵያውያኑ በንብረቶች የመገልገል መብት የላቸውም ብሎ ወሰነ። በውሳኔው ቅር የተሰኙት ኢትዮጵያውያን ለቁስጥንጥንያ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝ ግብፆቹ ከቱርኮቹ ጋር በነበራቸው የተሣሠረ ግንኙነትና ዳኞቹንም በስጦታ በመደለል ውድቅ ሆነ።

## II

ጊዜው የዘመነ መሳፍንት ማብቂያ ፍልሚያ የሚደረግበት ስለ ነበር ኢትዮጵያውያን መነኮሳትና ምእመናን ከአገራቸው ሲያገኙት የነበረው ድጋፍ ቀዘቀዘ። አፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መሳፍንትን ገርስሰው በምትኩ አዲስ መንግሥትና ሥርዓት ለመዘርጋትና አገርን ለማረጋጋት ሲጣደፉና የቱርክንም መንግሥት በጠላትነት ፈርጀውት ስለነበረ የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች ለማስመለስ ፋታ አላገኙም።ከእንግሊዝ መንግሥትም ጋር አፍላ ወዳጅነት ላይ በነበሩበት ጊዜ ንብረቶቹን ለማስመለስ ሞቅ ያለ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ አልታየም።

የእንግሊዝ ቆንስል ካፒቴን ካሜሮን ከታሠሩበት አንዱ ምክንያት በ1855 ዓ.ም ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ከኢየሩሳሌም ድረስ ተጉዘው በኢየሩሳሌም የእንግሊዝ ቆንስል ይሰጣቸው የነበረውን ድጋፍና ዕርዳታ ከማቋረጡም በላይ ከግብፆች ጋር ተባብሮ መቅደሳቸውንና ገዳማቸውን እንደ አስነጠቃቸው ለአፄ ቴዎድሮስ ያቀረቡት አቤቱታ እንደ ነበር ከእሥረኞቹ አንዱ ሚስተር ፍላድ ለእንግሊዝ መንግሥት መስከረም 18 ቀን 1859 ዓ.ም በጻፉት ደብዳቤ ገልጸውታል ።

የኢትዮጵያ ነገሥታት ለኢየሩሳሌም የነበራቸውን ፍቅርና መንፈሳዊ ስሜት የእንግሊዝ መንግሥት ጠንቅቆ በማወቁ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች የባለቤትነት ጉዳይ አፄ ቴዎድሮስ ያሠሩዋቸውን ዜጎቻቸውን ለማስፈታት የሚረዳ የመደራደሪያ ነጥብ ሊሆን እንደሚችል ገምተዋል። እሥረኞቹን ለማስፈታት ከንግሥት ቪክቶሪያ የተላኩት ልዩ ልዑክ ሚስተር ሑርሙዝ ራሳም አፄ ቴዎድሮስ እሥረኞቹን ከለቀቁ በአጸፋው የእንግሊዝ መንግሥት የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች በኢየሩሳሌም ለማስመለስ የሚጥሩና በኢየሩሳሌም ለነበረው ቆንስላቸው ጉዳዩን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ትእዛዝ ለማስተላለፍ ዝግጁ እንደነበሩ ለንጉሡ በቃል እንዲገልጽ አዘውታል። በሌላ በኩል በኢየሩሳሌም የአርመን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ እሥረኞቹ እንዲፈቱ የሚማልድ ልዑካን ከወርቅና ከአልማዝ የተሠራ መስቀልና የአደራ ደብዳቤ አስይዘው ወደ አፄ ቴዎድሮስ ዘንድ ልከው ነበር። እሥረኞቹ ከተፈቱ የቤተክርስቲያኒቱ ቅዱሳት መካናት ንብረቶቹ ለኢትዮጵያ እንደሚመለስና ለወደፊትም በኢትዮጵያውያን ላይ በደል እንዳይፈጸም ልዩ ጥበቃ ለማድረግ ዝግጁ እንደነበሩ አረጋግጠዋል። ልዑካኑ ኢትዮጵያ መጥተው መእዕክቱን ለአፄ ቴዎድሮስ ማድረሳቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አልተገኘም።

ነገሥታትና መሪዎች ይመጣሉ ያልፋሉ፤ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች በኢየሩሳሌም ባለቤትነት ጉዳይ ግን አልተለወጠም። መነኮሳቱና ምእመናኑ ሕጋዊና ተገቢ ጥያቄአቸውን ከትውልድ ወደ ትውልድ ያስተላልፋሉ። ትውልድና ዘመን በአለፈ ቁጥር የንብረቶቹ የባለቤትነት ክርክር የፖለቲካ ይዘት እየታከለበት ሊቋረጥ አልቻለም።

## III

አፄ ዮሐንስ አራተኛ በዴር ሡልጣን ይኖሩ ለነበሩ መነኮሳት ከፍተኛ እገዛ ያደርጉ እንደ ነበር የታሪክ ሰነዶች ያስረዳሉ። መነኮሳቱ ችግር በገዙባቸው የአርመን ገዳም ጥገኛ ለመሆን በተገደዱበት ጊዜ የገዳሙ አስተዳዳሪ የነበሩት መምህር ወልደ ሰማዕት ይህንኑ ለአፄ ዮሐንስ ገልፀውላቸው ነበር። እሳቸውም «አይዟችሁ እኔ ሳለሁ የሚቸግራችሁ ነገር አይኖርም» በማለት በየዓመቱ ገንዘብና ሌላም ዕርዳታ በመላክ ማኅበሩንና አንድነቱን አጽንተው ራሱን እንዲችል አድርገዋል።



www.ethiopianorthodox.org

አፄ ዮሐንስ በነገሡ በሦስተኛው ዓመት ከሞስኮቦች ቤተ ክርስቲያን አጠገብ «ዕብነ–ሕይወት» ብለው የሠየሙትን ቦታ በአራት ዕልፍ ገዝተው ማኅበሩ ወይን በመትከል እንዲጠቀምበት አድርገዋል። በዚሁ ቦታ ላይ ከግብፅና ከአርመን ክርክር ነፃ የሆነች «ደብረ ገነት» የተባለችውን ቤተክርስቲያንም አሠርተዋል። ቦታው ከፍተኛ ሥፍራ ላይ በመገኘቱ ከሕንፃ ቤተክርስቲያኑ የተለየ ቅርፅና ውበት ጋር ተዳምሮ የኢየሩሳሌም ተሳላሚዎችን እይታ ከሩቅ ይስባል።

አፄ ዮሐንስ ጉርዕ ላይ ከቱርኮች ጋር ባደረጉት ጦርነት ከምርኮ የተገኘውን ስድስት ሣጥን ወርቅ በኢየሩሳሌም ለሚገኙ መነኮሳት የለገሡ ሲሆን፣ የሣጥኑም ምልክት እስከ አሁን ይገኛል። ንጉሠ ነገሥቱ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳም መነኮሳትን ከመርዳታቸው በተጨማሪ ሥርዓትና ፍቅር በመካከላቸው እንዲኖር ንጉሣዊ ምክር በመለገስ ያበረታቱአቸው እንደ ነበር ይልኳቸው የነበሩት መልዕክቶች ያስረዳሉ።

## IV

አፄ ምኒልክ ከእርሳቸው በፊት የነበሩት ነገሥታት ሲያደርጉ እንደ ነበረው ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች በኢየሩሳሌም ጉዳይ የሚገባውን ትኩረት ከመስጠት አልተቆጠቡም። በተለያዩ ጊዜያት የንብረቶቹን ባለቤትነት ለማረጋገጥ ያደረጉት ሙከራ እየከሸፈ በመቸገራቸው የሩሲያ መንግሥት ንብረቶቹን በማስመለስ እንዲተባበራቸው ጠየቁ። የሩስያ መንግሥትም የንብረቶቹን ባለቤትነት ለማረጋገጥ የሚበጅ መረጃዎች በማሰባሰብ ለሚሰጣቸው አገልግሎት በአጸፋው ከሚመለሱት አሥራ ሁለት ንብረቶች ሁለት እንዲሰጡት ጠየቀ። በአቀረበው ጥያቄ መሠረት በ1885 ዓ.ም የቃል ስምምነት ተደረገ።

የሩስያ መንግሥት በመንግሥት ደረጃ ሰነዶች የማፈላለግን ተግባር ቢያካሂድ ከቱርክ መንግሥት ጋር አለመግባባት እንደሚፈጥርበት ገምቶ ሰነዶቹ በግለሰብ እንዲፈለጉ አደረገ። በኢትዮጵያ ውስጥ ሰነዶቹን የሚያፈላልጉ ኃላፊነት የሩሲያ ዜጋና የአፄ ምኒልክ ባለሟል ለነበሩት ለካውንት (በኋላ ደጃዝማች) ሊዮንቴፍ ተሰጠ። እርሳቸው ባደረጉት ጥረት በኢትዮጵያ ውስጥ ለጉዳዩ የሚጠቅሙ ሰነዶች ሳያገኙ ቀሩ። ከዚያም የምርምሩን አድማስ በማስፋት ፍለጋውን በኢየሩሳሌምና በቁስጥንጥንያ ለማካሄድ ተወስኖ በነበረበት ጊዜ ኢጣልያ የቱርክን ቅኝ ግዛት ሊቢያን ለመንጠቅ ጦርነት ከፈተች። የሩስያ መንግሥት በአጋጣሚው በመጠቀም ለቱርክ መንግሥት የጦር መሣሪያ ዕርዳታ ለመስጠት መሻቱን አስታወቀ። በአጸፋውም ስለ ኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች በኢየሩሳሌም ከቱርክ መዛግብት ቤት ሰነዶች ፈልጎ ያገኘውን ለመውሰድ እንዲፈቀድለት ጠየቀ። የቱርክ መንግሥት ለሚያገኘው ወሳኝ የጦር መሣሪያ ዕርዳታ ለእርሱ ፋይዳ የሌላቸው ሰነዶች አሳልፎ መስጠት ቀላል ዋጋ ስለነበረ ከሩስያ መንግሥት የቀረበለትን ሐሳብ በጸጋ ተቀበለው።

የሩስያ ቄሣር መንግሥታቸው ለጦር መሣሪያ መግዣ በመደበው ላይ ከሩስያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንና የሩስያ ልዕልት ኤልሣቤጥ በግላቸው ለዚሁ ዓላማ እንዲውል የቸሩትን 200,000 (የእንግሊዝ ፓውንድ) ጨምረው አንድ መርከብ ሙሉ የጦር መሣሪያ አስገብተው በሊቢያ ከጣልያን ጦር ጋር በፍልሚያ ላይ ለነበረው ለቱርክ ሠራዊት ላኩለት። መሣሪያው በተፈለገበት ወሳኝ ሰዓት ደርሶ የቱርክ ሠራዊት የኢጣሊያን ጦር ድል አድርጎ ቅኝ ግዛቱን አስከበረ። የቱርክ መንግሥት በቀውጢ ሰዓት የሩስያ መንግሥት ያሳየው ወዳጅነት ስላረካው የሩስያ ወኪሎች የሚፈልጉአቸውን ሰነዶች እንዲወስዱ ፈቀደላቸው።

የሩስያ መንግሥት የባለቤትነቱን ማረጋገጫ ሰነዶች ማግኘቱን በ1906 ዓ.ም ለኢትዮጵያ መንግሥት አስታወቀ። ከዚህ ጋር አያይዞ ቀደም ሲል በቃል በተደረገው መግባባት መሠረት ለድካሙ ዋጋ ሁለት ቦታዎችና በግዥ ደግሞ የሚቻለውን ያህል እንዲሰጡ ጥያቄ አቀረበ።

## V

ጉዳዩ ከፍጻሜ ሳይደርስ አፄ ምኒልክ ቢያርፉም አልጋውን የወረሱት ልጅ ኢያሱ በአያታቸው የተጀመረውን ድርድር በኢትዮጵያ ከሩስያ ቆንስል ጋር ቀጥለው አንድ የልዑካን ቡድን በኢየሩሳሌም በኩል አድርጎ ወደ ሩስያ እንዲጓዝ ተስማሙ።

ልዑካኑ ከልጅ ኢያሱ ለቄሣሩ የተጻፈ የአደራ ደብዳቤ ይዘው ድሬዳዋ ሲደርሱ አንደኛው የዓለም ጦርነት በመከፈቱ ጉዞው ተጓጐለ። በዚህ አጋጣሚ መፍትሔ ሊያገኝ ተቃርቦ የነበረው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች በኢየሩሳሌም ጉዳይ ተጨናገፈ።

ጦርነቱ ከተጠበቀው ጊዜ በላይ ተራዘመ። በመሐሉም የሩስያ አብዮት ፈነዳና ጉዳዩን በቅርብ ይከታተሉት የነበሩት ቄሣር ከነቤተሰባቸው ተረሸኑ። በኢትዮጵያ ውስጥም ልጅ ኢያሱን አውርዶ ወይዘሮ ዘውዲቱን ለማንገሥ ትግሉ ተጧጡፎ ነበር። እነዚህ ሁኔታዎች ተዳምረው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች ባለቤትነት ለማረጋገጥ የተደረገውን ጥረት ውጤት አልባ አደረጉት።

የሩስያ አብዮት ከሰከነ በኋላ የቦልሸቪስት መንግሥት የተሰበሰቡትን ሰነዶች ከርሸና ለተረፉት ለቄሣሩ ዘመድ ለዱክ እስክንድር አስረከባቸው። ዱኩ ሰነዶቹን የፔትሮግራድ ዩኒቨርስቲ የሕግ መምህርና በሔግ ፍርድ ቤት ዳኛ ለነበሩት ባሮን ኖልድ መርምረው እንዲበይኑ ሰጡአቸው።

ባሮን ኖልድ ፍርድ ለመስጠት የመረመሩአቸው ሰነዶች የሚከተሉት ናቸው።





- የቱርክ ካሊፋዎች፣ ፓሻዎችና ሡልጣኖች በልዩ ልዩ ጊዜያት የኢትዮጵያን የንብረት ባለቤትነት መብት አረጋግጠው ያወጡአቸው ድንጋጌዎች።
- መንገደኞች ከአሥራ ስድስተኛው እስከ አሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመናት ስለ ጉዞአቸው ከደረሱአቸው መጻሕፍት ውስጥ የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች የሚመለከቱት ክፍሎች።
- በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ከታወቁ ሰዎች ስለ ንብረቶቹ ባለቤትነት የተሰበሰቡ አስተያየቶች።
- በኢየሩሳሌም የታወቁ የሃይማኖት መሪዎች የግሪክ ፓትርያርክ፣ የማሮናይት ቤተ ክርስቲያን ቄስ፣ የአርመን ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ቄስና የላቲን ጵጵስና ጽ/ቤት አስተዳዳሪ የሰጡአቸው የምስክርነት ቃላት።
- የታወቀው የኢጣልያን ደራሲ ፔትሮ ዴላ ቻፔል በ1650 (እ.አ.አ) ከደረሰው መጽሐፍ ውስጥ የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች የሚመለከተው ክፍል።
- አባ ዱብዳ የተሰኙ ካህን በ1661 ዓ.ም (እ.አ.አ) ስለ ኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች ያዘጋጁት ጽሑፍ።
- አቡነ ሚክሊን «ስለ ቅዱሳት መካናት» ከተሰኘው መጽሐፋቸው ስለ ኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች የሚመለከተው ክፍል።
- አባ ዶሚኒክ ዛኔኪያ «የዛሬይቱ ፍልስጥኤም» በሚል ርዕስ የደረሱት መጽሐፍ።
- ኤፍ.ቪ.ቪርዲ ዱ ቪርና «የቅዱሳት መካናት ጥያቄ» በሚል ርዕስ በ1903 ዓ.ም (እ.አ.አ) ያደረጉት የምርምር ውጤት።
- አፄ ምንልክ በ1897 ዓ.ም ወደ ኢየሩሳሌም የሰደዱት የልዑካን ቡድን ከጀኔራል ጂጂ ማቻ ሂቻቻ በኢየሩሳሌም በቋሚነት ተመድበው ለነበሩ የሃይማኖት መሪዎች ላቀረቡላቸው መጠይቆች የሰጡአቸው መልሶች።
- አፄ ምንልክ የንብረቶቹ ባለቤትነት እንዲረጋገጥ በ1889 እና በ1900 ዓ.ም ለቱርክ መንግሥት ለጻፉአቸው ደብዳቤዎች የቱርክ መንግሥት እንደ ቱርክ ዘመን አቈጣጠር በ1325 የሰጠው መልስ።
- የኢየሩሳሌም ቅዱሳት መካናት ይዞታ አንድ ዓለም አቀፍ ጉባኤ ተቋቁሞ እስከሚወሰን ድረስ በነበሩበት እንዲቆዩ የሚደነግገውን የ1856 ዓ.ም (እ.አ.አ) የፓሪሱ ዓለም አቀፍ ስምምነት።
- የቱርክ መንግሥት ሡልጣን ዳግማዊ መሐመድ 1808–1839 ዓ.ም (እ.አ.አ) የዓለም አቀፍ ስምምነት በመቀበል በ1834 ዓ.ም (እ.አ.አ) ያወጡት ድንጋጌ።
- ሡልጣን መሐመድን የተኩት ሡልጣን አብዱል መጂድ በ1841 ዓ.ም (እ.አ.አ) የመሐመድን ድንጋጌ ያጸደቁበት ሰነድ።

ባሮን ኖልድ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትንና ሌሎችም ለጉዳዩ አግባብ ያላቸውን ሰነዶች መርምረው የሚከተለውን ፍርድ ሰጡ።

«የኢትዮጵያ የዴር ኤል ሡልጣን ገዳም ባለቤትነትም ጥንታዊና በእርግጥ ከ1834 እና 1841 ዓ.ም (እ.አ.አ) በፊት ለመሆኑ በቂ ማስረጃ አቅርቤአለሁ።»

«እኔ እንደ ተረዳሁት የኢትዮጵያውያን የዴር ኤል ሡልጣን ገዳም ባለቤትነት ጥንታዊ በእርግጥ ከ1834 ዓ.ም እና ከ1841 ዓ.ም (እ.አ.አ) በፊት ለመሆኑ በቂ ማስረጃዎች መርምሬአለሁ። ባለቤትነቱ ሙሉ ሆኖ ከገዳሙ ጋር ተያይዘው በሚገኙ መቅደሶች መከልከልና የበሮቹን ቁልፎች መያዝን ይጨምራል።»

«የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በ1838 ዓ.ም (እ.አ.አ) በ1862 እና በ1890 ዓ.ም (እ.አ.አ) የኢትዮጵያውያኑን መብት በመንካት ነባሩን ይዞታ በተደጋጋሚና በግብታዊነት ለመለወጥ ሙከራ አድርገዋል። እነዚህ የመብት መዳፈር ድርጊቶች ስለሆኑ ፍትሐዊ እርምጃ ተወስዶ ሙሉ በሙሉ መታረም አለባቸው። የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ነባሩን ይዞታ ሲለውጥ የቱርክ መንግሥት በቸልታ የተመለከተው ቢሆንም የኢትዮጵያውያኑ መብት ሙሉ የማያጠያይቅና የማይገሠሥ ነው።

በመደምደሚያም በፍልስጥኤም የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ የዴር ኤል ሡልጣን ገዳምና ከዚያው ጋር ተያይዘው የሚገኙት መቅደሶች ብቸኛ ባለቤት ከመሆኑም በላይ በበሮቹና በቁልፎቹ ጭምር በብቸኝነት መጠቀም የሚችል መሆኑን አምኜበታለሁ።»

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ፍርድ በማያሻማ መልክ የኢትዮጵያን የባለንብረትነት መብት አረጋግጦአል። ፍርዱ የተሰጠው ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ባለው ግለሰብ ቢሆንም ወደፊት ላልተወሰነ ጊዜ ተቀጥሮ የተዳፈነው የባለቤትነት ክርክር በሚከፈትበት ጊዜ የኢትዮጵያን አቋም አጠናክሮ ለማቅረብ ጠቃሚ ማስረጃ ሊሆን ይችላል።





www.ethiopianorthodox.org

በአፄ ምንልክ ዘመነ መንግሥት ተጀምሮ በልጅ ኢያሱ ጊዜ የተደከመበት ጉዳይ መክኖ እንዳይቀር በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመን ከፍተኛ ትኩረት አልተለየውም። በንግሥት ዘመን የዓለም ፖለቲካ ሁኔታዎች መለዋወጣቸው ለጉዳዩ አዲስ ገጽታ ሰጠው።

## VI

በንግሥት ዘመን መንግሥታቸው የወለደው ሥርነቀል እርምጃ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ራስ ተፈሪ (በኋላ ቀ.ኃ.ሥ.) ለዓለም መንግሥታት ዋና ጸሐፊ መጋቢት 25 ቀን 1915 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች በኢየሩሳሌም የባለቤትነት መብት ያቀረቡት ጥያቄ ነው። ማኅበሩ ጉዳዩን ተመልክቶ ለመወሰን ሥልጣን ቢኖረውም የወሰደው እርምጃ አልነበረም። በሌላ በኩል ደግሞ በቅርብ ምሥራቅ በተደረገው የኃይል አሰላለፍ የኦቶማን ቱርክ መንግሥት ተፍረክርኮ ግብፅና ፍልስጥኤም በእንግሊዝ መንግሥት ቅኝ ግዛት ውስጥ መጠቃለላቸው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች በኢየሩሳሌም የባለቤትነት ጥያቄ በአዲስ መልክ ማቅረብን ጠየቀ። በዚሁ ጊዜ የኢትዮጵያና የእንግሊዝ መንግሥታት ግንኙነት ዳብሮ ብዙ በጋራ ጉዳዮች ላይ መነጋገርና መደራደር ጀምረው ነበር።

የእንግሊዝ መንግሥት በጣና ሐይቅ ላይ ግድብ ለመሥራት፣ በኬንያ፣ በሱዳንና በእንግሊዝ ሱማሌ ድንበሮች ለማሸጋሸግና ለማስተካከል ይጉተጉት በነበረበት ወቅት፣ የኢትዮጵያ መንግሥት አንድ የልኡካን ቡድን ወደ ኢየሩሳሌም ልኮ አንድ ጉዳዩን ለማየት ለተሠየመ ኮሚሽን እንዲያስረዳ ወሰነ። ይህንን ውሳኔ የሰሙት በኢትዮጵያ የእንግሊዝ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ሚስተር ራስል የቡድኑ ተልእኮ እንዲሳካ መንግሥታቸው ለኮሚሽኑ በእንግሊዝ መዝገብ ቤት የሚገኙ መረጃዎች ቢኖሩ ፈልጎ እንዲልክለት አሳሰቡ። ከዚህም አያይዘው የልኡካኑ ቡድን ተልእኮ ተሳክቶለት ከተመለሰ፣ ከአፄ ምኒልክ ዘመን ጀምሮ ድርድር ሲደረግባቸው በቆዩ በጣናና በወለዳ ጉዳዮች ላይ ስምምነት ለመድረስ አመቺ ሁኔታ ሊፈጥር መቻሉን ለመንግሥታቸው ነሐሴ 26 ቀን 1923 ዓ.ም (እ.አ.አ) በጻፉት ደብዳቤ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያን አቋም ለኮሚሽኑ የሚያስረዳ ሰባት አባላት ያሉበት ቡድን ወደ ኢየሩሳሌም ተላከ። የልኡካን ቡድኑ አባላት የሚከተሉት ነበሩ።

1. ደጃዝማች ገብረሥላሴ የመልእክተኞች መሪ
2. አቶ ፋሲካ ሀብተሚካኤል አባል
3. አቶ (በኋላ ብላቴን ጌታ) ኅሩይ ወልደ ሥላሴ አባል
4. መልአከ ገነት ተድላ የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ የንስሐ አባትና የቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር አለቃ አባል
5. ከንቲባ ገብሩ አስተርጓሚ
6. አቶ ጳውሎስ ሁለተኛ አስተርጓሚ
7. አቶ ዓለሙ ሀብተሚካኤል የመልእክተኞች ጸሐፊ

የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ወኪል ሳትልክ ስለቀረች የኢትዮጵያ ልኡካን ያለ ውጤት ከኢየሩሳሌም ተመለሱ። የእንግሊዝ መንግሥት ግብፆቹ ኮሚሽኑ ዘንድ ቀርበው አቋማቸውን እንዲገልጹ ተጽእኖ አላደረገባቸውም። በዚህ የተነሣ የኢትዮጵያ መንግሥት ለእንግሊዝ መንግሥት የነበረው በጎ አስተያየት ተለውጦ ግንኙነታቸው የመሻከር አዝማሚያ መያዙን ሚስተር ራስል ለመንግሥታቸው ባቀረቡት ዘገባ አስታውቀዋል።

## VII

አፄ ኃይለ ሥላሴ ከነገሡ በኋላ ጉዳዩ ሳይቆረጥ ጠላት ኢትዮጵያን ወረረ። ሀገሪቱ በጠላት ቅኝ ግዛት ውስጥ በመጠቃለልዋ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች በኢየሩሳሌም ባለቤትና አስታዋሽ አጥቶ ለአምስት ዓመታት ቆየ።

አፄ ኃይለ ሥላሴ ወደ አልጋቸው እንደ ተመለሱ በጦርነት የወደመባቸውን አገር ማቋቋምና አገሪቷም ከኢጣልያን ቀኝ ግዛት ወጥታ ወደ እንግሊዝ ጥገኝነት እንዳትገባ የሚታገሉበት የውጥረት ዘመን ስለነበረ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያ ቅዱሳት መካናት ንብረቶች በኢየሩሳሌም ባለቤትነት ጥያቄ ተራውን መጠበቅ ነበረበት። አገር መልሶ ማቋቋሙና ማረጋጋቱ ሥራ ቀና አቅጣጫ ሲይዝላቸው ከግብፅ መንግሥት ጋር የሚደራደሩባቸው ጉዳዮች የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ከግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ጥገኝነት አላቆ ራሷን ማስቻልና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች በኢየሩሳሌም የባለቤትነት መብት ማረጋገጥ ነበር።

ከነዚህ ሁለት ጉዳዮች መንግሥት ቅድሚያ የሰጠው ቤተክርስቲያንዋን ራስዋን የማስቻል ጉዳይ ነበር። ወትሮ እንደሚደረገው አያሌ ወርቅ፣ እንቁና ገንዘብ እየተከፈለ ጳጳስ ማስመጣት ቀርቶ ከፓትርያርክ እስከ ጳጳሳት ያሉትን የሃይማኖት መሪዎች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እርሷ መርጣ እንድትሾም ሥልጣን እንድታገኝ ማድረግ ነበር። ግብፆች በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላይ የነበራቸውን የሃይማኖት የበላይነት ፈርተው በምትኩ በእኩልነት ላይ በተመሠረተ የሃይማኖት ወንድማማችነት ለመቀበል ፈቃደኛ አልነሩም። የኢትዮጵያ መንግሥት በጥያቄው ከገፋበት ቤተክርስቲያንዋን ለማውገዝ አስፈራርተው ነበር። በኢትዮጵያ በኩል ግብፆች በሰላምና በፈቃደኝነት ስምምነት ላይ ለመድረስ የማይተባበሩ ከሆነ የመገንጠል እርምጃ ለመውሰድ መቁረጥዋን በልዩ ልዩ ዘዴ እንዲያውቁት ተደረገ። ግብፆች የኢትዮጵያ መንግሥትና ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ማምረራቸውን ተገንዝበው በ1940 ዓ.ም ለዘመናት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ላይ ተንሠራፍቶ የነበረውን «የሃይማኖት ቅኝ አገዛዝ» ለማንሣት ተስማሙ።

የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ራሷን ለማስቻል ቅድሚያ መስጠቱ ትክክል እርምጃ ነበር። የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች በኢየሩሳሌም ለመንጠቅ የምትጥረው የሃይማኖት የበላይነቷን መከታ በማድረግ ነበር። የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት በትዕግሥትና በዘዴ ከ1500 ዘመን በላይ የቆየውን «የሃየማኖት ቅኝ አገዛዝ» ገርስሶ ራሷን ማስቻሉ የንብረቶቹ ባለቤትነት በተለየ መልክ እንዲታይ ጠይቆአል።

በሌላ በኩል በተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ እስራኤል መፈጠሯ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች በኢየሩሳሌም የባለቤትነት ጥያቄ የሚደመጥበት አመቺ ሁኔታ ፈጠረ። ቀድሞ ፍልስጥኤምንና ግብፅን በየተራ ሲገዙ የነበሩት የቱርክና የእንግሊዝ መንግሥታት በ1852 ዓ.ም (እ.አ.አ) የቱርክ መንግሥት በ1758 ዓ.ም (እ.አ.አ) የነበረው ይዞታ እንዳይለወጥ የደነገገውን ከማስፈጸም ቻለ በማለት ለግብፅ ማድላታቸው አልቀረም ነበር።

ከ1940 ዓ.ም ጀምሮ አረብ አገሮች በግብፅ ግንባር ቀደም መሪነት የእስራኤልን ህልውና ሲፈታተኑ መቆየታቸውና በኋላም 1960 ዓ.ም በተደረገው ጦርነት እስራኤል አረቦችን አሸንፋ ምሥራቅ ኢየሩሳሌምን በግዛትዋ ውስጥ ማጠቃለልዋ የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች ባለቤትነት መብት ለማስከበር አመቺ ሆነ። በተጨማሪም እስራኤል ከኢትዮጵያ ጋር ለመደራደር የምትፈልገው የቤተ እስራኤሎች (ፈላሾች) ጉዳይ፣ ኢትዮጵያ በአፍሪካ መንግሥታት ማኅበር የነበራት ተደማጭነትና የመሪነት ሚና የኢትዮጵያ ጠረፍ ቀይ ባሕርን በከፊል ማጠቃለሉና ማስተላለፍ ማስቻሉ ተደምረው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች በኢየሩሳሌም በሀገሪቱ እጅ እንዲሆኑ ሲደረግ፣ የባለቤትነቱ የመብት ጥያቄ ላልተወሰነ ጊዜ ተቀጥሮ ተቀምጦአል።

## ማጠቃለያ

የኮሚኒዝም ሥርዓት መፍረክረክ ያስከተለው የኃይል አሰላለፍና የፖለቲካ ለውጥ እስራኤልና አረቦች ልዩነታቸውን በማቻቻልና በሰላም ተደራድረው እንዲፈቱ አስገድዶአቸዋል። በኢትዮጵያ በኩልም ጠንካራ የመደራደሪያ ነጥቦች የነበሩ የፈላሾች፣ የቀይ ባሕርና በአፍሪካም የነበራት ተደማጭነት እንዳልነበሩ ስለሆኑ እስራኤል የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች በኢየሩሳሌም ጉዳይ ከዚህ ቀደም እንደደረሳቸው በ1852 ዓ.ም (እ.አ.አ) የቱርክ መንግሥት ያወጣን ድንጋጌ ለኢትዮጵያ በሚጠቅም ግብፅን ግን በሚጐዳ መልክ ተርጉማ ታስፈጽማለች ብሎ መገመት የዋህነት ይሆናል።

እስራኤል ከሌሎች የአረብ አገሮች ጋር ለምታደርገው ድርድር የግብፅ ሚና በቀላሉ የሚገመት አይደለም። በፖለቲካ ዓለም በነፃ የሚሰጥ ድጋፍ ወይም ዕርዳታ የለም። ለሁሉም ነገር ዋጋ አለው። ግብፅ የእስራኤልን ህልውና በስምምነት ለማረጋገጥ ለምታበረክተው ድጋፍ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች በኢየሩሳሌም ባለቤትነት ጉዳይ መደራደሪያ ልታደርገው የምትችል መሆንዋ ሊዘነጋ አይገባም። አይሁዶቹም ጉዳዩን ከአገራቸው ጥቅም አኳያ የማይመለከቱበት ምን ምክንያት ይኖራል?

ስለዚህ በኢትዮጵያ በኩል ከወዲሁ እነዚህን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የፌደራሉ መንግሥት፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንና የኢየሩሳሌም ድርጅት በአንድ ወጥ መረጃዎችን ማሰባሰብና ሙግቱ በሚከፈትበት ጊዜ ስለሚወሰደው እርምጃ ስልት መቀየስ ይኖርባቸዋል።

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ንብረቶች በኢየሩሳሌም ተጠቃሚዎች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ቢሆኑም፣ በሌላ ገጽታቸው ሲታዩ ልክ እንደ ላሊበላ አብያተክርስቲያን፣ እንደ አክሱም ሐውልት ወዘተ. የኢትዮጵያ ሕዝብ ቅርሶች በመሆናቸው ከላይ የተጠቀሱት አካላት የንብረቶቹን ባለቤትነት ለማረጋገጥ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያስፈልገውን ድጋፍ መስጠትና መተባበር ይኖርበታል። ❑



www.ethiopianorthodox.org

# ባህላዊ የቤተ ክህነት ትምህርት ከየት ወዴት?

ዶ/ር ኃይለ ገብርኤል ዳኜ

## ሀ. አመጣጥና ዕድገት

ከአክሱም ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ክርስትና ከሰሜን ኢትዮጵያ ወደ መሐልና ደቡብ ሲስፋፋ አድባራትና ገዳማት፣ በየተራራዎቹና ሸለቆዎቹ በብዛት እየተመሠረቱ መጥተዋል። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ እነዚህ አድባራትና ገዳማት ብዙ ንብረትና ሀብት ያካበቱ፣ ብዙ ሕዝብ የሚያስተዳድሩና የሚያስተምሩ ተቋማት ነበሩ። ከመሐል ምሥራቅ የተገኙ ቅዱሳን መጻሕፍት፣ በግእዝ ተገልብጠው እንዲስፋፉ አድርገዋል። እግዚአብሔርን ለማወደስ ዜማዎችና ቅኔዎች በየዘመናቱ ፈጥረዋል፤ አስፋፍተዋል። በየጊዜው የፈለቁት የቅዱሳንና የአበውን ተጋድሎ የሚገልጹ እምነታቸውን የሚያበሥሩ ብዙ ጽሑፎች እንዲጻፉ አድርገዋል።

እነዚህን ጽሑፎች ለሕዝብ የሚያስተምሩ በቅዳሴ፣ በዜማ፣ በቅኔ፣ እግዚአብሔርንና ቅዱሳንን በየአድባራቱ የሚያወድሱ ምሁራንን ለማፍራት ንባብ ቤት፣ ቅዳሴ ቤት፣ ዜማ ቤት፣ ቅኔ ቤት፣ እየተባሉ የታወቁ ትምህርተ ሥርዓት አዳብረዋል። እነዚህ ትምህርት ቤቶች ብዛት ያላቸው ስሞነኛ፣ ደብተራ፣ ሊቃውንት፣ ካህናት፣ የገጠር የአድባራትና ገዳማት መሪዎችን አፍርተዋል። የአገሬውም ወጣት በነዚህ ሊቀምሁራንና ሊቃውንት ቦታ ለመተካት ወደየአድባራቱ እየጐረፈ ከንባብ እስከ ዜማ፣ ቅኔና መጻሕፍት የተከማቸውን እውቀት ለመቅሰም ይንከራተቱ ነበር። የዛሬን አያድርገውና የገጠርም ሕዝብ ባህል አድርጎት ተማሪን ይመግባል፤ ይደግፋል። ትምህርቱን ሲጨርስ ማዕርግ የማግኘት ዕድል ወጣቱ ይታየው ነበር። በየአድባራቱ አገልግሎ መሪጌታ፣ ቀኝ ጌታ፣ ግራጌታ፣ አለቃ፣ መምህር መሆን ይመኝ ነበር። ይሆንለትም ነበር። ምኞቱ ማዕርግ ማግኘት ብቻ አልነበረም። ከማዕርጉ ጋር የሚሄድ ክብርን የሚያጐናጽፍ የአገልግሎት ወይም የሹመት ቦታ ነበረው። ከአገልግሎት ቦታው ጋር የተያያዙ እንደ ደሞዝ የሚሰጥ ርስትና ጉልት ወይም ማደሪያ መሬት ይገኝ ነበር። የሰሞነኛ መሬት፣ የቁስ ገበዝ መሬት፣ የአለቃ መሬት፣ የመሪጌታ መሬት ወዘተ. ይገኝ ነበር።

ከዚህም አልፎ ከመኳንንቱ፣ ከመሳፍንቱና ከንጉሠ ነገሥቱ ዙርያ በጽሑፍ ሥራ በማገልገል በዳኝነት በመሠማራት፣ ማዕርግና ክብር እንዲሁም ማደሪያ መሬት የማግኘት ዕድሉ ብሩህ ሆኖ ይታየው ነበር።

ከዚህ የተነ ሣም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ፣ በተለይም እስከ ጣልያን ወረራ ድረስ፣ የቤተ ክህነት ባህላዊ ትምህርት እጅግ ዳብሮ ብቸኛ የእውቀት ምንጭ ሆኖ ታይቶአል።

ከዚያ ወዲህ ምን ተፈጠረ? የሚከተሉትን ክስተቶች እስቲ እንመልከት።

## ለ. ዘመናዊ መዋቅራዊ ለውጦች ያስከተሉት ውድቀት

1. አፄ ኃይለ ሥላሴ ከአልጋ ወራሽነት ጊዜ ጀምሮ ማዕከላዊ አስተዳደር አቋቁመው የመኳንንትና መሳፍንት ግዛቶችን በቁጥጥራቸው ሥር ሲያደርጉ፣ በአንጻሩ አድባራትንና ገዳማትንም በማዕከላዊ ቁጥጥር ሥር እንዲውሉ አድርገዋል። ጣልያን ቤተ ክርስቲያናትን ለመቆጣጠር እንዲያመቸው «መንፈሳዊ ጉባዔ» የቤተ ክህነት ማዕከላዊ አስተዳደርን አቋቋመ። ከጣልያን ወዲህ አፄ ኃይለ ሥላሴም ይህን ፈለግ በመከተል የቤተ ክህነት ማዕከላዊ አስተዳደር በክፍለ ሀገርና አውራጃ ድረስ እንዲጠናከር አደረጉ። ጳጳሳትም ከማዕከል እስከ ክፍለ ሀገር ሲሾሙ አድባራትና ገዳማት በቁጥጥራቸው ሥር ዋሉ። በየጊዜው የሚሾሙት የአድባራት መሪዎች በአመዛኙ መነኮሳት ነበሩ። ደብተሮችና መሪ ጌታዎች በዕልቅና በቤተ ክህነት አመራር የመውጣት ዕድላቸው እየተጣበበ መጣ።
2. በየአድባራቱ የነበረው የሊቃውንት ክምችት አፄ ኃይለ ሥላሴ ባዋቀሩት ማዕከላዊ አካባቢ አስተዳደር ሥር፣ በጽሕፈት ሥራ፣ በፍትሕና እንዲሁም በዘመናዊ ትምህርት ቤቶች ቋንቋና ታሪክ ግብረ ገብ አስተማሪነት ለመቀጠር እየጐረፉ ወደ ከተሞች መጣ። ይህም በየአካባቢው ያሉትን አድባራት አዳከማቸው። ለመሆኑ ባህላዊ ትምህርት ቤቶቹ ሊቃውንቱን እየተከተሉ አልሄዱምን? ይባል ይሆናል። ይህ እንደሚከተለው ግልጽ ይሆናል።
3. የከተሞች መስፋፋት የባህላዊ ትምህርት ቤቶችን ዕድገት ቀጭቶአል። እንደ አዲስ አበባ ያሉ ከተሞች ሲስፋፉ በነዚህ ከተሞች ብዙ ታላላቅ አድባራት ተመሥርተዋል። እነዚህም አድባራት የገጠሩን አድባራት ሊቃውንት ተሻሙ። መኳንንትና መሳፍንቱ ዓይናቸው ከተሞች ላይ ዓረፈ። የከተማ አድባራትም



YOUR ENJOYMENT IS OUR SATISFACTION



ገደራ ሆቴል
GEDERA HOTEL
Tel : 251-1-531900- 533894/95
Fax: 251-1-533893
P.O.Box 31452
Addis Ababa - Ethiopia

NEED A PACKAGE DELIVERY COMPANY YOU CAN RELY ON?

UNITED PARCEL SERVICE
H. MAYLER PLC
P.O.BOX 41519
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
TEL: 251-1-615808/621308
FAX: 251-1-615808



If your looking for a package delivery company you can rely on, here's something for you to consider

UPS has more custom-built vehicles around the world, more conveniently-located facilities around the world and more dedicated people around the world than any other package delivery company

So if you want to be sure your next important package gets where it's supposed to be when it's supposed to be there, why in the world would you send it with anyone but UPS?

Consider it done.

Http://www.ups.com

በስታር ቴክኒካል ትሬዲንግ ኃ.የተ. የግል ኩባንያ
የአዲስ ጋዝና ፕላስቲክ ፋብሪካ

ደንበኞቻችን በነባር አገልግሎት ስጦታችን ያውቁናል። ለዚህም ማረጋገጫው ፀሐይና ዝናብ ቅዝቃዜና ሙቀት ቢፈራረቅባቸው የማይሰነጣጠቁ የፕላስቲክ ወንበሮችን በክፍትም ሆነ



በዝግ መጋዘን ሊከማቹና ሊሰካኩ የሚችሉ የፍራፍሬ፣ የዳቦ፣ የአሣ፣ የሥጋ እንዲሁም የአልኮል፣ የወይን ጠጅ እና የቢራ ጠርሙስ መያዣ ሣጥኖችን እያመረትን በጅምላም ሆነ በችርቻሮ እንሸጣለን።

በተጨማሪም ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ለድራፍት ቤቶች፣ ለብዮዳና ለለስላሳ መጠጥ እና ለምግብ ማሽጊያ የሚያገለግል የካርቦን ዳይኦክሳይድ ጋዝ እምርቱን እንሸጣለን

ጎብኙን!!!

አድራሻችን፡ አዲስ አበባ ወረዳ 21 ቀበሌ 04
የስልክ ቁጥር 15 86 48፣ 51 98 99
የመልዕክት ሣጥን ቁጥር 2407
አዲስ አበባ



www.ethiopianorthodox.org

ኢስት አፍሪካን ትሬዲንግ ሐውስ ለሚትድ
EAST AFRICAN TRADING HOUSE LTD




የኢስት አፍሪካን ሆልዲንግስ አባል ኩባንያ
Member of East African Holdings

ስልክ 760920,760919 ፋክስ 763062 E-mail: eaethiopia@telecom.net.et




ስም ያለው ትምህርት ቤት አቋቁመው ሊቃውንት አላፈሩም። ያቋቋሟቸው «ቄስ» ትምህርት ቤቶች ለዘመናዊ ትምህርት ቤት መጋቢ ከመሆን እምብዛም አላለፉም። በዛሬው ጊዜ ታላላቅ አድባራት ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመወዳደር እንደ ካቶሊኩ ካቴድራል ዘመናዊ ትምህርት ቤት ለመገንባት ያልማሉ ይጥራሉ እንጂ ለጥንቱ ትኩረት አይሰጡም።

4. ከጣልያን ወረራ ወዲህ የዘመናዊ ትምህርት ቤቶች በየከተማው በገፍ ሲመሠረቱና እነዚህም ከድሮው ጋር ሲነጻጸር እጅግ በርካታ በየሙያው የተማሩ ወጣቶች ማፍራት ቀጠሉ። አዲሱን ዘመናዊ ትምህርት የቀሰመው ወጣት በአፄ ኃይለ ሥላሴ አስተዳደር ሥር የተሰገሰጉትን ደብተሮችና ሊቃውንት ከፍትሕ አስተዳዳር ሳይቀር እየተኩአቸው ሄዱ። የተሻለ የመቀጠር ዕድል ከባህላዊ ትምህርት ይልቅ በዘመናዊው የተማረ ሆኖ ታየ። ይህም ባህላዊ ትምህርት «አያበላም» የሚል ስሜትን አስከተለ።

5. ማዕከላዊ ቤተ ክህነት ከአንደኛ ደረጃ እስከ ኮሌጅ ዘመናዊ ትምህርት ቤቶች በማቋቋም አትኩሮቱን ከባህላዊው ወደ ዘመናዊው ወሰደው። ለዘመናዊ ትምህርት ቤቶች የሚያወጣው ወጪ ለባህላዊ መምህራን ከሚያደርገው ድጎማ ጋር ሲነጻጸር፣ ለባህላዊው ትኩረት መንሣቱን በግልጽ ያሳያል።

6. ባለፈው ሶሻሊስት ሥርዓት መሬት በአራሹ ገበሬ ቁጥጥር ሥር ሲውል፣ ከባህል ትምህርት ቤት ተመርቀው በየአድባራቱና ገዳማቱ በማገልገል ማደሪያ መሬት የማግኘት ዕድል ጨለመ። ደጋፊዎቹ መኳንንቱ መሳፍንቱና ንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣናቸውን አጡ።

7. ባሁኑ ጊዜ (ከሩቅ) እንደምናየው የቤተ ክህነት ባህላዊ ትምህርት ቤቶች ደጋፊ ተንከባካቢ ያጡ ይመስላል። ቤተ ክህነትም ከባህላዊ ትምህርት ቤት ለየት ባለ መልኩ ካህናትን እያሠለጠነ ነው። ቤተ ክህነት ዛሬ የሚኮራበት የቤተልሔሙ፣ የዋሸራው፣ የዲማው ዓይነቱ ሳይሆን በፈረንጁ ሥርዓት በተገነባው መንፈሳዊ ኮሌጅ ነው።

## ሐ. የባህላዊ ትምህርት ቤት ዕድል ምንድነው?

1. አሁንም በየአድባራቱ አልፎ አልፎ ቢሆንም እንደ ድሮው «ባያበላም» ጥንታዊው ባህላዊ ትምህርት በተመናመነ መልኩ እየተካሄደ ነው። ከምክንያቶቹ አንዱ ቅዳሴ፣ ዜማና ቅኔ ለየአድባራቱ አገልግሎት አሁንም ቢሆን ይፈለጋል። ስለዚህ ቅዳሴ፣ ዜማ፣ ቅኔና አቋቋም በትላልቅ አድባራት ሲማሩት ይስተዋላል።

2. በባህላዊ ትምህርት ቤት ለመማር የሚፈልጉ ወጣቶች ከድሮው በተለየ ምክንያት አሁንም ይገኛሉ። የገጠር ሕዝብ ኑሮ አሽቆልቁሎአል። በድርቅና በተፈጥሮ መዛባት ምክንያት የገጠሬው ምርት በማሽቆልቆሉ የገበሬው ልጅ በውትድርና ካልሆነም በድቁናና በክህነት ተሠማርቶ ከግብርና ኑሮ ለመገላገል ይፈልጋል። ሆኖም አራሹ ገበሬ እንደ ድሮው ተማሪዎችን መመገብ ስለማይችል ባህላዊ ትምህርት ቤት ድጋፍ ካላገኘ መቀጠል ይሳነዋል።

3. ከዘመናዊ ትምህርት ቤት ወድቀው ወይንም ጨርሰው በርካታ ወጣቶች የሥራ ፈቱን መደብ እየተቀላቀሉ ይገኛሉ። ዘመናዊ ትምህርት እንደ ተባለለት በዛሬው ጊዜ ለቅጥር ለማዕርግ ላያደርስ ይችላል የሚል አስተሳሰብ በገጠር እየተስፋፋ ነው። ስለዚህ የቅጥር ተስፋው ለመነመነ ዘመናዊ ትምህርት ከገጠር ወደ ከተማ ለብዙ ዘመናት ከመኳተን በአቅራቢያ ባለው ባህላዊ ትምህርት ቤት ለመማር የሚፈልጉ መኖራቸው ታውቆአል።

በትላልቅ አድባራት እንደ ቤተልሔም ባሉት ባህላዊ ትምህርት የሚማሩት ዛሬ አንድ ተስፋ አላቸው። ይህም ተስፋ በገጠር ቤተ ክርስቲያናት ሄደው ማገልገል አይደለም። ገጠር ቤተ ክርስቲያን በአመዛኙ ሊደግፋቸው አይችልም። የገጠር ቤተ ክርስቲያናት፣ አድባራት እየተዳከሙ ሲሄዱ በአንጻሩ የከተማ አድባራት እያበቡ እየተስፋፉ መሄዳቸውን በገጠር ያሉት አድባራት ይመለከታሉ። ከተሞች የባለሀብቶች መናኸሪያ እንደ መሆናቸው አድባራት ከቅድመ አብዮት እጅግ በበለጠ መልኩ በሕዝብ ድጋፍ እየበለጸጉ ነው። እነዚህ የከተማ አድባራት ለገጠር ባህላዊ ትምህርት ቤቶች ትልቅ ተስፋ ሆነዋል። በገጠር አድባራት ዜማ፣ ቅኔና አቋቋም ተምሮ በየከተሞቹ ባሉት አድባራት ለመቀጠር ሥራ ፍለጋ ወደ ከተሞች መጓዝ ተጀምሮአል።

የከተማ አድባራትም የገጠር ቤተ ክርስቲያናትን እንርዳ በማለት ምዕመናንን ሲቀሰቅሱ ይሰማሉ። በዚህም መሠረት የከተማው ሕዝብ ለገጠር አድባራት አክብሮቱን በብዙ መልኩ እየገለጸ ነው። ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ የመጣው «መንፈሳዊ ጉዞ» እንቅስቃሴ ለዚህ አንዱ ምሳሌ ነው። በየከተማው ምሁራንና ምዕምናን እንደ ወርቅ ጉር ያለ አድባራትን ለማገልበት እንቅስቃሴ ሲያካሂዱ ይታያል።

የባህል ትምህርት ቤቶችን ለመርዳት ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን የኢትዮጵያ ወዳጅ በሆኑት ጀርመናዊ ፕሮፌሰር ሐየር በጀርመን አገር ከሃያ ዓመት በላይ ለባህላዊ ትምህርት ቤት ደሞዝና አበል በመስጠት የሚንቀሳቀሰው የ«ታቦር ሶሳይቲ ነው»። ለተወሰኑ ትላልቅ አድባራት መምህራንና ተማሪዎች በየወሩ አበል ይከፍላል።

በየከተሞች ያሉ አድባራት ምሁራን የዚህን ጀርመናዊ ማኅበር አርአያ መከተል ይችላሉን? እስኪ ይታሰብበት። ❑




www.ethiopianorthodox.org

# ማኅበራዊ ሕይወት በተጉለት ወግዳ

ከዶ/ር ያሬድ አግረ

## መልክአምድራዊ አቀማመጥ

ወግዳ፣ በተጉለት አውራጃ በስተምዕራብ በሸዋ ሜዳማ ወሰን ላይ የሚገኝ አምባ ነው። በምዕራብ በጫጫና በምሥራቅ በበሬሳ ወንዝ ሸለቆ የተከበበ በአንዳንድ አካባቢዎች አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ጠበብ ያለና በሌላው በኩል ሰፋ ያለ ሜዳ ነው። ነዋሪዎቹ በቀጥታ ወደ ወንዞች በሚያቆለቁሉት ተራሮች የሰፈሩ ናቸው። ከአንድ ገደል ጫፍ ላይ በመቆም እስከ አድማሱ መጨረሻ ሲመለከቱት ትዕይንቱ ተራ በተራ ሜዳማና የወንዞች ሸለቆ የሚደጋገምበት ሆኖ ይታያል።

ከደብረ ብርሃን ወደ ወግዳ የሚወስደው መንገድ ጥርጊያ ሲሆን፣ ወግዳን መሃል ለመሃል በማቋረጥ ርዝመቱ ከ45 ኪሎ ሜትር በላይ ይሆናል። የመንገዱ ግራና ቀኝ በመስኮች የተከበበ ሲሆን፣ ከመስኮቹ በታች የወንዝ ሸለቆ ይታያል። መልክአ ምድሩም ምንጊዜም በዙሪያው በማይታጡት የባሕር ዛፍ ተክል የተከበበ፣ እንደ ነጠብጣብ በሚታዩ የሣር ወይም የቆርቆሮ ቤቶች የተሸፈነ ነው። አልፎ አልፎ በመጠን ጎላ ያሉ ዙሪያ ክብ የቆርቆሮ ጣራ ያላቸውና በድንጋይ የተሠሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተክርስቲያን ይታያሉ። ከነዚህ ለየት ብላ የምትታየው ደግሞ፣ ከ1500–2000 ቤተሰቦችን የሚያገለግለው የአስተዳዳር ቢሮ፣ የሸቀጣ ሸቀጥ መደብሮችና የእህል ወፍጮ ቤት ያለው የኅብረት አገልግሎት፣ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና ከሃምሳ በላይ የሆኑ መኖሪያ ቤቶች ያላት ጎሽ ባዶ የተባለችው ከተማ ናት። ጎሽ ባዶ ከደብረ ብርሃን 20 ኪሎ ሜትር ያህል ስትርቅ፣ ከከተማዋ ትይዩና ከመንገዱ ባሻገር ቀድሞ የሬድ ባርና ልማት ድርጅት አሁን የነርሶች ማሠልጠኛ የሆነው ቢሮና የሠልጣኞች መኖሪያ ይታያል።

በሸለቆውና በሜዳው ላይ ለም መሬቱን ተከትለው የሚኖሩ ቤተሰቦች ተበታትነው ሰፍረዋል። ቤቶቻቸው በጭቃና ጭድ በተጣበቁ ድንጋዮች የተገነቡ ክብ የሣር ጎጆዎች ናቸው። ቤተሰቦቹ ጎጆአቸውን መኝታ ቤት፣ ማዕድ ቤትና የእንስሳት ማደሪያ አድርገው ባንድ ላይ ይጠቀሙበታል። በሀብት የደረጁት ቤተሰቦች ደግሞ የቆርቆሮ ክዳን ያላቸው ቤቶች በመሥራት ለየት ብሎ የተሠራ መኝታ ቤትና ማዕድ ቤት አላቸው። መኖሪያ ቤቶቹን ከአውሬና ከሌባ ለመከላከል፣ ከላይ ከባሕር ዛፍ አጠናዎች፣ ከታች በድንጋይ የተገነባ አጥር አላቸው። ከሸለቆው ከፍታ ላይና ከየስርቻው ጉርንዳ ቦታዎች ላይ ካሉት ኮረብታዎች ጎን 600 ሜትር ካሬ የሚሆን የእርሻ ማሳዎች ይታያሉ። ቀጥ ካለው ተዳፋት ላይ ተደላድለው የሚያርሱት ገበሬዎችና በሬዎቻቸው የሚያስደንቁ ናቸው።

ገበሬዎቹ በየቀኑ ወደ እርሻቸው ደርሶ መልስ ለሚያደርጉት ጉዞ በሸለቆው ጥግ እየተጠማዘዘ የሚያስኬድ መንገድ አበጅተዋል። የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ጥናቱን በሚያከናውንበት ወቅት፣ ከሚያድርበት ሜዳማ ቦታ ቁልቁለቱን እየወረደ፣ አቀበቱን እየወጣ ሲመላለስ፣ ጉዞው የጠየቀውን ችግርና ይህንንም ለመቋቋም ያደረገው ጥረት ከባድ ቢሆንም፣ በሌላ ወገን ደግሞ ጠና ያሉ ሴቶችና ወንዶች ሸክም ይዘው ቀልጠፍ ብለው ሲቀድሙት መገረሙን ያስታውሳል። «አቀበቱ የሚጣደፈውን ጉረምሳ ያደክመዋል፣ በዝግታ የሚራመደው ሽማግሌ ግን ያሸንፈዋል» የሚለውን የአገሬውን ብሂል ከሰማ በኋላ ግን ችግሩን ለመረዳት አስችሎታል።

## የአየር ጠባይ

በወግዳ የደጋውና የወይና ደጋው ሙቀት በ12 እና በ20 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ መሃከል ከፍና ዝቅ ይላል። ክረምቱ በዋና ዋናዎቹ የእርሻ መሬቶች ላይ ቀዝቃዛ ሆኖ ዝናቡ በዓመት እስከ 1000 ሚሊ ሜትር ይደርሳል። የዝናቡ መጠን በመኸር ወቅትም እየዘነበ ሰብል የሚሰጥበትም ጊዜ አለ። የሰብሉ ሁኔታ እንደ መሬቱ ከፍታና ዝቅታ ይለያያል። እስከ 2750 ሜትር ከፍታ ካለው ከደጋው ይልቅ ወይና ደጋው የበለጠ አዝርዕት ያበቅላል። ወግዳ በአብዛኛው ደጋና ወይና ደጋ ሲሆን የተቀረው ቆላ ነው። የላይኛው ደጋ ሜዳ ውኃ አዘል አፈር ይበዛዋል። ዝቅተኛው ቦታ እጅግም ፍሬ ስለማይሰጥ ለከብት ርቢ አመቺ ነው።




## ግዮን ኢንደስትርያልና ኮሜርሽያል

(ግኢኮ) ኃ/የተ/የግ/ማ

ሰምና ቡና ለውጭ ገበያ በማቅረብ፣ በላኪነት፣ በትራንስፖርት አገልግሎትና ኬሚካል በማምረት ሥራ የተሰማራና የተደራጀ ኩባንያ ነው።

- ግኢኮ - በ52 አዳዲስ ከባድ ስካንያ፣ ኢቬኮና ቮልቮ በባለተሳቢ ተሽከርካሪዎች በመታገዝ የተቀላጠፈ የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል፤
- ግኢኮ - ሠፊፍ አቅልጦና አጣርቶ ሰም ለውጭ ገበያ በማቅረብ አንደኛ ደረጃነትን ስለያዘ ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች ሠፈፋቸውን ሲያቀርቡለት በጥሩ ዋጋ ይገዛል፤
- ግኢኮ ልዩ ልዩ ዕቃዎችን በተለይ ጨው፣ ጎማ፣ የመኪና መለዋወጫዎች፣ ሳሙና እና ልዩ ልዩ የሸቀጠ ዕቃዎች ከውጭ ስለሚያስመጣ ለማከፋፈል እንዲሁም በችርቻሮ ለመሸጥ የሚፈልጉ ግለሰቦችንም ሆኑ ድርጅቶችን ያስተናግዳል፤
- ግኢኮ - በቅርቡ አስተማማኝ ጥራት ያለው በረኪና ማምረት ስለጀመረ ለማከፋፈል እንዲሁም በችርቻሮ ለመሸጥ የሚፈልጉ ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የሚፈልጉትን ለመግዛት ይችላሉ፤

ደንበኞቻችን የሞቀና ከልብ የሚያስደስት መስተንግዶ ይጠብቃቸዋል።

አድራሻችን፤

ግዮን ኢንደስትርያልና ኮሜርሽያል ኃ/የተ/የግ/ማ
አዲስ አበባ - ወረዳ 25 - ቀበሌ 01 - የቤት ቁጥር 1037
ስልክ፡ 752237፣ 752602፣ 793063
ፋክስ፣ 755211፣ 504685
Email: GHION.&IND&COM.@telecom.net.et

የአለኝታዎ ማህተም
የአንድ ኢንሹራንስ ትልቅነቱ ፣ አስተማማኝነቱ፣
ካሳ የመክፈል ችሎታው ፣ ፍጥነቱ፣
የደንበኛን አለኝታ ማስከበሩ ፣ ተመራጭነቱ ! !
ለማናኛውም የኢንሹራንስ ፍላጎትዎ
እናስታውስዎ ! !

ኒያላ አለልዎ !

☎

| አዲስ አበባ | | ክፍለ ሀገር | |
|---|---|---|---|
| በቅሎ ቤት | (01)654585/653605 | አዋሳ | (06)201749 |
| ቦሌ | (01)533353/533636 | ባሕር ዳር | (08)201718 |
| ጎላ ሰፈር | (01)555501/02 | ድሬዳዋ | (05)110408 |
| ቄራ | (01)651792 | ደሴ | (03)112942 |
| | | ጂማ | (07)110706 |
| | | መቀሌ | (03)401111 |
| | | ናዝሬት | (02)113399 |

ፋክስ (251-1) 533541/340474 ፖ.ሣ. ቁ. 12753
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
E-Mail: nisco@telecom.net.et

ኒያላ ኢንሹራንስ አ.ማ.





www.ethiopianorthodox.org

በወግዳ፡ በማናቸውም አማሮች ዘንድ እንዳለው ሁሉ፡ ቤተሰብ፡ ባል፡ ሚስትና ያላገቡ ልጆቻቸው የሚሰባሰቡበት ማዕከል ነው። አዲስ ጋብቻ የመሠረቱት ባልና ሚስት ጎጆ ወጥተው መኖሪያ ቤት በመሥራት ራሳቸውን ይችላሉ። በቤተሰብ ውስጥ ወንዶች ከሴቶች ይልቅ የበላይነት ቢኖራቸውም በአንድነት፡ በጋራና በእኩልነት ተሰባስቦ የመተዳደር ባህል ሰፍኖ ይታያል። የቤተሰብን ልዩ ልዩ ምጣኔ ሀብታዊ ተግባሮች በቅልጥፍና ለማከናወን የሥራ ክፍፍል ይደረጋል። የወንድ፡ የሴትና የልጆች የሥራ ድርሻ በግልጽ ይታወቃል። እያንዳንዱ ቤተሰብ ራሱን ቢችል የሚመረጥ ቢሆንም፡ የቤተሰቦች በዝምድናና በጉርብትና መረዳዳት የቁሳቁሶችን እጥረት ለመቋቋምና ድንገተኛ ችግርን ለመወጣት ከፍተኛ ሚና አለው።

## ጋብቻ

በዘር ቈጠራ በሰባት ትውልድ ውስጥ የማይዛመዱ ወንድና ሴት ጋብቻ ሊፈጽሙ ይችላሉ። ከጋብቻ ዓይነቶች በብዛት የተለመደው በተጋቢዎች ወላጆች ምርጫ የሚወሰነውና በመሬት ይዞታና ሀብት ረገድ በሕጋዊ እኩልነት የተመሠረተው «ሰማንያ» የተባለው የጋብቻ ዓይነት ነው። ሆኖም በአሁኑ ጊዜ ሴትና ወንድ አስቀድመው በመተዋወቅና በመፈቃቀድ ለጋብቻ የሚስማሙበት ሁኔታ እየተለመደ የመጣ ቢሆንም፡ መሠረታዊው የወላጆች ፈቃድና ስምምነት አስፈላጊ ነው።

በወላጆች በኩል ለጋብቻ ትኩረት የሚሰጣቸው መስፈርቶች ጠባይ፡ ትጋትና የወላጆች የዘር ሐረግ ነው። የመሬት፡ የከብትና የእህል ስጦታም ተፈላጊ መስፈርቶች ናቸው። ይህም ቢሆን በገቢ ምንጭ ረገድ ከቤተሰብ ቤተሰብ ልዩነት እንደ መኖሩ መጠን፡ «ካብትሽ በካብቴ» በሚል ስምምነት መጋባትም ተለምዷል። በሁለቱ ተጋቢ ቤተሰቦች በኩል ስምምነት ላይ ሲደረስ በሚደረገው ግንኙነት የወንዱ ወገን የሚሰጠው የከብት ቍጥር እንደ በሬ፡ በግ፡ እህልና ጥሬ ገንዘብ በቅድሚያ ይገለጻል። ከሴት ወገን በከብት እኩል፡ በእህል ደግሞ የወንዱን ግማሽ መስጠት ይጠበቃል። ይኸውም የጋብቻቸው ዘላቂነት ሲረጋገጥ የሚሰጥ ይሆናል።

አዲሱ ቤተሰብ መሬት የሚያገኘው ከቀበሌ ሹማምንት ሲደለደል ወይንም ከወላጆቹ ሲሰጠው ወይንም አባወራው መሬት ሲከራይ ነው። ከጋብቻ በኋላ የሚገኝ መሬትና ሀብት የጋራ ሆኖ በፍቺ ጊዜ ተካፍለው ይለያያሉ። ልጅ መውለዳቸው የጋብቻቸውን ጽናት ስለሚያመለክት ሀብታቸውንም አንድ ላይ ይቀላቅላሉ።

ሌላው የጋብቻ ስምምነት፡ አንደኛው ወገን ለሰማንያ ጋብቻ ብቁ ሀብት ሳይኖረው ሲቀር እንደ አገልጋይ ተቈጥሮ ከምግብና ከመጠለያ በተጨማሪ የዓመት ልብስና እህል ወይም በግ ከባለንብረቱ ይሰጠዋል። የዚህ ዓይነቱ ጋብቻ በማንኛውም ወገን ፍላጎት ሊቋረጥ የሚችል ሲሆን፡ በአንፃሩ ደግሞ ስምምነቱ የቀጠለ እንደሆን ወይም ልጅ የተወለደ እንደሆን ጋብቻው ቋሚ በመሆን ወደ «ሰማንያ» እንደሚሸጋገር በውል ይታወቃል።

## የቤተሰብ ግንኙነት

በአማራ ቤተሰብ፡ ባልና ሚስት ጋብቻቸው በውል የጸና ሆኖ፡ በእኩልነት የጋራ ሀብት እንደሚኖራቸውና ሴቶች መሬት እንደሚወርሱ ይታወቃል። በወግዳ ግን ወንዶች በቤተሰብ ውስጥ የበላይነት ሥልጣን ያላቸው መሆኑ አይካድም።

ባል በሴት እንቅስቃሴ ጣልቃ ሳይገባ በማንኛውም ረገድ ተሰሚነት አለው። ሴትም ምግብ አብስሎ የማቅረብና ሌሎች የቤት ሥራዎችን የማከናወን ኃላፊነት ሲኖራት፡ የውጭ ጉዳይ ኃላፊነቱን ለባል በመተው በመሃከላቸው ያለውን ልዩነት ታከብራለች። የግብር ክፍያ፡ የመሬት ክርክር፡ ከበላይ ሹም መመሪያ መቀበል የወንድ ድርሻ ነው። ከዚህ በላይ የተመለከተው አጠቃላዩ ሁኔታ ይሁን እንጂ፡ ግብይትን በሚመለከት በጋራ ውይይት እንደሚወሰንና የቤት ውስጥ አመራር ከፍተኛው ድርሻ ለሴትዋ እንደሚተውላት ይታያል። የጓሮ አትክልት፡ የዶሮ ርቢ እና የመሳሰለው የሴትዋ ኃላፊነት ነው። ወንድ ከብት የማርባት፡ የማገዶ እንጨት የማከማቸት፡ እህል የመሸጥ፡ ከሰል የማምረትና መሰል ሥራዎችን ያከናውናል። ሴቶች ደግሞ እንቁላል፡ አትክልት፡ ዶሮ፡ በቤት ውስጥ የተዘጋጀ መጠጥ፡ በመጠን አነስ ያለ እህልና የመሳሰሉትን በአቅራቢያቸው ወደሚገኙ ገበያዎች በመውሰድ ግብይት ያካሂዳሉ። ይህ ዓይነቱ የሥራና የኃላፊነት ሚና ልዩነት እንደ ሁኔታው ይለዋወጣል። ለምሳሌ የእያንዳንዳቸው የሥራ መጠን እንደ ወራቱ፡ ማኅበራዊ ግዴታው፡ እንዲሁም የሕፃን እንክብካቤ



ከሚያስከትለው የሥራ ድርሻ ጋር ተነጻጽሮ ማን የትኛውን ኃላፊነት እንደሚወስድ ተፅእኖ ይኖረዋል።

## ፍቺ

በወግዳ ለፍቺ ምክንያት የሚሆኑት በሀብትና በስሜት አለመጣጠም ሲሆኑ፡ ለምሳሌ በአንዱ ወገን ገንዘብ ወይም ንብረት ማባከን፡ ስንፍና፡ ዝሙት፡ ከጋብቻ ውጭ ልጅ መውለድ፡ አካል የሚያጎድል ሕመም፡ መሃንነት፡ እንዲሁም ሌሎች የቤተሰብን ሀብት ሊቀንሱ የሚችሉ ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ። አንዳንዴም በሴትዋ በኩል የገጠማትን ቅሬታ ለማስወገድ ስትል እነዚህን ምክንያት አድርጋ ትወጣና መብቷን ለማስከበር ለድርድር ትጠቀምባቸዋለች።

የፍቺ ውሳኔ ላይ የሚደረሰው ከሁለቱም ወገን በተመረጡ ሽማግሌዎች አማካኝነት ነው። አልፎ አልፎ ስምምነት ሳይገኝ ሲቀር፡ ጉዳዩ ለአቅራቢያው ወይም ለቀበሌ ፍርድ ቤት ውሳኔ ይቀርባል። ውሳኔው ፍች ከሆነ መሬታቸውን አብረዋቸው እንደሚቀሩት የቤተሰብ አባላት ብዛት ይካፈላሉ። ሆኖም መሬትና ልጆችን በሚመለከት ወንዶች የቤተሰቡ የገቢ ምንጭ ተደርገው ስለሚቈጠሩና ልጆችን ከእንጀራ እናት ለመጠበቅ የሚችሉ መስሉ ስለሚታመን ክፍፍሉ ለወንድ ሲያደላ ይታያል። ለምሳሌ፡ ቤተሰቡ ያለው ሀብት አንድ በሬ ብቻ ቢሆን፡ በሬው ለወንድየው ይቀርና በምትኩ ለሴት ተመጣጣኝ ጥሬ ገንዘብ ወይም ተለዋጭ ንብረት በማካካሻነት ይሰጣል።

ሴቷ በአቅራቢያው ለመኖር ከመረጠች የመሬት ድርሻዋን ትረከባለች። ዳሩ ግን ሌላ ጋብቻ ለመመሥረት ዕድሏ እንዲቃናላት ወይም በአማቾች አካባቢ ላለመኖር ፈቅ ብላ ትኖራለች። ባቅራቢያው እየኖረች እንደ ገና ሌላ ካገባች ግን በፍች የደረሳትን መሬት ለቀበሌው መመለስ ይኖርባታል። አንዳንድ ሴቶች፡ በተለይ በዕድሜ የገፉት፡ በተወለዱበት ቀበሌ አግብተው እንደሆነ የድርሻ መሬታቸውን ላለመልቀቅ ሲሉ እዚያው መኖርን ይመርጣሉ። ሴቶች ድርሻቸውን ከብት፡ እህልና ከቀረው ሀብት (ቤት) ግማሹን ይዘው ከተለዩ በኋላ እንደገና ሲያገቡም ይታያሉ። ❑

ትራቭል ኢትዮጵያ
TRAVEL ETHIOPIA
AND BE SEVEN YEARS YOUNGER



አገር ማስጎብኘት፡ ፎቶ ሳፋሪ፡ መኪና ማከራየት እንዲሁም ሌሎች ግልጋሎቶችን በተቀላጠፈ መልክ ለማግኘት ምርጫዎ ትራቭል ኢትዮጵያ ይሁን።

በሙያው የካበተ ልምድ ያላቸው ሰራተኞቻችን የደንበኞቻችንን ፍላጎት ለማሟላት ዝግጁ ናቸው።
አድራሻችን
ግዮን ሆቴል ቅጥር ግቢ ውስጥ።

የመ.ሣ. ቁጥር 9438
ስልክ፡ 251-1-510168/150040/150036/553767/121250
ፋክስ፡ 251-1-510200, 550897, 551276
ኢ-ሜይል፡ travelethiopia@telecom.net.et
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ



www.ethiopianorthodox.org

# የወርቅ ጉር ገዳመ አድኅኖ

## ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን

### ሥራና ልማት ኮሚቴ ዓላማ፣ ስልትና ክንውን

ፍሥሐ ኃይለ መስቀል (ዶ/ር)

## 1. መግቢያ

ወርቅ ጉር የመንደር ስም ነው። የሚገኘውም በሰሜን ሸዋ ዞን ከደብረ ብርሃን ከተማ 22 ኪ.ሜ ወደ ምዕራብ ወረድ ብሎ በበሬሣና በጫጫ ወንዞች መካከል በሚገኝ ወሸመጥ መሳይ ስፍራ ላይ ነው። አካባቢው ተጉለት፣ አንዳንዴም ወግዳ ይባላል። ተጉለት ወይንም ወግዳ እንደ አብዛኛው የሰሜን ሸዋ አካባቢ የተፈጥሮ ለምነቱ እንዲሁም የሕዝቡ ምጣኔ ሀብታዊ አቋም በሚያሳስብ ሁኔታ ላይ ነው የሚገኘው። ዛፉ ተጨፍጭፎ፣ አፈሩ ተሸርሽሮ ያለቀና ድንጋዩ የገጠጠ በመሆኑ አካባቢው ተጐሳቊሎ አሳዛኝ እይታን አትርፏል። ነዋሪው ገበሬ እንደ መሆኑ ከዚህ መሬት ላይ የሚያመርተው ሰብል ቤተሰቡን ለማኖር ከሚያስፈልገው መጠን በጣም አነስተኛ ነው። በመሆኑም ጉስቋላው የአካባቢው ሕዝብ የራሱን ችግር አሸንፎ እንደ አባቶቹ አብያተክርስቲያንን የመጠገንና ካህናቱን የመደገፍ አቅም የለውም። ስለሆነም ያሉት አብያተክርስቲያናት እየፈረሱና እየወደቁ ይገኛሉ። የወርቅ ጉር ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያንም በተጠቀሰው ችግር ምክንያት ወደ መዘጋቱ ተቃርቦ ነበር።

የወርቅ ጉር ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን በአገራችን ከታወቁት ቀደምት አብያተ ክርስቲያን አንዱ ነው። ቤተክርስቲያኑ በ14ኛው ምዕተ ዓመት በአፄ ዘረዐ ያዕቆብ ዘመን ተተክሎ በ15ኛው ምዕተ ዓመት በተካሄደ የሃይማኖት ወረራ ተቃጥሎ ንዋየ ቅድሳቱ እንደ ተዘረፉ ወይንም እንደ ተቃጠሉ ሲነገር፣ ጽላቱ ግን በካህናቱ ብርታት በቤተክርስቲያኑ አካባቢ በሚገኝ ዋሻ ተቀብሮ እንደነበር ታሪኩ ይናገራል። ቤተክርስቲያኑ ቢቃጠልም ስፍራው ቅድስናውን እንደ ጠበቀና በቅጥር ግቢውም የሚገኘው ዐፀድ ግርማ ሞገሱን እንደተላበሰ የሚገኝ ሲሆን፣ በአባቢው የሚገኘው ጸበልም በፈዋሽነቱ ብዙ ተአምራትን በመሥራት ዝናን ለማትረፍ ችሎአል።

በ1955 ዓ.ም የአካባቢው ተወላጆች፣ በተለይም ክቡር ብላታ ደምሴ ወርቅ አገኘሁ እና አቶ መኮንን ወርቅ አገኘሁ፣ ለወርቅ ጉር ቅዱስ ገብርኤል አነስተኛ ቤተክርስቲያን አሠርተው ታቦቱ ወደ ቀድሞ ስፍራው ተመልሶ ካህናትም ተመድበውለት የገዳሙ ሥርዓት በመጠኑ እንዲቀጥል ተደረገ። ባለፈው ሩብ ምዕተ ዓመት ውስጥ በአገራችን በደረሰው ለውጥ ምክንያት ራሳቸውን ችለው ይተዳደሩ የነበሩ አብያተክርስቲያን በየሰበካቸው ካሉ ምዕመናን በሚገኝ ዕርዳታ ብቻ እንዲተዳደሩ መደረጉ ይታወሳል። ገዳማት በአብዛኛው ከሕዝብ መኖሪያ ራቅ ብለው የሚገኙ እንደ መሆናቸው መጠን፣ ይደግፏቸው የነበሩ የወቅቱ ባለርስቶች ከወደቁ በኋላ ደጋፊ በማጣት በአብዛኛው በመፈራረስ ላይ ይገኛሉ። ስለዚህም በእነሱ ይተዳደሩ የነበሩት መነኮሳት ከየገዳማቱ እየወጡ በዱርና በከተማ ተንከራትተው እየባከኑ ነው። በመሆኑም ለአብያተክርስቲያንና ለካህናት አለቆች መንፈሳዊ አመራር ይሰጡ የነበሩ የበቁ መነኮሳትና መናንያን ቊጥራቸው በአሁኑ ጊዜ እየተመናመነ ይገኛል። ይህ ሁኔታ የእኛነታችን መታወቂያና መኵሪያችን በሆነችው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ላይ የሚያስከትለውን መዳከም በማስተዋልና በመገንዘብ ችግሩን የመቋቋምና መፍትሔም የመፈለግ ኃላፊነት እንዳለበት በመገንዘብ፣ የወርቅ ጉር ቅዱስ ገብርኤልን ቤተክርስቲያን በተቻለ መጠን ለማሠራትና የአካባቢው ነዋሪም የሚራዳበትንና የሚሳተፍበትን የልማት መርሐ ግብር ለመዘርጋት ኮሚቴው ተቋቋመ።

## 2. የኮሚቴው/ድርጅቱ ዓላማ

የቤተክርስቲያኑ ሥራና ልማት ድርጅት ጠቅላላ ዓላማ ይህችን በመውደቅ ላይ ያለች ታሪካዊ ገዳም ለመታደግ ቤተ ክርስቲያኑን ዘላቂነት ባለው ሕንፃ ለመተካትና ለሚያገለግሏት መነኮሳትና ካህናት መኖሪያና የተሻሻለ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ለማቋቋም፣ በተጓዳኝም በአካባቢው የሚኖሩት ምዕመናን የሚረዱበትን የልማት ሥራዎች በማከናወን የአካባቢውንና የነዋሪውን አሳዛኝ እይታ በመጠኑም ቢሆን ለመለወጥ ነው።

ዘርዘር ባለ መልኩ የድርጅቱ ዓላማ የሚከተሉትን ያካትታል:-

1ኛ. ከምዕመናን የገንዘብ ዕርዳታ በማሰባሰብ የቤተክርስቲያን ሕንፃ መገንባት፣

2ኛ. የአገራችን ገዳማት ባህልና አገልግሎት ጨርሶ እንዳይጠፋና ቅርስነቱም ተጠብቆ እንዲኖር አስተዋጽኦ ማድረግ፣

3ኛ. የበቁ መነኮሳት ተሰባስበው ለአገራችንና ለወገናችን ደኅንነት ፈጣሪአችንን የሚማለዱበትና ለካህናት አለቆችም ሆነ ለምዕመናኑ በተቻለ መጠን መንፈሳዊ አመራር መስጠት የሚያስችለውን ሁኔታ ማመቻቸት፣

4ኛ. በቅኔና ዜማ፣ በመጻሕፍትም ትርጓሜ የታወቁ ምሁራን ተሰባስበው ለአካባቢው አብያተ ክርስቲያን ምርጥ አገልጋዮች የሚያሠለጥኑበት መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ማቋቋም፣

5ኛ. ካህናቱና የአካባቢው ሕዝብ ኑሮአቸውን ሊያሻሽሉ የሚያስችሉ ተቋማት የሚደረጁበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

6ኛ. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ካህናት ዛፍ የመትከልና ዐፀድን የመንከባከብ ባህላቸው ይበልጥ ዳብሮ አካባቢውን እንዲያለሙ መርዳት፣

7ኛ. በአካባቢው የሚገኙ ቁሳዊና መንፈሳዊ ትውፊቶች የሚጠበቁበትን ሥርዓት ማመቻቸትና ቅርስነታቸው ተጠብቆ ለቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፉ ማገዝ።

## 3. ስልት

ድርጅቱ ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ በቅድሚያ ያከናወነው መተዳደሪያ ደንብ አዘጋጅቶ ሕጋዊነት እንዲኖረው ከቤተክህነት አስፈላጊውን ፈቃድ ማግኘትና ሥራውን የሚያንቀሳቅሱ ኮሚቴዎች ማዋቀር ነበር። በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የበላይ ጠባቂነት በአካባቢው ሰበካ ጉባኤ አንድ ኮሚቴ ተቋቋመ። በዐቢይ ኮሚቴው ሥር የሚከተሉት ኮሚቴዎች ተዋቅረው የሥራ መመሪያ ወጣላቸው።

- የቤተክርስቲያን ሥራ አስተባባሪ ኮሚቴ
- የገንዘብ አሰባሳብ ኮሚቴ
- የልማት ኮሚቴ
- የበዓል አስተባባሪ ኮሚቴ
- የሒሳብ አያያዝና ኦዲተር ኮሚቴ

እነዚህ ኮሚቴዎች ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት ተከፋፍለው መሥራት እንዲችሉ እንዳስፈላጊነታቸው ንዑሳን ኮሚቴዎችን አቋቁመው የሥራ መመሪያ ወጣላቸው።

እያንዳንዱ ኮሚቴ የሥራ ዕቅዱን ለዐቢይ ኮሚቴው አቅርቦ እንዲጸድቅ ካደረገ በኋላ ክንውኑን በየወሩ እያቀረበ አስተያየት ይሰጥበታል።

## 4. ክንውን

የኮሚቴው የመጀመሪያ ዕቅድ የቤተክርስቲያኑን ሕንፃ በመጠነኛ ይዘት ለመሥራት ነበር። ነገር ግን ከኮሚቴው አባላትና የኮሚቴውን የሥራ ዕቅድ በቅርብ በሚከታተሉ ምዕመናን የወርቅ ጉር ቅዱስ ገብርኤል እንደ ማዕከል በመሆኑ በአካባቢው ለሚገኙና ተመሳሳይ ችግር ላለባቸው አብያተክርስቲያን አገልግሎት ቢሰጥ ጠቀሜታው የበለጠ ይሆናል በሚል ገንቢ ሐሳብ መሠረት፣ የሕንፃው መጠንና ይዘት ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲያድግ ተወሰነ። በዚህም መሠረት የዐቢይ ኮሚቴው አባል የሆኑት የቤተክርስቲያኑ መሃንዲስ ይህንኑ ዓላማ በመከተል በመጀመሪያ የቀረበውን የሕንፃውን ንድፍ በማሻሻል አሁን የሚታየውን ቅርዕ፣ መጠንና ጥራት እንዲይዝ ተደርጓል።

የኮሚቴውን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ የገንዘብ አሰባሳቢ ኮሚቴ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች እያዘጋጀ ገንዘብና ማቴሪያል ማሰባሰብ ጀመረ። ዋና ዋናዎቹ የዕርዳታ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች:-

- በታወቁ ሆቴሎች የዕርዳታ ማሰባሰቢያ ምሽት ማዘጋጀት፣
- በየዓመቱ ለታኅሣሥ ቅዱስ ገብርኤል በዓል ወደ ገዳሙ የጉዞ ፕሮግራም ማዘጋጀት፣
- በተለያዩ ዝግጅቶች ቶምቦላ፣ ሎተሪ...ማዘጋጀት፣
- ወደ ቤተክርስቲያኑ ለሚመጡና በተለያየ አጋጣሚ ኮሚቴው ለሚያገኛቸው ምዕመናን ዓላማውን በመግለጽ የበኩላቸውን ዕርዳታ የሚያዘጋጁበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- የሚሰበሰበው ገንዘብ ሁሉ ሕጋዊ ደረሰኝ እየተቈረጠለት ባንክ እንዲገባ ተደርጎ፣ ማናቸውም ወጪ አስፈላጊነቱ በመሃንዲሱና በቤተክርስቲያን አሠሪ ኮሚቴው ሲረጋገጥ በዐቢይ ኮሚቴው ሊቀመንበርና በዋና ጸሐፊው ፊርማ ወጪ ማድረግ።





www.ethiopianorthodox.org

በልማቱ በኩል ታስቦ የነበረው አካባቢውን በደን መሸፈን፣ ትምህርት ቤትና ክሊኒክ ማቋቋም፣ ለአካባቢው ሕዝብ ተጨማሪ ገቢ የሚያስገኙ ፕሮጀክቶች ማቋቋም ነበር። እስካሁን መጠነኛ የዛፍ ችግኞች መትከል ቢቻልም በልማቱ በኩል አመርቂ ውጤት ገና አልተገኘም። የዛፍ ተከላውን ዕቅድ ለየት የሚያደርገው «የዛፍ ጉዲፈቻ» የተሰኘው ፕሮግራማችን ነው። በዚህ ፕሮግራም መሠረት በጎ አድራጊ ምዕመናን ለአንድ ዛፍ አንድ ብር ሒሳብ የተቻላቸውን እንዲሰጡ ይደረግና የአካባቢው ገበሬዎች ተክለውና ተንከባክበው ላጸደቁት ለእያንዳንዱ ዛፍ በየዓመቱ አንድ ብር እንዲሰጣቸው ይደረጋል። የዚህን ዕቅድ ጥቅም በጎ አድራጊዎች የተገነዘቡት ቢሆንም፣ የአካባቢው ሕዝብ ገና አልለመደውም። ይህን ለማለማመድ በየዓመቱ የሐምሌ ገብርኤልን ዋዜማ «የዛፍ ቀን» ብለን የኮሚቴው አባላት ከተገኙት የአካባቢው ምዕመናን ጋር ችግኝ መትከል ጀምረናል።

የበዓል ዝግጅቱን በተመለከተ በየዓመቱ የታኅሣሥ ገብርኤልን በዓል ለማክበር ወደ ወርቅ ጉር ለሚሄዱ ምዕመናን አውቶቡስ ተከራይቶ በማቅረብ፣ በቤተክር ስቲያኑ አካባቢ ዳስ በመጣል፣ ምግብና መጠጥ የመሳሰ ሉትን አገልግሎቶች በማቅረብ ልዩ አስተዋፅኦ አድርጓል። በመሆኑም ባለፉት አሥር ዓመታት ከአዲስ አበባ ወደ ወርቅ ጉር የሚሄዱ ምዕመናን ቍጥር በየዓመቱ እያደገ በመሄድ ላይ ይገኛል። በ1980 ዓ.ም በአንድ አውቶቡስ የተጀመረው የጉዞ ፕሮግራም በ1992 ዓ.ም አሥራ አራት አውቶቡሶችንና በርከት ያሉ የግል መኪኖችን ለማካተት ችሏል።

አባታችን አቡነ ኤፍሬም እንዳሉት ይህ ዝንባሌ ወርቅ ጉርን «ዳግማዊ ቁልቢ» ሳያሰኘው አይቀርም። እውነትም ቦታው ለአዲስ አበባ ያለው ቅርበት፣ የአካባቢው ተፈጥሮ ልዩ ስሜት የሚቀሰቅስ በመሆኑና ምዕመናን ለሕዝቡ መሻሻል አስተዋፅኦ የማድረግ ዕድል ስለሚኖራቸው፣ እንዲሁም በሌሎችም ምክንያቶች የዚህ ገዳም ታዋቂነትና መስህብ ወሰን ያለው አይመስልም።

## ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሔዎች

ዕቅድን ተግባራዊ ለማድረግ በሚወሰድ እርምጃ ይብዛም ይነስም የሚያጋጥሙ እንቅፋቶች ይኖራሉ። የወርቅ ጉር የቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሥራና ልማት ኮሚቴ በየወቅቱ በርካታ ችግሮች ገጥመውት ነበር። በኮሚቴው አባላት ቁርጠ መንፈትና ተባብሮ የመሥራት ችሎታ የቤተ ክርስቲያኑን ሕንፃ በተመለከተ ያጋጠሙትን በርካታ ችግሮች ተቋቁሞ ዕቅዱን ተግባራዊ ማድረግ ችሏል።

እስካሁን የረባ ውጤት ያልተገኘው ልማቱን በተመለከተ ነው። ወደ ኋላ ዞር ብለን ስናስተውለው የችግሩ ዋና ምክንያት ዕቅዶችን ተግባራዊ የሚያደርግ ባለሙያ በቦታው ላይ ያለመመደብ ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ አወቃቀራችን በኮሚቴ ሳይሆን ድርጅታዊ መሆን ይኖርበታል። የኮሚቴ አባላት ሐሳብ በማመንጨትና ዕቅድ በማውጣት፣ ግፋ ሲልም ገንዘብ በማሰባሰብ እንጂ የዕለት ተዕለት ሥራ ማከናወን አይችሉም። ስለዚህ የልማት ሥራን ለማንቀሳቀስ መንግሥታዊ ያልሆነ አገር በቀል በጎ አድራጎት ድርጅት NGO አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል። ስለሆነም ይህንኑ ሊያሟላ የሚችል በጎ አድራጎት ድርጅት በማቋቋም ላይ ነን። በዚህ ድርጅት አማካይነት በአካባቢው ት/ቤትና ክሊኒክ ይቋቋማል፤ የመሬት አጠቃቀም ዘዴ ተግባራዊ ይሆናል። የውኃና የማገዶ አቅርቦት ይሻሻላል። በአጠቃላይ የአካባቢው ሕዝብ የተሻለ ኑሮ እንዲያገኝ ይደረጋል። ይህ ሁሉ የሚሆነው በምዕመናኑና የተለያዩ በጎ አድራጊዎች በሚሰጡት ድጋፍ ነው። በመጠነኛ አስተዋጽኦ ወገንን መርዳት መቻል በራሱ ትልቅ ዕድል መሆኑን ተገንዝቦ በዕድሉ ወዲያው መጠቀም ከፍተኛ የሕሊና ዕረፍትና እርካታ ይሰጣል። ❑

### አገሬ

ገብረክርስቶስ ደስታ

እዚያ ዘመድ አለ
ሁሉም የናት ልጅ ነው
ሁሉም ያባት ልጅ ነው
ጠላትም አንዳንዴ ይመጣል መቃብር
ባላጋራም ቸር ነው «ያገር ልጅ» ሲቸግር
መቅደስ ነው አገሬ
አድባር ነው አገሬ
አገሬ ዓርማ ነው የነፃነት ዋንጫ
በቀይ የተጌጠ በአረንጓዴ ቢጫ
አገሬ ታቦት ነው መቅደስ የሃይማኖት
ዘመን የፈተነው በጠበል በጸሎት
ለምለም ነው አገሬ
ውበት ነው አገሬ
ብሞት እሄዳለሁ ከመሬት ብገባ
እዚያው ነው አፈሩ የማማ ያባባ
ስሳብ እሄዳለሁ ቢሰበርም እግሬ
አለብኝ ቀጠሮ ከትውልድ አገሬ
አለብኝ ቀጠሮ
ከትውልድ አገሬ ካሳደገኝ ጓሮ።

SAFARI PALACE
HOTEL
Nazareth
Four Star Hotel
Spacious Rooms
4 Restaurants
Conference Center
Swimming Pool
Health Fitness Center
Relaxing Garden
Entertainment for all Ages
Baby Sitting
Nazareth Reservations Tel.: 02 11 40 38

የወርቅ ጉር ቅዱስ ገብርኤል የቤተክርስቲያን
ህንፃ ሥራና ልማት ኮሚቴ
ዓላማውን ለማሳካት እርዳታ ለምታደርጉ
በአቢሲኒያ ባንክ
የተንቀሳቃሽ ሒሳብ ቁጥር 48
የከፈተ መሆኑን ይገልፃል።
ለምታደርጉት አስተዋፅኦ በጉዳሙ ስም
ምስጋናችንን እናቀርባለን።



www.ethiopianorthodox.org